# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ማክሰኞ 83ኛ ዓመት ቁጥር 085 ኅዳር 25 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







## የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ጉብኝት አመርቂ ውጤት የተገኘበት ነው

### - የኢትዮጵያ አረንጓዴ ዐሻራ በሌሎች ሀገራት እንደተሞክሮ ተወስዷል

**ማርቆስ በላይ**



(ከግራ ወደ ቀኝ) አንቶኒዮ ጉተሬዝ፣ ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እና ሼህ ቢን ዛይድ

አዲስ አበባ፡- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የሰሞኑ ጉብኝትና የተለያዩ ጉባዔዎች ተሳትፎ አመርቂ ውጤት የተገኘበትና የኢትዮጵያን በጎ ገጽታ ከፍ ያደረገ መሆኑን የመንግሥት ኮሙኒኬሽን ሚኒስትር ለገሰ ቱሉ (ዶ/ር) ገለጹ፡፡

የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድን (ዶ/ር) የአውሮፓና የዩናይትድ አረብ ኤምሬትስ ቆይታ አስመልክተው በሰጡት ማብራሪያ እንደገለጹት፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሰሞኑ ጉብኝትና የተለያዩ ጉባዔያት ተሳትፎ የተሳካ፣ አመርቂ ውጤት የተገኘበትና የኢትዮጵያ ክብር የታየበት ብሎም በጎ ገጽታዋ ከፍ ያለበት ነው፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በቆይታቸው በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት (ተመድ) የኢንዱስትሪ ልማት ድርጅት ዓመታዊ ጉባዔ፣ በአየር ንብረት ለውጥ የመሪዎች ጉባዔ እና በቼክ ሪፐብሊክ ይፋዊ ጉብኝት አድርገዋል ያሉት ዶክተር ለገሰ ፤ ከጉባዔው ጎን ለጎን ከተለያዩ ሀገራት መሪዎችና የዓለምአቀፍ ተቋማት መሪዎች ጋር ውጤታማ የሁለትዮሽ ውይይት ማድረጋቸውን አመላክተዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በኢንዱስትሪ ልማት ድርጅት ዓመታዊ ጉባዔ ላይ በክብር እንግድነት


የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል









ፎቶ፡ ገበበ ገብሬ

ሽመልስ ገዛኸኝ (ዶ/ር)

## ዓለም አቀፍ የቀዶ ጥገና ህክምና የብቃት ማረጋገጫ ፈተና በአዲስ አበባ ተሰጠ

### - ፈተናው በኢትዮጵያ መሠጠቱ የሜዲካል ቱሪዝምን ያሳድጋል

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- በ14 የአፍሪካ ሀገራት መሥራት የሚያስችል ዓለም አቀፍ የቀዶ ጥገና ህክምና የብቃት ማረጋገጫ ፈተና በአለርት አጠቃላይ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ተሰጠ። ፈተናው በኢትዮጵያ መሰጠቱ ለሜዲካል ቱሪዝም እድገት በጎ አስተዋጽኦ የሚያደርግ መሆኑ ተጠቁሟል።

የአለርት አጠቃላይ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ዋና ሥራ አስኪያጅ ሽመልስ ገዛኸኝ (ዶ/ር) በወቅቱ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ የፈተና ዝግጅቱ በኢትዮጵያ መካሄዱ ሀገሪቷ በሜዲካል ቱሪዝም እየተጓዘችበት ያለውን ሁኔታ የሚያጠናክር ነው። ተፈታኞችም ሆኑ ፈታኞች ከተለያዩ የዓለም ሀገራት እንደመምጣታቸው ዓለም አቀፍ ከሆኑ ጤና ተቋማት ጋር ትስስር ለመፍጠር፣ ተሞክሮ ለመውሰድና የክህሎት


ዓለም አቀፍ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




ፎቶ - በሪሁን ታደሰ

አቶ መንግሥቱ ንጉሤ

## ባለሥልጣኑ የኢትዮጵያና የጂቡቲን የአየር ትራንስፖርት ደህንነት እያስጠበቀ ነው

### - ቦሌ አየር ማረፊያ በዓመት 144 ሺህ አውሮፕላኖችን ያስተናግዳል

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያንና የጂቡቲን የአየር ትራንስፖርት ደህንነት ሳምንቱን ሙሉ 24 ሰዓት በመጠበቅ ውጤታማ ሥራ እያከናወነ መሆኑን


ባለሥልጣኑ የኢትዮጵያና ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


## ትግበራ የናፈቀው "ቅድሚያ ለደህንነት" መርህ

**ተስፋ ፈሩ**



ዓለም አቀፉ የላብ አደሮች ድርጅት ከሳምንት በፊት በድረ ገጹ እንዳስነበበው፣ ዓለማችን በየዓመቱ ሦስት ሚሊዮን የሚጠጉ ሰዎችን ከሥራ ጋር በተያያዙ አደጋዎችና በሽታዎች ታጣለች፡፡ በሀገራችንም በየዓመቱ በርካታ ዜጎች በነዚህ ምክንያቶች ሕይወታቸውን ያጣሉ፡፡

በኢትዮጵያ ሠራተኛ ማህበራት ኮንፌዴሬሽን (ኢሰማኮ) የሙያ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ ባለሙያው ደምስ ወንድአፈራው የሥራ ላይ አደጋ ብዙዎችን ለአካል ጉዳት፣ ለጤና መታወክና ሞት እየዳረገ ቢሆንም ተገቢው ትኩረት እንዳልተሰጠው ይናገራሉ፡፡

መደበኛ ባልሆነ መንገድ የምንሰማቸው የሥራ ላይ አደጋ ጉዳቶች ብዙ ናቸው፡፡ አሰሪዎች በሥራ ቦታዎች የሚደርሱ አደጋዎችን ይደብቃሉ፡፡ ችግሩ በስፋቱ ልክ እንዳይታወቅ ያደረገው አንዱ ምክንያት ሠራተኞች ላይ የሚደርሱ ጉዳቶችን መዝግቦ ለመንግሥት አካል ሪፖርት ማድረግ የአሰሪው ኃላፊነት እንዲሆን መደረጉ ነው፡፡ መረጃ ለመሰብሰብ የተዘረጋው ሥርዓት ደካማ በመሆኑ


ትግበራ የናፈቀው ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል








# የቢሾፍቱ ከተማ ጂፒ ኤስ መተግበሪያ በመጪው ወር ይፋ ይደረጋል

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- የቢሾፍቱ ከተማን ህንጻዎች፣ መኖሪያ ቤቶችና መንገድ የሚያሳይ የጂፒ ኤስ መተግበሪያ በታህሳስ ወር ይፋ እንደሚያደርግ የኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት አስታወቀ። ይህም በአዳማ፣ በአዲስ አበባ፣ በባህር ዳር፣ በደብረ ብርሃን፣ በሃዋሳና በጅማ ከተሞች ተግባራዊ እንደሚደረግ ተገልጿል።

የኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር አቶ አብዲሳ ይልማ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ኢንስቲትዩቱ ቴክኖሎጂ የማልማት፣ ሳተላይትን የመቆጣጠር፣ ከሳተላይት የሚመጡ መረጃዎችን የመቀበልና ጥቅም ላይ የማዋል ሥራዎችን ይሠራል። በ2016 የመጀመሪያው ሩብ ዓመትም ከዲጂታል አድራሻ ሥርዓት ጋር በተገናኘ ጠንካራ ሥራዎች ተሠርተዋል።

በዲጂታል አድራሻ ሥርዓት ሰዎች ከቦታ ቦታ ሲንቀሳቀሱ ጎግል ጂፒ ኤስ ይጠቀማሉ። ነገር ግን በዚህ የተሟላ አገልግሎት ማግኘት አይቻልም ያሉት አቶ አብዲሳ፤ ኢንስቲትዩቱ ይህንን ችግር ለመፍታት የሚያስችል ሀገር በቀል መተግበሪያ ማለትም የጂፒ ኤስ አገልግሎትን መተካት የሚችል መተግበሪያ አልምቷል ብለዋል።

ይህም የቢሾፍቱ ከተማን እያንዳንዱ ህንፃና



አቶ አብዲሳ ይልማ

መኖሪያ ቤት የሚያሳይ ሲሆን መተግበሪያው በታህሳስ ወር ይፋ እንደሚደረግ የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር አቶ አብዲሳ ተናግረዋል።

እንደ አቶ አብዲሳ ገለፃ፤ የጂፒ ኤስ መተግበሪያውን ተግባራዊ ለማድረግ በአዲስ አበባ ኮልፌ ቀራኒዮ ተሞክሮ ነበር። አዲስ አበባ ትልቅ ከተማ በመሆኗና ለኢንስቲትዩቱ ሥራ አዲስ በመሆኑ መተግበሪያውን ተግባራዊ ማድረግ ውስብስብ ሆኗል ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ መተግበሪያውን ተግባራዊ ለማድረግ ትንሽና በቅርብ ርቀት በሚገኝ ከተማ መምረጥ አስፈላጊ ሆኗል፤ በዚህም የቢሾፍቱ ከተማ ተመርጧል ብለዋል።

"ጂፒ ኤስ ዋና ዋና መንገዶችንና ህንፃዎችን ያሳያል እንጂ የግለሰብ ቤትን ለይቶ አያመለክትም። ኢንስቲትዩቱ ያለማው ቴክኖሎጂ ግን የእያንዳንዱን ግለሰብ ቤትና የውስጥ ለውስጥ መንገድ በመለየት የዲጂታል ኮድ ይሰጣል" ብለዋል።

መተግበሪያው በስማርት ስልክ የሚጫን ሲሆን ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ የሚደረግ እንቅስቃሴን ማሳለጥ የሚያስችል ነው። ይህም ለአምቡላንስና ለእሳት አደጋ አገልግሎት፣ ዘመድ ለመጠየቅ፣ ጭነትን በተገቢው ቦታ ለማድረስ እና በቀላሉ ለማጓጓዝ የሚያስችል ሀገር በቀል መተግበሪያ መሆኑን ጠቁመዋል።

በቀጣይ መተግበሪያውን በአዳማ፣ በአዲስ አበባ፣ በባህር ዳር፣ በደብረ ብርሃን፣ በሃዋሳና በጅማ ተግባራዊ ለማድረግ እቅድ ተይዟል ያሉት አቶ አብዲሳ፤ አሁን ላይ በቢሾፍቱ ያሉትን ህንፃዎችና መኖሪያ ቤቶች እንዲሁም መንገዶች የሚያሳይ ኔትወርክና ኮድ ተሰጥቷል ብለዋል።



አቶ አክሊሉ ታደሰ

# የድሬዳዋ ነጻ ንግድ ቀጣና የልዩ ኢኮኖሚክ ዞን አዋጁ ሲጸድቅ በሙሉ አቅሙ ሥራ ይጀምራል

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- የልዩ ኢኮኖሚክ ዞን አዋጅ በተወካዮች ምክር ቤት ሲጸድቅ የድሬዳዋ ነጻ የንግድ ቀጣና በሙሉ አቅሙ ሥራ እንደሚጀምር የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን አስታወቀ፡፡

የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ አክሊሉ ታደሰ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በድሬዳዋ ነጻ የንግድ ቀጣና ውስጥ የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ቀደም ብሎ ሥራ የጀመረ በመሆኑ የተዘጋጁ ሼዶች ወደ መሙላቱ ደረጃ ደርሰዋል፡፡

የሎጀስቲክስና የወጪና የገቢ ምርት የሚካሄድባቸው ኮሪደሮችን ወደ ሥራ ለማስገባት ዝግጅታቸው ተጠናቆ የሕግ ማዕቀፍ መጽደቅን በመጠባበቅ ላይ መሆናቸውን የገለጹት አቶ አክሊሉ፤ የሕግ ማዕቀፉና የልዩ ኢኮኖሚክ ዞን አዋጁ በሚኒስትሮች ምክር ቤት መጽደቁን ተናግረዋል፡፡ ሆኖም አዋጁ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሲጸድቅ የነጻ ንግድ ቀጣናው በሙሉ አቅሙ ወደሥራ ይገባል ብለዋል፡፡

እንደ ሥራ አስፈጻሚው ማብራሪያ፤ የሎጀስቲክስና የንግድ ሥራውን ወደ ሥራ ለማስገባት አስፈላጊው ዝግጅት ተጠናቋል፡፡ ከዝግጅቶች መካከል ወደ ነጻ የንግድ ቀጣናው የሚገቡ ባለሀብቶች የሚመለመሉበት የመስፈርት ዝግጅት ተደርጓል፡፡ ባለሀብቶች ወደ ንግድ ቀጣናው በሚገቡበት ወቅት የሚከፍሉበት የታሪፍ ዝግጅትና ለታሪፍ የሚሆን የሕጋዊ ማዕቀፍ ዝግጅትም ተካሂዷል፡፡

የድሬዳዋ ነጻ የንግድ ቀጣና በሙሉ አቅሙ ወደ ሥራ ሲገባ ሌሎች ሀገራት ከነጻ የንግድ ቀጣና ያገኙትን ጥቅም ያስገኛል ተብሎ ይጠበቃል ያሉት አቶ አክሊሉ፤ የድሬዳዋ ነጻ የንግድ ቀጣናም ከመላ ሀገሪቱ ለተማረው የሰው ኃይልና ለጉልበት ሠራተኞች ከፍተኛ የሆነ የሥራ እድል ወደ መፍጠር ይሸጋገራል ብለዋል፡፡ እንደ ሀገር ችግር የሆነውን የውጭ ምንዛሬ እጥረት ለመፍታትም ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ጠቁመዋል፡፡

እንደ አቶ አክሊሉ ገለጻ፤ በኢትዮጵያ የሚመረቱ ምርቶች በተቀላጠፈ መንገድ ወደ ዓለም ገበያ እንዲደርስ የማሳለጥ ሚናው የጎላ ይሆናል፡፡ ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ምርቶች በትራንስፖርት መዘግየት ምክንያት በህብረተሰቡ ላይ ለኑሮ ውድነት ምክንያት የሆኑ ጉዳዮችን ያስተካክላል፡፡ በአነስተኛ ወጪ ዜጎች የሚፈልጓቸው ምርቶች ወደ ሀገር እንዲገቡ ያደርጋል፡፡ እንዲሁም የኑሮ ውድነትን ጫና በማቃለልና በሀገር ውስጥ የተጀመረውን የኢኮኖሚ እድገት ወደ ተሻለ ደረጃ በማሸጋገር ረገድ ትልቅ ተስፋ ይኖረዋል፡፡

በነጻ ንግድ ቀጣናው ውስጥ ባንኮች፣ ሆቴሎች፣ መዝናኛ ማዕከላት፣ አፓርትመንቶች፣ የውጭ ድርጅቶች፣ የፋይናንስ ተቋማት፣ የጉምሩክ ማዕከል አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚከትሙ ሲሆን ውሃ፣ ቴሌኮም፣ የኃይል አቅርቦት፣ የመኖሪያ ቤቶች፣ የመዝናኛ ማዕከላት ሥራዎች መጠናቀቃቸውንና ባንኮች፣ ግምሩክና የመንግሥት ተቋማት ሥራ መጀመራቸውንም ሥራ አስፈጻሚው ተናግረዋል፡፡



# በክልሉ ከሁለት ሚሊዮን በላይ ሰዎችን ከወባ በሽታ ወረርሽኝ መከላከል ተችሏል

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- በክልሉ የተሻለ የጤና አገልግሎት በማቅረብ ከሁለት ሚሊዮን በላይ ሰዎችን ከወባ በሽታ ወረርሽን መከላከል እንደተቻለ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ጤና ቢሮ አስታወቀ፡፡ ባለፉት ሶስት ወራት በክለሉ የወባ ወረርሽኝን ለመከላከል አንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን አጎበር ተሠራጭቷል።

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ጤና ቢሮ ኃላፊ አቶ ኢብራሂም ተማም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በተደረገው የተቀናጀ የጤና አጠባበቅ ሥርዓትና የአጎበር ስርጭት ከሁለት ሚሊዮን በላይ ሰዎችን ከወባ ወረርሽኝ መከላከል ተችሏል፡፡

"ባለፉት ሁለት ዓመታት የወባ ወረርሺኝ ጫና ከፍተኛ ነበረ፤ ወረርሺኙን ለመከላከል የህብረተሰቡን ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ ተሠርቷል" ያሉት ኃላፊው፤ ከጤና ባለሙያዎችና ለህብረተሰቡ ጋር በመቀናጀት ለወባ ትንኝ መራቢያ የሆኑ ውሃ ያቆሩ ቦታዎች የማዳፈን ሥራ እየተሠራ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

በክልሉ የወባ ወረርሺኝን ለመከላከል ባለፉት ሶስት ወራት ከአንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን በላይ አጎበር መሠራጨቱን አስታውቀው፤ በህብረተሰቡ በኩል ከአጎበር አጠቃቀም ጋር በተያያዘ የተወሰነ ክፍተት በመኖሩ ችግሩን ለመፍታት በኤክስቴንሽን ፕሮግራም የአጠቃቀም ሥልጠና መሰጠቱን ተናግረዋል፡፡

በተጨማሪም የወባ ወረርሽኝን ለመከላከል ሰባት ሺ 634 ኪሎ ግራም የፀረ-ወባ ኬሚካል በተለያዩ ቦታዎች መረጨቱን ገልጸው፤ ክንውኑ በአንጻራዊነት የወባ ስርጭቱን መቀነስ አስችሏል ሲሉ አስረድተዋል።

አሁን ላይ ሁለት ሺህ 185 ሊትር የፀረ-ወባ ኬሚካል በ54 ወረዳዎች መሰራጨቱን አመላክተዋል፡፡

በተጨማሪም ከ600 ሺህ ካሬ ሜትር ስፋት ያለው የወባ ትንኝ መራቢያ ሥፍራዎች ላይ የኬሚካል ርጭት እየተካሄደ እንደሚገኝ አመላክተዋል፡፡

በሕክምና ተቋማት የመድኃኒት እጥረት እንዳይኖር ከጤና ሚኒስቴርና ከኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት ጋር በመተባበር እየተሠራ መሆኑን ገልጸው በወባ በሽታ የተጠቁ ሰዎች በአፋጣኝ ህክምና እንዲያገኙ እየተደረገ ነው ብለዋል፡፡

በክልሉ የወባ ምልክት ከታየባቸው 265 ሺህ 540 ሰዎች ውስጥ 156 ሺህ 996 ሰዎች በሽታ ተገኝቶባቸው ሕክምና ማግኘታቸውን አስታውቀዋል።

የወባ በሽታ በክልሉ ሁሉም ዞኖች የተከሰተ ቢሆንም በተለይ በቤንች ሸኮ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች ላይ የወባ ወረርሽኝ ስርጭቱ ከፍተኛ መሆኑን የገለጹት ኃላፊው፤ በተሠሩ የቁጥጥር ሥራዎች ስርጭቱን መግታት እንደተቻለ አመላክተዋል፡፡

የዝናብ ሁኔታው ቀጣይነት ያለው በመሆኑ የወባ ወረርሽኝ ስጋቱን እንዳያባብስ ህብረተሰቡ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ሊያደርግ እንደሚገባም ኃላፊው መልዕክት አስተላልፈዋል።

# በበጋ መስኖ ስንዴ ከአንድ ሚሊዮን ሄክታር በላይ መሬት በዘር ተሸፍኗል

**አዲሱ ገረመው**



አዲስ አበባ፡- በበጋ መስኖ ስንዴ እስካሁን ከአንድ ሚሊዮን 65 ሺህ ሄክታር በላይ መሬት በዘር እንደተሸፈነ ግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ። 117 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማግኘት በሁሉም ክልሎች በስፋት እየተሠራ ነው።

በግብርና ሚኒስቴር የሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ሥራ አስፈጻሚ አቶ ከበደ ላቀው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ከበጋ መስኖ ስንዴ ጋር በተያያዘ በባህላዊና በትራክተር የማረስና መሬቱን ለዘር ዝግጁ የማድረግ ሥራዎች እየተሠሩ ነው። እስካሁን ከአንድ ሚሊዮን 65ሺህ ሄክታር በላይ የበጋ መስኖ ስንዴ በዘር ተሸፍኗል።

እንደ ሥራ አስፈጻሚው ገለጻ፤ በዘንድሮው የበጋ መስኖ እንቅስቃሴ ከሦስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት 117 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማግኘት በሁሉም ክልሎች በስፋት እየተሠራ ነው። በቅድመ ዝግጅቱ ምዕራፍ እስከ ኅዳር 17 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ ባባህላዊ መንገድ አንድ ነጥብ አንድ ሚሊዮን ሄክታር መሬት፤ በትራክተር ከ638 ሺህ ሄክታር መሬት በድምሩ አንድ ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ታርሷል። ከአንድ ሚሊዮን 65ሺህ 791 ሄክታር መሬት በላይ በዘር ተሸፍኗል። በዚህ ሁሉም ክልሎች ከቅድመ ዝግጅቱ ጀምሮ እየሠሩ ይገኛሉ።

የደረሱ የመኸር ሰብሎችን ከመሰብሰብ ጎን ለጎን የበጋ መስኖ ስንዴን የማልማቱ ሥራ ተጠናክሮ ቀጥሏል ያሉት ሥራ አስፈጻሚው፤ አዳዲስ ቴክኖሎጂን ተጠቅሞ ምርታማነትን ማሳደግ በሚቻልባቸው ሁኔታዎች ላይም ግንዛቤ እየተሰጠ እንዳለ ገልጸዋል።

ከበጋ መስኖ ስንዴ ጎን ለጎን የመደበኛ መስኖ ሥራዎች በተሳካ ሁኔታ እየተሠሩ እንዳለም አመልክተው፤ በመደበኛ የመስኖ ሥራ አትክልትና ፍራፍሬን በስፋት ለማልማት ታስቦ ወደ ሥራ እንደተገባም አስታውቀዋል።

ሥራ አስፈጻሚው፤ የተለያዩ የውሃ አማራጮችን በመጠቀም የበጋ መስኖ ስንዴን በማስፋት የስንዴ ፍላጎትን በሀገር ውስጥ የመተካት ሙሉ አቅም ተገንብቷል ብለዋል። ይህ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ የሚሄድ የልማት ሥራ መሆኑንም ጠቅሰዋል።

ለሀገር ውስጥ ፍጆታ የሚያስፈልገውን 170 ሚሊዮን ኩንታል መሆኑንና ይህንን በመኸሩ፣ በበልግና በበጋው ባሉ ወቅቶች የስንዴ ፍላጎትን የመሸፈን አቅም ተፈጥሯል ሲሉ ገልጸዋል።

የግብርና ሜካናይዜሽንን በመጠቀም የሚታረሰውን መሬትና የሚሰበሰበውን ሰብል የማሳደግ ሥራው ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ጠቅሰው፤ በተለይም ለበጋ መስኖ ስንዴ ቴክኖሎጂውን የማስፋት ሥራው ላይ በትኩረት እንደሚሠራ አመልክተዋል።




# የኢትዮ-ጅቡቲ የባቡር ትራንስፖርት የጭነት አቅም 40 በመቶ ዕድገት አሳይቷል

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮ- ጅቡቲ የባቡር ትራንስፖርት የጭነት አቅም በየዓመቱ ከ35 እስከ 40 በመቶ ዕድገት እያሳየ መሆኑን የኢትዮ-ጅቡቲ ባቡር ትራንስፖርት አክሲዮን ማህበር አስታወቀ፡፡

የአክሲዮን ማኅበሩ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አብዲ ዘነበ (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የባቡር ትራንስፖርቱ የጭነት አቅም እንዲሁም የትራንስፖርት አገልግሎት በየዓመቱ እስከ 40 በመቶ እድገት እያሳየ ነው፡፡

በባቡር አገልግሎቱ ሁለት ሚሊዮን ቶን በላይ ጭነት የማጓጓዝ አቅም መፈጠሩን አመላክተው፤ አሁን ያሉትን 20 የባቡር ጣቢያዎች ለማሳደግ ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን ዶክተር አብዲ አመላክተዋል።

የኢትዮ- ጅቡቲ የባቡር ትራንስፖርት ሥራ ከጀመረ አምስተኛ ዓመቱ እንደሆነው አስታውሰው፤ የባቡር ትራንስፖርቱ የተለያዩ የጭነት መስተጓጉሎችንና ለጭነት የሚወጣው የውጭ ምንዛሬ ወጪ መቀነስ አስችሏል ብለዋል።

የባቡር ትራንስፖርቱ ቀጣናዊ ትስስሩን ይበልጥ ለማጠናከርና የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ለማረጋጋት ጉልህ አስተዋጽዖ እያበረከተ እንደሚገኝ ገልጸው፤ የባቡር ትራንስፖርቱን አቅም ለማሳደግ ከቻይና ሁለት ተቋራጮች ጋር ሲከናወኑ የቆዩ የአቅም ግንባታ ሥራዎች ወደ መገባደድ መድረሳቸውን ተናግረዋል፡፡

በሚቀጥሉት ጊዜያትም አሁን ላይ በባቡር አገልግሎቱ ማጓጓዝ ከሚቻለው ሁለት ሚሊዮን ቶን አቅሙን ወደ አራት ሚሊዮን ቶን ከፍ ለማድረግ ዕቅድ ተያዞ እየተሠራ መሆኑን አስታውቀዋል።

በባቡር ትራንስፖርቱ ላይ የነበረው የኃይል መቆራረጥ ችግር ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ጋር በቅንጅት በመሥራት ከባለፈው ዓመት ጀምሮ ችግሩ ተቀርፎ ተገቢውን አገልግሎት እየተሰጠ እንደሚገኝ አመላክተዋል፡፡

ከስርቆትና ከውድመት ጋር ተያይዞ የነበረውን ችግር ለመቅረፍ ደግሞ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ተገቢው ሥራ በመከናወኑ ስርቆቱን ከ85 በመቶ በላይ መቀነስ መቻሉን አስረድተዋል።

ከውጭ የሚገቡ የባቡርት ትራንስፖርት መቀያየሪያ ዕቃዎችን ለመግዛት የውጭ ምንዛሬ እጥረት ከፍተኛ ችግር ሆኖ ቆይቷል ያሉት ዶክተር አብዲ፤ አሁን ላይ ችግሩን ለመቅረፍ ከብሔራዊ ባንክ ጋራ በጋራ በመሥራት መፍትሄ ለማግኘት ጥረት እየተደረገ መሆኑን ተናግረዋል።

በተያያዘ ለባቡር ትራንስፖርት አቅም ማደግና የኢንዱስትሪና የቴክኖሎጂ ትራንስፎርሜሽንን ለማሳደግ የቤልት ኤንድ ሮድ ኢኒሼቲቭ ጠቀሜታው የጎላ ነው ያሉት ዶክተር አብዲ፤ የተለያዩ ዓይነት ግብዓቶች በብዛትና በፍጥነት ማቅረብ እንዲሁም በዘርፉ የዳበረ እውቀትና ልምድ ለማግኘት ኢትዮጵያ ከኢኒሼቱቩ ይበልጥ ተጠቃሚ መሆን እንደምትችል አመላክተዋክል።

# በአዲስ አበባ የመሬት ይዞታ ማረጋገጥ በቅርቡ ይጀመራል

**ሳሙኤል ወንደሰን**



አቶ ግፋወሰን ዴሲሳ

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ከተማ የመሬት ይዞታ የማረጋገጥ ሥራ በቅርቡ እንደሚጀመር የከተማዋ የመሬት፣ ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አስታወቀ። እስከ 2016 የመጀመሪያው ሩብ ዓመት ከ330 ሺህ በላይ ቁራሽ መሬቶችና የጋራ መኖሪያ ቤቶች በካዳስተር ሥርዓት እንደተመዘገቡም ተገልጿል።

የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር አቶ ግፋወሰን ዴሲሳ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በከተማዋ በ80 ሺህ የመሬት ይዞታዎችን እና 80 ሺህ ባለመብቶችን የማረጋገጥ ሥራ በቅርቡ ይጀመራል።

የመሬት ይዞታ የማረጋገጥ ሥራው ከለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ በስተቀር በሁሉም ክፍለ ከተሞች ተግባራዊ ይደረጋል ያሉት አቶ ግፋወሰን፤ ይህ የይዞታ ማረጋገጥ እወጃ ከተላለፈ ከአሥራ አምሥት ቀን በኋላ የይዞታ ይረጋገጥልኝ ጥያቄዎች ማቅረብ ይቻላል ብለዋል። የማረጋገጥ ሥራውም በ80 ቀታናዎችና በ320 ሰፈሮች እንደሚከናወን ጠቁመዋል።

በከተማዋ 444 ሺህ ቁራሽ መሬት እና 750 ሺህ ባለመብቶች አሉ ያሉት አቶ ግፋወሰን፤ ከዚህ ውስጥ በዘመናዊ የመሬት ይዞታ ምዝገባ ሥርዓት የተከናወነባቸው ቁራሽ መሬቶች 172 ሺህ ሲሆኑ 335 ሺህ የሚሆኑት ደግሞ የግል ይዞታዎች በሊዝ እና በኪራይ የሕዝብ መጠቀሚያ ቦታ ያላቸው ባለመብቶች ናቸው ብለዋል።

እንደ ዋና ዳይሬክተሩ ገለፃ፤ ይዞታዎቹ የግል ይዞታዎች በነባርና በሊዝ ስሪት፤ አረንጓዴ መሠረተ ልማት፣ መንገድ፣ ክፍት ቦታ፣ የአስተዳደር ቦታዎች እና ሌሎችን ይጨምራል። በዘመናዊ የመሬት ይዞታ ምዝገባ ሥርዓት በዋናነት ሁለት ዓይነት ቴክኖሎጂ ተግባራዊ እየተደረገ ሲሆን አንደኛው የሪል እስቴት ካዳስተር ነው። ሁለተኛው ደግሞ መብት ክልከላና ኃላፊነትን የሚመዘግብ ሥርዓት ነው።

በዘንድሮ በጀት ዓመት ሥር ነቀል የሆነ የይዞታ ማረጋገጥ ሥራ ይሠራል ያሉት አቶ ግፋወሰን፤ በጀት ዓመቱ ሲጠናቀቅ ደግሞ በአምሥት ክፍለ ከተሞች የካዳስተር ሥርዓት ሙሉ ለሙሉ እውን ይሆናል። እነዚህም አራዳ፣ ቂርቆስ፣ ልደታ፣ ጉለሌና አዲስ ከተማ ናቸው ብለዋል።

በከተማዋ ካሉት 424 ሺህ በላይ የመሬት ይዞታዎች መካከል በዘመናዊ የመሬት ይዞታ ምዝገባ ሥርዓት የተከናወነባቸው ከ330 ሺህ በላይ ቁራሽ መሬቶችና የጋራ መኖሪያ ቤቶች ናቸው። በዘንድሮ ሩብ ዓመት 53 ሺህ የመሬት ይዞታዎች ወደ ካዳስተር ሥርዓት መግባቱን ገልጸዋል።

በ2015 በጀት ዓመት ወደ ካዳስተር ሥርዓት የገባው 120 ሺህ የመሬት ይዞታዎች ሲሆኑ የ2016 በጀት ዓመት እቅዱ ደግሞ 120 ሺህ የመሬት ይዞታዎችን ወደ ዘመናዊ የካዳስተር ሥርዓት ለማስገባት እየተሠራ እንደሆነም ተናግረዋል።

በይዞታ ማረጋገጥ ሂደት ከሚያጋጥሙት ተግዳሮቶች ውስጥ የባለይዞታዎች ማመልከቻ አለመያዝ፣ አጎራባች አለመፈራረም፣ የባለይዞታዎች ግንዛቤ ማነስ ተጠቃሽ ናቸው ያሉት አቶ ግፋወሰን፤ በሚቀጥሉት ጥቂት ቀናት ሁሉም ክፍለ ከተማ የመረጃ ማሰባሰብና ማደራጀቱን ሥራ አጠናቀው ለይዞታ ማረጋገጥ እወጃ ዝግጁ እንደሚሆኑ ገልጸዋል።

ኤጀንሲው በ7ኛው ዙር የይዞታ ማረጋገጥ እወጃ ከ160ሺ በላይ ቁራሽ መሬቶችንና የጋራ መኖሪያ ቤቶችን አረጋግጦ በካዳስተር ሥርዓት ለመመዝገብ የዝግጅት ምዕራፍ ሥራዎችን በማጠናቀቅ ላይ መሆኑን ተናግረዋል።

# ባለሥልጣኑ የኢትዮጵያና የጂቡቲን የአየር...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን አስታወቀ። በቦሌ ዓለም አቀፍ አየር ማረፊያ በየዓመት 144 ሺህ የተለያዩ አውሮፕላኖች እንደሚያርፉና እንደሚነሱም ባለሥልጣኑ አስታውቀዋል፡፡

የተቋሙ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ መንግሥቱ ንጉሤ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ ባለሥልጣኑ የአየር ትራንስፖርት አገልግሎቱ አስተማማኝና ደህንነቱ የተጠበቀ እንዲሆን ሃላፊነቱን እየተወጣ ይገኛል።

ባለሥልጣኑ ያለምንም መቆራረጥ ሳምንቱን ሙሉ በየቀኑ 24 ሰዓት አገልግሎት እየሰጠ መሆኑን የጠቀሱት ም/ዋና ዳይሬክተሩ፤ ከኢትዮጵያ በተጨማሪ የጂቡቲን የአየር ክልል በመቆጣጠር የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት ደህንነቱ የተጠበቀ እንዲሆን እየሠራ ይገኛል ብለዋል።

በቦሌ ዓለም አቀፍ አየር ማረፊያ በየዓመት 144 ሺህ የተለያዩ አውሮፕላኖች እንደሚያርፉና እንደሚነሱ ጠቁመው፤ በተጨማሪም በዓመት የኢትዮጵያን የአየር ክልል አቋርጠው ወደተለያዩ ሀገራት የሚያልፉ ከ60 ሺህ በላይ አውሮፕላኖች መኖራቸውን ተናግረዋል።

በተጨማሪ በጂቡቲ የአየር ክልል ከ25 ሺህ ጫማ ከፍታ በላይ የሚበሩ አውሮፕላኖችን ደህንነት በማስጠበቅ ረገድ በጋራ እየተሠራ መሆኑን አመላክተዋል።

በኢትዮጵያና በጂቡቲ የአየር ክልል የሚንቀሳቀሱ አውሮፕላኖችም ሆኑ ሰው አልባ የአውሮፕላን በረራዎች የአየር ትራንስፖርት ደህንነት ከአደጋ ነፃ እንዲሆን እየተሠራ መሆኑን አስገንዝበዋል።

የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን የአየር ደህንነት ለማስጠበቅ የሚረዱ ዘመናዊ የቅኝት መሣሪያ ራዳሮች እንዳሉት የተናገሩት ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፤ የአውሮፕላኖችን ፍጥነት፣ የከፍታ ጫማ፣ አቅጣጫና አጠቃላይ የደህንነት እንቅስቃሴዎችን መሬት ላይ ሆኖ በመቆጣጠር እንደሚሠራ አስረድተዋል።

በድሬዳዋ፣ በጎዴ፣ በአርባምንጭና በተለያዩ አካባቢዎች የተተከሉ የራዳር መሣሪያዎች የአየር ትራንስፖርት ደህንነቱን በማስጠበቅ ረገድ ጉልህ ሚና እየተጫወቱ መሆኑንም ገልጸዋል።

ማንኛውም በቦሌ ዓለም አቀፍ አየር ማረፊያና በተለያዩ የሀገሪቷ አካባቢዎች የሚንቀሳቀስ አውሮፕላን ከባለሥልጣኑ የአየር ትራፊክ ተቆጣጣሪዎች በሚሰጠው መመሪያ መሠረት ደህንነቱ ተጠብቆ እንደሚበር አመላክተዋል።

በአየር ክልላችን ውስጥ እንዲበሩ ፈቃድ የተሰጣቸው አውሮፕላኖች ከበረራ ጋር በተያያዘ አስፈላጊ የሆኑ የኤሮኖቲካል መረጃዎችን በተለያዩ የግንኙነት አማራጮች ከባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ያገኛሉ ብለዋል።

አንድ የአውሮፕላን ፓይለት ቁልፍ ለማስነሳትም ሆነ አውሮፕላኑን ማንቀሳቀስ ሲፈልግ ለእያንዳንዱ ክንውኑ የአየር ትራፊክ ተቆጣጣሪዎች መመሪያ አስፈላጊ መሆኑን ጠቁመው፤ ከተለያዩ ዓለም አቀፍና የሀገር ውስጥ የአየር ትራንስፖርት ኩባንያዎች ጋር በቅንጅት እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል።

ባለሥልጣኑ ብሔራዊ የአየር ትራንስፖርት ደህንነትን ከማስጠበቅ አኳያ ከዓለም አቀፍ ተቋማት ዕውቅና ያለው ከአደጋ ነጻ የሆነ አገልግሎት እየተሰጠ መሆኑን አመላክተዋል።

ዘመኑ ያፈራቸውን ቴክኖሎጂዎች ከመጠቀም አኳያ በድጋፍና በተለያዩ አማራጮች የሚቀርቡ መሣሪያዎች እንዳሉ ገልጸው፤ በቅርቡ ከፈረንሳይ መንግሥት የተበረከተው የፀረ ድሮን ቴክኖሎጂ ጥቅም ላይ መዋሉን ተናግረዋል።

የተቋሙን አቅም ለማሳደግ በሚደረገው ጥረት ብሔራዊ የኤር ናቪጌሽን ዕቅድ እየተዘጋጀ መሆኑን አመላክተው፤ ዕቅዱ ኢትዮጵያ በአየር ትራፊክ ደህንነት ከራሷ አልፋ ለሌሎችም ሀገራት የምትተርፍበትን አቅም የሚገነባ መሆኑን ጠቁመዋል።

በአሁኑ ወቅትም የሶማሊያና የጂቡቲ ባለሙያዎችን በአየር ትራፊክ ቁጥጥር ዘርፍ በማሠልጠን በትብብር እየተሠራ መሆኑን አስታውቀዋል።

ባለሥልጣኑ የሚያከናውናቸው ሥራዎች የተለያዩ አየር መንገዶችን ቀልጣፋና ደህንነቱ የተጠበቀ የአየር ትራፊክ ቁጥጥር አገልግሎቶችን በማግኘት ውጤታማና ትርፋማ እንዲሆኑ እያገዘ መሆኑን አስረድተዋል።

ባለሥልጣኑ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ከተለያዩ አየር መንገዶች፣ ከኢትዮጵያ አየር ኃይልና የፀጥታ ተቋማት ጋር በአጋርነት እየሠራ መሆኑን ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ ሲቪል አቪየሽን ባለሥልጣን ደህንነቱ የተጠበቀ፣ አስተማማኝና ውጤታማ የኤር ናቪጌሽን አገልግሎት በመስጠቱ በ2015 ዓ.ም ብቻ ከ16 ሚሊዮን በላይ የሆኑ ተሳፋሪዎች በተለያዩ አየር መንገዶች ተጓጉዘዋል።

# ዓለም አቀፍ የቀዶ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ልውውጥ ለማድረግም መርሀ ግብሩ ትልቅ ጠቀሜታ ያለው ነው፡፡

በ14 የአፍሪካ ሀገራት መሥራት የሚያስችል የቀዶ ጥገና ህክምና የብቃት ማረጋገጫ ፈተናው በአፍሪካ ደረጃ ለ23ኛ ጊዜ በኢትዮጵያ ደግሞ ለሁለተኛ ጊዜ ትላንት የተሰጠ ሲሆን፤ ኢትዮጵያን ጨምሮ ከሰሃራ በታች ካሉ 14 የአፍሪካ ሀገራት የተውጣጡ ባለሙያዎች ፈተናውን ወስደዋል፡፡ በፈተናው ላይ የምስራቅ፣ የደቡብና መካከለኛው አፍሪካ የቀዶ ጥገና ሀኪሞች ተካተዋል። ፈተናው የጠቅላላ ቀዶ ጥገና፣ የፕላስቲክ ሰርጀሪ፣ የሽንት ቧንቧ፣ የአጥንትና የህጻናት ቀዶ ህክምና ዘርፍን የተመለከቱ መሆናቸውን ዶክተር ሽመልስ ተናግረዋል፡፡

የቀዶ ህክምና የብቃት ማረጋገጫ ፈተናው ከሰሃራ በታች ካሉ የአፍሪካ ሀገራት ማለትም፤ ከኢትዮጵያ፣ ኬንያ፣ ደቡብ ሱዳን፣ ሱዳን፣ ቦትስዋና፣ ቡሩንዲ፣ ማላዊ፣ ሞዛምቢክ፣ ናሚቢያ፣ ሩዋንዳ፣ ታንዛኒያ፣ ዩጋንዳ፣ ዛምቢያና ዚምባቡዌ የተውጣጡ ከ150 በላይ የህክምና ባለሙያዎች እየተሰጠ ሲሆን፣ ከሁሉም አህጉራት የተውጣጡ ከ300 በላይ የረጅም ጊዜ ልምድ ያላቸው የህክምና ባለሙያዎች ፈተናውን መስጠታቸውን አስታውቀዋል፡፡

እንደ ዶክተር ሽመልስ ገለጻ፤ ፈተናው በአፍሪካ ደረጃ ለ23ኛ ጊዜ በኢትዮጵያ ደግሞ ለሁለተኛ ጊዜ የተሰጠ ሲሆን፤ 80 በመቶ የሚሆኑ ተፈታኞች ኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች ናቸው። የቀዶ ጥገና ህክምና የብቃት ማረጋገጫ ፈተናውን የሚያልፉ ሀኪሞች በ14 የአፍሪካ ሀገራት ተዘዋውረው የመሥራት እድል የሚያገኙ ይሆናል።

ዝግጅቱ በኢትዮጵያ መካሄዱ የሀገር ገጽታን ለመገንባትና የሜዲካል ቱሪዝምን ለማነቃቃት ትልቅ ፋይዳ ያለው መሆኑን ዶክተር ሽመልስ ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ የቀዶ ህክምና ማህበር ፕሬዚዳንት አትክልት ባራኪ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ የፈተናው መዘጋጀት ይህክምና ባለሙያዎችን ብቃት ከማሻሻል ባለፈ እንደ ሀገር ለጤና አገልግሎቱ አሰጣጡ መሻሻል ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖረዋል ብለዋል።

በዕለቱ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት ፈተናው የተሰጠበትን የአለርት ሆስፒታልን የጎበኙ ሲሆን፤ ሆስፒታሉ ከሚሰጠው የህክምና አገልግሎት ባሻገር የልህቀት ማዕከል ለመሆን የሚያስችለውን መሠረተ ልማት በበቂ ለማሟላት ድጋፍ ሊደረግለት እንደሚገባ ጠቅሰዋል፡፡

በመርሀ ግበሩ አዲስ የተደራጁ የድንገተኛ አደጋና የጥርስ ህክምና ክፍል ጨምሮ በሆስፒታሉ ለታካሚ ምቹ የሆኑ የመሠረተ ልማት ሥራዎች ተጎብኝተዋል፡፡ ጉብኝቱ ለተቋሙ ሠራተኞች ተነሳሽነትን የሚፈጥርና በሚሰጡ ግብረ መልሶችም የማሻሻያ ርምጃዎችን ለመውሰድ እንደሚያስችል ዶክተር ሽመልስ ገልጸዋል፡፡

በጉብኝቱ የጤና ሚኒስትር ዶክተር ሊያ ታደሰ፣ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ምክትል አፈ ጉባዔ ሎሚ በዶና ሌሎች የምክር ቤት አባላት ተገኝተዋል።

# የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ጉብኝት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ተጋብዘው መገኘታቸውን አስታውሰው፤ አካታችና ዘላቂ የኢንዱስትሪ ልማትን ለማረጋገጥ በተካሄደው ውይይት መሳተፋቸውን ገልጸዋል፡፡

በጉባዔው የተለያዩ ኢኮኖሚያዊ ማሻሻያ በማድረግ ውጤታማ የሆኑ ሀገራት ልምድ ማቅረባቸውን ጠቁመው፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ኢትዮጵያ ባለፉት አምስት ዓመታት ኢኮኖሚያዊ ማሻሻያ አመርቂ ውጤት ማስመዝገቧንና ሀገራት ድጋፍ ማድረግ እንዳለባቸው መግለጻቸውን አስረድተዋል፡፡

ጉባዔው ኢትዮጵያ በአረንጓዴ ዐሻራ ፣ በምግብ ዋስትና፣ በሌማት ትሩፋትና በሌሎች መስኮች ያደረገቻቸውን በጎ ልምዶች ለዓለሙ ማህበረሰብ ያካፈለችበት መሆኑን ዶክተር ለገሰ ተናግረው፤ በተለይም ከተመድ የኢንዱስትሪ ልማት ድርጅት ዋና ዳይሬክተር ኢትዮጵያ አግሮ ኢንዱስትሪና ሌሎችን ለማስተሳሰር የምታደርገው ጥረት ለሌሎች ሀገራት ልዩ ተሞክሮ ሊሆን እንደሚችል አድናቆት ተችሮታል ብለዋል፡፡

የበለጸጉ ሀገራት እንደ ኢትዮጵያ ስኬታማ ሥራዎችን በመሥራት ላይ ለሚገኙ ሀገራት ድጋፋቸውን አጠናክረው መቀጠል እንዳለባቸው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ማሳወቃቸውንና ኢትዮጵያ የአረንጓዴ ዐሻራ ስኬትና ሂደት የምታሳይበት ኤክስፖ መክፈታቸውን ዶክተር ለገሰ ገልጸዋል፡፡

በተጨማሪም ከዓለም አቀፍ ጉባዔዎች ጎን ለጎን ከተለያዩ ሀገራት መሪዎችና የዓለም አቀፍ ተቋማት መሪዎች ጋር የሁለትዮሽ ግንኙነት አካሂደዋል ያሉት ሚኒስትሩ፤ በተለይም አጋርነት የማስፋት፣ የፋይናንስ ኢንቨስትመንት ላይ በመምከር አወንታዊ የሆኑ ምላሾች የተገኙበት ነው ብለዋል፡፡

በሌላ በኩል ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በቼክ ሪፐብሊክ በነበራቸው ይፋዊ ጉብኝት በተለይም በግብርና መካናይዜሽን፣ በኢንዱስትሪ፣ ለአየር ኃይል የአቅም ግንባታ ላይ ከሚሠሩ ተቋማትና ፣ ከባለሀብቶች ጋር መወያየታቸውን ገልጸዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ የፕሬስ ሴክሬታሪ ኃላፊ ቢለኔ ስዩም በበኩላቸው ፤ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በቼክ ሪፐብሊክ በነበራቸው ጉብኝት በተለይም በቱሪዝምና በግብርናው ዘርፍ በጋራ ለመሥራት፣ በመከላከያ የአቅም ግንባታና የልምድ ልውውጥ፣ አየር ኃይልን ለማጠናከር አብሮ ለመሥራት ውይይት ማድረጋቸውን አመላክተዋል።

በተባበሩት ዓረብ ኢምሬትስ በተዘጋጀው የተመድ የአየር ንብረት ለውጥ ጉባዔ ላይ ደግሞ ኢትዮጵያ የመካነ ርዕይ ማዘጋጀቷን በመግለጽ፤ የአረንጓዴ ዐሻራ ስኬቶችን፣ የግብርና፣ የምግብ ዋስት፣ ታዳሽ ኃይል ሥራዎችን ለመሪዎች ማቅረባቸውን ተናግረዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በኮፕ 28 ላይ ያቀረቡት ሃሳብ ተግባር ላይ ያተኮረ መሆኑን ጠቅሰው፤ የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል በርካታ ጥረቶች ይደረጋሉ ማለታቸውን ገልጸዋል፡፡

የኢትዮጵያ አረንጓዴ ዐሻራ ተሞክሮ በሌሎች ሀገራት ላይ ተነሳሽነትን የፈጠረ መሆኑን ጠቅሰው፤ የኢትዮጵያን የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር በመከተል የተለያዩ ሀገራት የዛፍ ተከላ ኢኒሼቲቮችን ማስጀመራቸውን አንስተዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በተባበሩት አረብ ኤምሬትስ በነበራቸው ቆይታ የተለያዩ የሁለትዮሽ ውይይቶች ማካሄዳቸውን ጠቁመው፤ በተለይም ከቤልጂየም ጠቅላይ ሚኒስትር ፣ ቀጣናዊ አህጉራዊና በሁለትዮሽ ጉዳዮች ላይ መወያየታቸውን ተናግረዋል።

በተጨማሪም ከኩባ ፕሬዚዳንት በትምህርት በጤና በቱሪዝም ላይ በጋራ ለመሥራት መወያየታቸውንና ከተለያዩ ሀገራት መሪዎችና የዓለምአቀፍ ተቋማት መሪዎች ጋር ተገናኝተው በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ውጤታማ ምክክር ማድረጋቸውን አስታውቀዋል።

# ትግበራ የናፈቀው"ቅድሚያ ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

እንደ ሀገር በየዓመቱ የሚጠናቀረው ሪፖርት የአደጋውን ስፋት አያሳይም ነው የሚሉት።

አቶ ደምስ እንደሚያስረዱት በሥራ አካባቢ በአካል ላይ ከሚደርሰው ጉዳት በተጨማሪ በጤና ላይ የሚደርስ ጉዳት አለ። ይህም ከነጭራሹ ቁጥጥር የሚደረግበት ሥርዓት ስላልተበጀለት ከሙያ ደህንነት ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ሲነሱ ትኩረት የሚደረገው አደጋ ላይ ብቻ ነው። ምቹ የሥራ አካባቢ ያልፈጠሩ ተቋማት ተጠያቂ ሲሆኑ አይታይም፤ ይህም ችግሩ እንዳይቀንስ አድርጎታል።

“ሕይወት ማጣትና ከሕይወት ማጣት ያልተናነሱ ጉዳቶች ሲደርሱ የሚሰጠው የጉዳት ካሳ የአምስት ዓመት ደሞዝ ነው” የሚሉት ባለሙያው፣ አብዛኛው ሠራተኛ ደሞዙ አነስተኛ ስለሆነ ሕይወቱን ላጣ ሰው የሚሰጠው ካሳ እጅግ አነስተኛ መሆኑን በመግለጽ የሚሰጠው ካሳ ለስሙ መመጠን አለበት ይላሉ።

የአዲስ አበባ እሳትና አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን የሕዝብ ግንኙነት ባለሙያ አቶ ንጋቱ ማሞ መሥሪያቤታቸው አደጋ ሲደርስ ከሚሰጠው ምላሽ ባሻገር በአደጋ ቅነሳ ሥራ ባደረገው ቅኝት በመዲናዋ የሚካሄዱ አብዛኞቹ ግንባታዎች የሥራ ላይ ደህንነት መርሆችን ጠብቀው የሚሠሩ አለመሆናቸውን መገምገሙን ይገልጻሉ።

“እኛ የምንጠራው የሞት አደጋ ሲሆን ወይም ተጎጂዎችን አፈርና ድንጋይ ተጭኗቸው አስክሬናቸውን ማንሳት የማይችሉበት ሁኔታ ሲፈጠር ነው” የሚሉት የሕዝብ ግንኙነት ባለሙያው፤ “ብዙ ጊዜ በተለይም ከሞት አደጋ በመለስ ያለን ጉዳት አሰሪዎች ይደብቃሉ። አደጋ ሲከሰት በአሰሪዎች ላይ የሚጣለው ቅጣት አነስተኛ መሆኑ ለጉዳዩ ትኩረት እንዳይሰጡት አድርጓል” ባይ ናቸው።

በየካቲት 12 ሆስፒታል ሜዲካል ኮሌጅ የፕላስቲክና ሪኮርስትራክቲክ ሰርጅኑ ዶክተር መኮንን እሸቴ በፋብሪካዎችና ግንባታዎች ውስጥ ለሚሰሩ ሠራተኞች ደህንነቱ የተጠበቀ የሥራ አካባቢ በመፍጠር ረገድ ባሉ ክፍተቶች ብዙ ወጣቶች ለቃጠሎ እየተጋለጡ ነው። በግንባታ ቦታዎች ላይ ብረት ተሸክመው ሲንቀሳቀሱ ብረቱ ከፍተኛ ኃይል ተሸካሚ የኤሌክትሪክ ገመድ እየነካ ለቃጠሎ የተዳረጉ ወጣቶች ቁጥር በርክቷል ይላሉ።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ አርክቴክቸር ኢንስቲትዩት የኮንስትራክሽን ቴክኖሎጂና ማኔጅመንት ክፍል መምህሩ ረዳት ፕሮፌሰር ይሄነው ብርሃኔ ተገቢው ትኩረት ቢሰጥና ጥንቃቄ ቢደረግ የሥራ ላይ አደጋዎችን መቀነስና መቅረፍ እንደሚቻል ይናገራሉ።

ለደህንነት የሚያስፈልገው በጀት ከአጠቃላይ የፕሮጀክቶች በጀት አንጻር እጅግ በጣም ትንሽ ስለሆነ በየትኛውም ደረጃ ያለ ኮንትራክተር ሊያሟላ የሚችለው ቀላል ነገር መሆኑን የጠቆሙት ረዳት ፕሮፌሰሩ፤ ነገር ግን ይህን ባለማድረግ የሰው አካል እንደሚጎድልና ሕይወትም እንደሚጠፋ ይገልጻሉ።

መፍትሔ ነው የሚሉትን ሃሳብ ሲያመላክቱም፤ ድርጅቶች አነስተኛም ቢሆን ወጪ የሚያስወጣን ነገር በግል ተነሳሽነት ያደርጋሉ ብሎ መጠበቅ የዋህነት ስለሚሆን በጥብቅ የሚተገበር አስገዳጅ የሆነ የሕግ ማዕቀፍ ያስፈልጋል። በሥራ ቦታዎች ላይ ራሱን የቻለ የደህንነት ተቆጣጣሪ መኖር አለበት። በተጨማሪም እዚሁ እኛ ሀገር በግንባታ ላይ ከተሰማሩ የውጭ ሀገር ኮንትራክተሮች መማር እንችላለን። የመጀመሪያ ርዳታ መስጠት የሚያስችል ክሊኒክና ቋሚ የጤና ባለሙያ ሁሉ አላቸው ብለዋል።

በሥራና ክህሎት ሚኒስቴር የሙያ ደህንነትና ጤንነት ዴስክ ኃላፊ ጥዑመእዝጊ በርሄ እንደሚናገሩት ለሥራ ላይ ደህንነትና ጤንነት አሠሪውም ሆነ ሠራተኛው የሚሰጡት ትኩረት በጣም አናሳ ነው። ብዙ አሠሪዎች የሥራ አካባቢን ደህንነትና ጤንነት መጠበቅ ተጨማሪ ወጪ ያስወጣል እንጂ ይበልጥ ትርፋማ ያደርጋል ብለው አያስቡም።

እንደ ሀገር በተለያየ ቦታ ላይ የሚገኙ አብዛኞቹ አመራሮችና ባለሀብቶች ለደህንነት የሚሰጡት ትኩረት አናሳ ነው ያሉት ኃላፊው፣ በሀገራችን “ቅድሚያ ለደህንነት” የሚለው መርህ ገና አለማደጉን ገልጸዋል።

አክለውም፤ በሀገር ደረጃ ያለን የሥራ ላይ ድህንነት ተቆጣጣሪ የሰው ኃይል ከ500 የማይበልጥ ነው። ይህ አነስተኛ ቁጥር ያለው የቁጥጥር ባለሙያም የአቅም ውስንነት ያለበት ነው። የሥራ ላይ ደህንነትን ለመጠበቅ የሚያስፈልጉ ቴክኖሎጂዎች እጥረትም አለ ብለዋል።

አቶ ጥዑመእዝጊ መሥሪያ ቤታቸው አጠቃላይ የሙያ ደህንነትና ጤንነት ለመጠበቅ አዲስ አሠራር እየዘረጋ መሆኑን ጠቁመው፤ ከ12 ሚኒስትር መሥሪያ ቤቶች ጋር የጎንዮሽ የመግባቢያ ስምምነት ተፈራርመናል። በቁጥጥር ረገድ ያለውን የሠለጠና የሰው ኃይል እጥረት ለመቅረፍ በዚህ ዓመት በቢኤ ዲግሪ ለተመረቁ ለ1000 ተማሪዎች ሥልጠና ለመስጠት ዝግጅቶች ተጠናቀዋል ብለዋል።

በተጨማሪም በተወሰ ጊዜ እየተገናኘ ስለ ሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት የሚወያይና የደረሱ አደጋዎችን በዝርዝር ገምግሞ ሪፖርት የሚያደርግ “የሥራ አካባቢ የሥራ አመራር ኮሚቴ” የሚባል መዋቅር ከአሰሪውና ከሠራተኛው በተውጣጡ አባላት በእያንዳንዱ የሥራ ቦታ ላይ ለማቋቋም እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል።

ዓለም አቀፉ የላብ አደሮች ድርጅት ከሥራ ጋር በተያያዙ አደጋዎችና በሽታዎች በየአመቱ ይሞታሉ ካላቸው ሦስት ሚሊዮን የሚጠጉ ሰዎች ውስጥ 2.6 ሚሊዮኑ በሥራ ላይ አደጋ፤ 330,000 ያህሉ ደግሞ ከሥራ ጋር በተያያዙ በሽታዎች ሕይወታቸውን የሚያጡ ናቸው። 395 ሚሊዮን ሠራተኞች ደግሞ ለሞት የማይዳርግ የሥራ ላይ ጉዳት ይደርስባቸዋል።

ድርጅቱ የሠራተኞች ደህንነትን ማስቀደም ግቡ ያደረገ “ዓለም አቀፍ የሥራ ደህንነትና ጤና ስትራቴጂ ለ2024-2030” የተባለ አዲስ እቅድ በማስተዋወቅ ሀገራት ለሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤና ትኩረት እንዲሰጡ ጥሪ አቅርቧል።

በሀገራችንም የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር እየዘረጋ ያለው አሠራር በተደጋጋሚ የሚነገረውን መርህ በተግባር ለመተርጎም የማያስችል ከሆነ ግን ክቡር የሆነው የሰው ልጅ ሕይወት መቀጠፉ ነገም የሚቀጥል እንደሆነ ባለሙያዎቹ ይናገራሉ።

# ርዕሰ አንቀፅ

## በችግር ውስጥ የሚገኙ ወገኖቻችንን መታደግ የሁሉም ዜጋ ኃላፊነት ነው!

በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በተከሰቱ የሰላም እጦቶች፤ ድርቅና ጎርፍ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች ለችግር ተጋልጠዋል። ይህንንም ተከትሎ መንግሥት በራሱ አቅም ለተጎጂ ወገኖቻችን ድጋፍ በማቅረብ፤ ችግሩ የከፋ ጉዳት እንዳያስከትል በኃላፊነት መንፈስ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል።

የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ሰሞኑን እንዳስታወቀው፤ በሀገሪቱ በጎርፍ፣ በግጭትና በድርቅ ለተጎዱ 7 ነጥብ 3 ሚሊዮን ዜጎች ከሁለት ሳምንት በፊት በሁለት ዙር 7 ነጥብ 9 ቢሊዮን ብር ወጪ በማድረግ የርዳታ አቅርቦቶችን አከፋፍሏል፡፡

ርዳታው የቅድሚያ ቅድሚያ ለሚያስፈልጋቸው ፤ በሰሜን ጎንደር፣ በዋግኽምራና በትግራይ ክልል ለሚገኙ ሦስት ዞኖች ተከፋፍሏል፤ ርዳታው ለ3 ነጥብ 6 ሚሊዮን ለሚሆኑት ተጎጂዎች በገንዘብ ፤ለተቀሩት ደግሞ በምግብ ነክ ድጋፎች ተሰራጭቷል፡፡

በሶማሊያ ክልል ሰሞኑን የተከሰተውን ጎርፍ ተከትሎም፤ ለአደጋው ተጎጂዎች አንድ ሺህ 821 ኩንታል የስንዴ ዱቄትና ሩዝ፤ 9 ሺህ 200 ኪት ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች በመንግሥት በኩል ድጋፍ ተደርጓል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ደቡብ ኦሞ ዞን ዳሰነች ወረዳ ባጋጠመ የጎርፍ አደጋ ለተፈናቀሉ 16 ሺህ 648 አባ ወራዎችና እማ ወራዎች 3 ሺህ 140 ልዩ ልዩ ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች በመንግሥት ወደ አካባቢው ተልከዋል፡፡

ከመከላከያ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ሄሊኮፕተር በመታገዝ የሰዎችን ሕይወት የማዳን፣ የምግብ ቁሳቁሶችን፣ መድኃኒት፣ አጎበርና የውሃ ማጣሪያ ኬሚካል የማሰራጨት ሥራዎችም እየተሠሩ ነው፡፡

መንግሥት ካለበት፤በየትኛውም ሁኔታ ሊከሰቱ ከሚችሉ አደጋዎች የዜጎች ህይወት የመታደግ ኃላፊነት አንጻር በሰላም እጦት፤ በድርቅና በጎርፍ አደጋዎች ችግር ውስጥ የሚገኙ ዜጎቻችንን ሕይወት ለመታደግ እያደረገ ያለው ጥረት እውቅና ሊሰጠው የሚገባ ነው።

ችግሩን በወቅቱ ከማሳወቅ ጀምሮ፤ ባለው አቅም በችግሮቹ ምክንያት አንድም ዜጋ መሞት አይገባውም በሚል ያለውን ሀገራዊ አቅም በማቀናጀት፤ ዜጎችን ለመታደግ እየሄደበት ያለው ርቀት ለዜጎች ህይወት ያለውን ከበሬታ በተጨባጭ የሚያመላክት ነው።

ዓለም አቀፍ የእርዳታ ሰጪ ድርጅቶች ለችግሩ ተገቢውን ትኩረት እንዲሰጡ ከማድረግ ጀምሮ፤የተገኙ የእርዳታ አቅርቦቶች የችግሮቹን አሳሳቢነት ታሳቢ ባደረገ መንገድ ለተጎጂዎች እንዲከፋፈል እያደረገ ያለውም ጥረት የሚበረታታ ነው።

በተለይም የመከላከያ ኃይሉ ያለውን ሙያዊ አቅም ጨምሮ፤ የእርዳታ አቅርቦቶች እና አስፈላጊ ቁሳቁሶችን ለተጎጂ ወገኖቻችን በወቅቱ እንዲደርስ ማድረጉ፤ሀገራዊ አቅሞችን በማቀናጀት ችግር ውስጥ ላሉ ዜጎቻችን ፈጥኖ ለመድረስ ያስቻለ ነው። የመከላከያ ሠራዊቱን ሕዝባዊነትም በተጨባጭ ያመላከተ ነው።

ይህም ሆኖ ግን፤ ከችግሮቹ ስፋትና፤ አሁን ላይ እንደሀገር ካሉብን መልከ ብዙ ተግዳሮቶች አንጻር፤ በችግር ውስጥ ያሉ ዜጎቻችንን የመታደግ ኃላፊነት ለመንግሥት ብቻ የሚተው ሳይሆን፤ የእያንዳንዱን ዜጋ ድጋፍ የሚሻ፤ ሀገራዊ ንቅናቄ መፍጠርን የሚጠይቅ ነው።

ለዚህ ደግሞ ከሁሉም በላይ ባለሀብቶቻችን በችግር ውስጥ ያሉ ዜጎችን ህይወት በመታደግ ሂደት ኃላፊነት እንደሚሰማው ዜጋ የሚቻላቸውን ሁሉ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል ፤ችግሩ በዜጎች ላይ የከፋ ጉዳት ከማስከተሉ በፊት ፈጥነው በመንቀሳቀስ በአደጋ ውስጥ ለሚገኙ ዜጎቻችን ያላቸውን አጋርነት በተግባር ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል።

ጉዳዩ ከሰብአዊነት ጋር የተቆራኘ በመሆኑ፤ በውጪ የሚኖሩ ኢትዮጵያውን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ችግሩን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር በሚደረገው ጥረት ውስጥ የራሳቸውን አስተዋጽኦ በማበርከት፤ ለሀገራቸውና ለሕዝባቸው ያላቸውን ፍቅር፤ እንዲሁም ለሰብአዊነት ያላቸውን ከበሬታ በተጨባጭ ማሳየት ይጠበቅባቸዋል! ለዚህም ከዚህ ቀደም ወገኖች በችግር ውስጥ በሚሆኑበት ጊዜ ዜጎች በራሳቸው ተነሳሽነት ያደርጉ የነበረውን ዓይነት ድጋፍ አሁንም ለመደገም ዝግጁ መሆን ይገባቸዋል፡፡

**አዲስ ዘመን**
ኢፕድ
ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፦ epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፦ 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## አብሮን ዘመናት እየተሻገረ ያለ የምርት ብክነት

**ሚሊዮን ሺበሺ**

ለዋጋ ግሽበት ምክንያት ናቸው ከሚባሉ ነገሮች አንዱ የምርት ብክነት ነው፡፡ የምርት ብክነት ማለት ሊገኝ ከሚገባው ምርት ውስጥ በአያያዝና አሰባሰብ ችግር ምክንያት መጠኑ ሲቀንስ ማለት ነው፡፡ ሊገኝ የሚገባው የምርት መጠን ቀነሰ ማለት የምርት ቅናሽ ተከሰተ ማለት ነው፡፡ የምርት መቀነስ ደግሞ የዋጋ ግሽበትን ያመጣል፡፡

የዋጋ ግሽበት የሚባለው በተወሰነ የጊዜ መጠን ውስጥ የምርት እና አገልግሎቶች ዋጋ መጨመር ማለት ነው፡፡ በሚፈለገው ልክ ማቅረብ አለመቻል ማለት ነው፡፡ እነዚህ ነገሮች ሲከሰቱ ‹‹የኑሮ ውድነት›› ይባላል ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም ምንም የተውሰበሰበ የምጣኔ ሀብት ትንተና ሳያስፈልገው፤ የአንድ ምርት ወይም አገልግሎት ዋጋ ከፍተኛ ይሆናል ማለት ነው፡፡

ምንም እንኳን አሁን በሀገራችን (በተለይም በከተሞች) የሚታየው የኑሮ ውድነት ምክንያቱ የምርት ብክነት ብቻ ነው ባይባልም ቢያንስ ግን አንዱ ምክንያት ነው፡፡ አሁን ወቅቱ በብዙ የኢትዮጵያ አካባቢዎች (በተለይም በማዕከላዊና ሰሜን ኢትዮጵያ አካባቢዎች) የመኸር ወቅት ነው፡፡

የኅዳር ወር በከፍተኛ ትጋት ሰብል የሚሰበሰብበት ወር ነው፡፡ በዚህ ወቅት ታዲያ ከፍተኛ የሆነ የምርት ብክነት ያጋጥማል፡፡ የምርት ብክነቱ የሚያጋጥምባቸውን ምክንያቶች ከመጥቀሴ በፊት ግን አንድ ገጠመኝ ላስታውስ፡፡

በ2010 ዓ.ም ይመስለኛል፡፡ በወቅቱ ስያሜው የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር ወደ ቆቃ አካባቢ የፍራፍሬ ምርቶችን ለማስጎብኘት ወስዶን ነበር። በወቅቱ ባለሙያዎች ከነገሩን ነገር አንዱ ከፍተኛ የሆነ የምርት ብክነት እንደሚያጋጥም ነው፡፡ በአያያዝ ምክንያት በተለይም እንደ ቲማቲም፣ ማንጎና አቮካዶ የመሳሰሉ ምርቶች በተፈላጊው የምርት ጥራት አይላኩም፡፡ የመለየት ሥራው አስቸጋሪ ነበር፡፡

የሰብል ምርት የሆኑትን የግብርና ምርቶች ስናስተውል ደግሞ የበለጠ ከፍተኛ ብክነት ይታይባቸዋል፡፡ የ2ኛ ደረጃ ትምህርት እስከማጠናቅቅበት ጊዜ ድረስ ከግብርና ሥራዎች አልራቅኩም፤ እኔ ንቁ የግብርና ተሳታፊ ባልሆን እንኳን ቤተሰብን በማግዝበት ሰዓት በትንሹ፤ ከዚያ ውጪ ደግሞ በአካባቢያችን የሚከናወኑ የግብርና ምርት አሰባሰብ ሂደቶችን በማየት ከፍተኛ ብክነት እንደሚፈጸም አስተውያለሁ፡፡

በብዙ አካባቢዎች የግብርና ምርቶች የሚሰበሰቡት በልማዳዊ መንገድ ነው፡፡ ለምሳሌ፤ ጤፍ የሚታጨደው በእጅ (በማጭድ) ነው። የጤፉን አገዳ ይዘው ጭንቅላቱ እየተወዛወዘ ችቧቸው እስከሚሞላ ያጭዳሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ የጤፉ ፍሬዎች ይወድቃሉ፡፡ የጤፍ ፍሬ በጣም ትንንሽ ከመሆናቸው የተነሳ መሬት ላይ አይታዩም። እንደሚባክን ግን ያውቃሉ፡፡ ቃሉን በጋዜጣ ለመጠቀም ባይመችም ጤፍ ሳይታወቅበት የሚባክን ምርት መሆኑን የሚገልጽ አባባልም አላቸው፡፡

እያጨዱ ችቧቸው ሲሞላ ከኋላ የታጨደው ላይ እያስቀመጡ ነው ወደፊት የሚሄዱት፡፡ ያ ማሳ ላይ በትንሽ በትንሹ (በችቦ ልክ) የተቀመጠ ጤፍ እንደገና ከፍ ወዳለ ስብስብ ይሰበሰባል፤ አሁንም እየፈሰሰ ነው፡፡ ከዚያ በኋላ አሁንም ተሰብስቦ ክምር ይደረጋል፤ አሁንም እየፈሰሰ ነው። ማሳ ላይ የተከመረው ክምር ደግሞ ሰፈር አካባቢ ወደሚገኘው አውድማ በሸክም ይወሰዳል፤ አሁንም እየፈሰሰ ነው።

አውድማው ጤፍ ለማበራየት በሚያስችል ሁኔታ ተደርጎ ይዘጋጃል፡፡ የሚበራየውም በበሬ ነው፡ ፡ በሬ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ የጤፍ ፍሬዎች ከአገዳውና ከሙሉ ገለባው ተላቀው በኩንታል ውስጥ እስከሚታዩ ድረስ ያለው ሂደት ከ24 ሰዓት በላይ የሚወስድ ሥራ ስለሆነ ዘርዝረን አንጨርሰውም፤ በዚህ ሁሉ ሂደት ውስጥ የጤፍ ፍሬዎች ይባክናሉ። ምንም እንኳን ሳይንሳዊ የተጠና ነገር ባይኖረውም ገበሬዎች በልማድ እንደሚናገሩት የሚባክነው ምርት ወደ ጎተራ ከሚገባው አይተናነስም፡፡

ለዚህ ደግሞ አንድ ማሳያ አለ፡፡ ‹‹ምርትና ግርድ›› የሚሉት፡፡ ምርት ማለት በትክክል የተጣራው ሲሆን ግርድ ደግሞ የተራረፈው ማለት ነው፡፡ በምርትና በግርዱ መካከል የጤፍ ፍሬዎች ልዩነት የላቸውም፤ ልዩነቱ ግርዱ ከገለባው ጋር ያለው መሆኑ ነው፡፡ ከአቅም በላይ ሆኖ ያመለጠው ማለት ነው፡፡ ይህ አውድማ ላይ ብቻ የሚባክነው ነው፡፡

እንደ ማሽላ እና ጥራጥሬ ያሉ የሰብል አይነቶች ከተሰበሰቡ በኋላ ልጆች ‹‹ቃርሚያ›› በሚል ማሳ ውስጥ ይሄዳሉ፡፡ በምርት አሰባሰብ ሂደት ውስጥ ከቁጥቋጦ ውስጥ፣ ከእርከን ሥር፣ ከቦይ አካባቢ የተራረፉትን ለመሰብሰብ ማለት ነው፡፡ እንደማሳው መልከዓ ምድራዊ አቀማመጥ ሁኔታ ልጆች ብዙ ምርት ያገኛሉ፡፡

ያንን ያገኙትን ምርት ቤተሰብም ሆነ የማሳው ባለቤት አይጠይቃቸውም፡፡ ሸጠው ብሩ ለራሳቸው ነው፡፡ ልጆች እንደዚያ ካላደረጉ ደግሞ የወዳደቀው (የባከነው) ሰብል የአራዊት ይሆናል ማለት ነው፡፡

ከማሳ እስከ ጎተራ ባለው ሂደት ውስጥ ይህ ሁሉ ብክነት ያጋጠመው አሰራራችን ዛሬም ያው ነው፡፡ በኮምባይነር ምርት የሚሰበስቡ አካባቢዎች እጅግ በጣም ጥቂት ናቸው ፤ ጥቂት መሆናቸው ብቻ ሳይሆን የኮምባይነር አገልግሎት የሚያገኙት አብዛኞቹ ኩታ ገጠም አካባቢዎች እና የስንዴ ማሳዎች ናቸው ፡፡ በኢትዮጵያ በሰፊው ለምግብነት የሚውለው የጤፍ ምርት በዘመናዊ መንገድ መሰብሰብ አለመቻሉ /ብዙ ብክነት ማስተናገዱ ምን ማለት እንደሆነ ለመገመት አይከብድም፡፡

የምርት ብክነት የሚያጋጥመው በእነዚህ የአገዳ እህሎች ላይ ብቻ አይደለም፡፡ በአትክልትና ፍራፍሬ ጭምር ነው ፤እንዲያውም ችግሩ የከፋ ሳይሆን አይቀርም፡፡ በተለይ እንደ ቲማቲም ያሉ ፍራፍሬዎች በቀላሉ የሚበላሹ ስለሆኑ በከፍተኛ ሁኔታ ይባክናሉ። የሚባክኑት በአያያዝና አሰባሰብ ችግር ነው፡፡ ይህ ደግሞ ለባለቤቱ ብቻ ሳይሆን እንደ ሀገርም ኪሳራ እየሆነ ነው ፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ ‹‹የምርት እጥረት አለ›› ብሎ መናገር አሳፋሪ መሆን አለበት፡፡ ምክንያቱም በየትኛውም አካባቢ ቢሄዱ ቢያንስ ከአንዱ አካባቢ ያለው ሌላ አካባቢ ላይኖር ይችላል እንጂ በሁሉም ቦታዎች የምርት አይነቶች አሉ። ዳሩ ግን የግንዛቤ እጥረት አለ፡፡ የግንዛቤ እጥረት ነው የምርት እጥረት ያመጣብን፡፡

አፈሩ እጅግ ብዙ ምርቶችን ያፈራል፤ ዳሩ ግን ወደ ተጠቃሚ የሚደርሰው ከግማሽ በታች የሚሆነው ሊሆን ይችላል፡፡ የተቀረው እዚያው ባክኖ ይቀራል፡፡ በዚህ ምክንያት ባለ ምርቱ ሸጦ ሊያገኘው የሚገባውን ገንዘብ ሳያገኝ ይቀራል ነው፤ ሸማቹ የኅብረተሰብ ክፍል ተፈላጊውን ጥራት ብቻ ሳይሆን ያንኑም ጥራቱን ያልጠበቀውን ሳይዳረስ ይቀራል ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ የአቅርቦትና ፍላጎት አለመጣጣም ይመጣል፤ ይህ ደግሞ የዋጋ ግሽበት፤ ቀጥሎም የኑሮ ውድነት ያስከትላል ማለት ነው፡፡

ስለዚህ የምርት እጥረት እንዳያጋጥም የግንዛቤ እጥረትን እናስተካክል! ለዚህ ደግሞ የዘርፉ ባለሙያዎች ወደ አምራቹ የኅብረተሰብ ክፍል በመጠጋት በችግሩ ዙሪያ ያለውን እውነታ ሊያሳውቁት እና ሊያስተምሩት የተሻሉ መፍትሔዎችን አብረውት ሊያፈላልጉ ያስፈልጋል፣ መንግሥትም ለዚህ የሚሆኑ ሁኔታዎች ሊያመቻች፤ አስፈላጊ ግብዓቶችን ሊያቀርብ ይገባል!

# ነፃ ሃሳብ

# ዘርፉን ከመንግሥት ጀርባ ለማውረድና ኢኮኖሚያዊ ጥቅሙን ለማጎልበት

**ታምራት ተስፋዬ**

ስፖርት በተለይ በአሁኑ ወቅት ለስሜት አሊያም በማዝናናት ብቻ አይወሰንም። ጤናማና አምራችና ትውልድ ከማፍራት በተጓዳኝ በርካታ የኅብረተሰብ ክፍልን በቀጥታና ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ ተጠቃሚ ያደርጋል። በርካታ ቢሊዮን ዶላር የሚንቀሳቀስበት ግዙፍ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ሆኖም የሀገራት ዋነኛ የኢኮኖሚ ምንጭና የምጣኔ ሀብት እድገታቸው መዘውር ሆኗል።

የተለያዩ ስፖርቶች በፍቅር ከሚወደዱባቸው ሀገራት መካከል ኢትዮጵያ አንዷ ናት፡፡ በሀገሪቱ ዘመናዊ የስፖርት ውድድሮች መካሄድ ከጀመሩ አንድ ክፍለ ዘመን ሊሞላቸው ተቃርቧል። ይሁንና እነዚህን ሁሉ ዓመታት መመልከት ሳያስፈልገን የቅርቦቹን አስርና አስራ አምስት ዓመታት እንኳን ብንቃኝ የስፖርት ዘርፍ በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ፈሰስ ይደረግለታል።

በመንግሥት ወጪ በርካታ የስፖርት መሰረተ ልማት አውታሮች እየተስፋፉ በተለይ የውድድር ማከናወኛ ግዙፍና ዘመናዊ ስታዲየሞች ተገንብተዋል። የአንዳንዶቹ ግንባታም ቀጥሏል። ከስቴዲየም ግንባታ በተጓዳኝ በተለያዩ ከተሞች የወጣት ስፖርት አካዳሚዎች ተከፍተዋል።

ይህ የሀገሪቱ መንግሥት ስፖርቱን የማጎልበት ዓላማና ሚና መሰረተ ልማቶችን በማስፋፋት ብቻ ተወስኖ የሚቆም ግን አይደለም። በሀገሪቱ የሚገኙ ፌዴሬሽኖች መካከል ከ90 በመቶ በላይ የሚሆኑት በራሳቸው ገቢ መፍጠርና ማምጣት የማይችሉና ከዓመት ዓመት የሥራ ማስኬጃ ድጎማ ለመጠየቅ የመንግሥት በር ከማንኳካት ያልቦዘኑ ናቸው። ይህ እንደመሆኑም የሀገሪቱ መንግሥት በየዓመቱ በሩን ለሚያንኳኩ ፌዴሬሽኖች እጁን አያጥፈም።

ከፌዴሬሽኖች በተጓዳኝ በመንግሥት ተቋማት አሊያም ልማት ድርጅቶች ስር የሚገኙ ክለቦችም በየዓመቱ የዚሁ ድጎማ ተቋዳሽ ናቸው።የራሳቸውን ገቢ በራሳቸው መሸፈን እንኳን ያልሆነላቸው አንዳንድ የመንግሥት ጥገኛ ክለቦች በአንፃሩ ለአንድ ተጫዋቾች በሚሊዮን የሚቆጠር የፊርማና የወር ደሞዝ ይከፍላሉ። ከሀገር ውስጥ አልፈው ከውጭ ተጫዋቾች ያስመጣሉ።ከዓመት ከዓመት ከቀበሌ ጀምሮ የሚደረጉ ስፖርታዊ ውድድሮች ለማከናወን፣ ለስልጠና ለምልመላ፣ የስፖርት ትጥቆችን ለመግዛት እንዲሁም ለተዋናዮቹ የሚሆን አበል እየተባለ ረብጣ ገንዘብ ፈሰስ ይደረጋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ማንኛውንም ሀገር ከዓለም አቀፍ የስፖርት የሀብት ምንጭ ተጠቃሚ ከሚያደርጉ መንገዶች አንዱና ዋነኛው የስፖርት ኢንቨስትመንት መሆኑ ይታወቃል። የኢትዮጵያን የስፖርት ዘርፍ በዚህ መነፅር ከተመለከትነው ግን እንደ አንድ ኢኮኖሚና ኢንቨስትመንት ሆኖ አናየውም።

ዘርፉ «አክሳሪ አሊያም አትራፊ ነው» የሚለው በቅጡ አይታወቅም። ዘርፉ በሀገሪቱ አጠቃላይ ኢኮኖሚ ውስጥ ያለው ድርሻ ምን ያህል እንደሆነና ለኢንቨስትመንት ያለውን አመቺነት ለመረዳት በዚህ ረገድ የተጠኑ ጥናቶችን መኖር አለመኖራቸውን ማረጋገጥም እጅጉን ከባድ ነው፡፡

ዘርፉ በሀገሪቱ ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት (ጂዲፒ) ውስጥ ትርጉም ያለው ገቢ ማስገኘት ችሏል ወይንስ ጨርሶ በኢኮኖሚ ገቢ ምንጭነት ደረጃ አልደረሰም ለማለትም በቂ መረጃ የለም፡፡ ይህ መረጃ የሀገሪቱን ስፖርት በበላይነት ከሚመራው ተቋም በሪፖርት መልክ ሲቀርብ አይታይም፡፡ አይሰማም፡፡

በእርግጥ አነጋጋሪ ቢሆንም ቀጥታም ሆነ ቀጥተኛ ባልሆነ መልኩ በሀገሪቱ ውስጥ የስፖርቱ ዘርፍ አበርክቶ ሙሉ በሙሉ የለም ማለት አያስደፍርም። በተለይ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ከውድድርነት ተሻግሮ ታላላቅ የግንባታ ፕሮጀክቶች ለማስፈፀም የህዝብ ተሳትፎ ለማጠናከር በሚደረገው ርብርብ ላይ የማስተባበር ሚና እያበረከት ነው። ይህም እንደ አንድ ሀገራዊ ኢኮኖሚያዊ ምንጭ ሊወሰድ የሚገባው ነው። ይሁንና ይህም ቢሆን ቦግ ጭለም የሚል እንደመሆኑ የዘርፉን አበርከቶ ውስን አድርጎታል።

ሌላው ከሥራ ፈጠራ አንፃር ነው። ስፖርት በሀገር እድገት ከሥራ እድል ፈጠራ አኳያ ያለው ፋይዳ በአንድና በሁለት ደረጃ ተጠቅሶ የሚቆም አይደለም። ለአብነት በኮንስትራክሽን ዘርፍ አንድ ስታዲየም ሲገነባ በአማካኝ ለብዙ ሺ ዜጎች የሥራ እድልን የመፍጠር አቅም አለው። ሥራ እጥነትን መቅረፍ በራሱ አንድ የኢኮኖሚ አስተዋጽኦ ነው። ይሁንና በሥራ እድል ፈጠራም ቢሆን የሀገራችን የስፖርት ሴክተር ምን ያህል ሰዎችን በስሩ አቅፏል ለምን ያህል ዜጎችስ የሥራ እድል ፈጥሯል የሚለው በቅጡ የሚታወቅ አይመስለኝም።

በእርግጥ ስፖርቱ ከተሞች እንዲለሙ ምክንያት እየሆነ ነው። ትላልቅና ዓለም አቀፋዊ ይዘትን የተላበሱ ስታዲየሞች ግንባታ መገንባት ሌሎች የመሰረተ ልማት ግንባታዎች ጎን ለጎን እንዲገነቡ መልካም አጋጣሚ ይፈጥራል። ይህም ትልቅ የልማት በርን በመከፈት የስታዲየሙ ግንባታ በሰፈረበት ከተማ ውበትና ኢኮሚኖሚያዊ እድገት የራሱን አስተዋጽኦ እንደሚፈጥር የሚካድ አይደለም፡፡

ይሁንና እነዚህ የስፖርት መሰረተ ልማቶች ከሚሰጡት ስፖርታዊ አገልግሎት በተጨማሪ እንዴት ተጓዳኝ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም መስጠት ይችላሉ? እንዴትስ እየሰጡ ነው? የመሰረተ ልማቱን ያህል ስፖርቱን ኢኮኖሚ ማድረግ የሚችል ተመጣጣኝ አሰራርና አመራር እንዲሁም ስፖርተኛ አፍርተናል? ስፖርቱ ከሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ ፖለቲካዊና ማህበራዊ እድገት አንፃር እየተጋዘ ነው ወይንስ ተንቀራፏል? የሚለውን ጥያቄ ለጠየቀ መልሱን ማግኘት ቀላል አይሆንለትም፡፡

በቅርቡ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ቆይታ ያደረጉት የባህልና ስፖርት ሚኒስትሩ አቶ ቀጀላ መርዳሳም ይህን ታሪክ ለመለወጥና የስፖርት ዘርፉ ከድጋፍ ወጥቶ በሀገራዊ ኢኮኖሚ ዕድገት ላይ አስተዋጽኦ እንዲኖረው ለማድረግ አቅጣጫ ተቀምጦ ሥራዎች መጀመራቸውን አሳውቀዋል፡፡፡

‹‹የብዙ ሀገራት ተሞክሮ የሚያሳየው ስፖርት የገቢ ምንጭ ሆኖ ሀገራዊ ጥቅም እያስገኘ ነው፡፡ መንግሥት ስፖርትን ከመደገፍ አልፎ ዘርፉ በራሱ መንግሥትን እንዲደግፍ መሥራት ያስፈልጋል።›› ያሉት አቶ ቀጀላ፣ በኢትዮጵያም ዘርፉን ለኢንቨስመንት ክፍት በማድረግ ተጠቃሚ ለመሆን እየተንቀሳቀሰች መሆኑንም ነው የጠቆሙት፡፡

እርሳቸው እንደነገሩንም፣ እስካሁን ሲሠራበት የቆየው ስፖርትን ማልማት በሚል አካሄድ ነበር። አሁን ግን ስፖርትን ለልማት ማዋል የሚቻልበት አቅጣጫ ተቀምጧል፡፡ በዚሁ መሠረትም በዘርፉ ለሚሰማሩ ኢንቨስተሮች ምቹ በማድረግ ስፖርቱ ከድጋፍ ወጥቶ በሀገራዊ የኢኮኖሚ ዕድገት ላይ አስተዋጽኦ እንዲኖረው እየተሠራ ነው፡፡

ይህ ስፖርቱን ከኢንቨስትመንት ጋር ለማስተሳሰር የተጀመረ እንቅስቃሴ ይበል የሚያሰኝ ነው፡፡ይሁንና በተለይም ክለቦችን ከመንግሥት ጀርባ የማውረድ ተግባር ጊዜ ሊሰጠው የሚገባ እንዳልሆነ ሊታሰብበት ይገባል፡፡ ስፖርትን ወደ ኢንቨስትመንት ለመቀየር ከሚረዱ አማራጮች መካከልም ክለቦች በሕዝባዊ መሰረት እንዲታቀፉ ማድረግ አንደኛው ነው፡፡

እንደሚታወቀው ክለቦች በውድድር መድረኮች ለሚኖራቸው ውጤታማነትና ቆይታ በተለይም ለህልውናቸው ቀጣይነት የሚከተሉት የክለብ አደረጃጀት እጅግ ወሳኙን ድርሻ ይወስዳል። የክለቦችን አደረጃጀትና አመራር ቀጣይነትና መሰረት ባለው መልኩ ሕዝባዊ መሰረተን የተከተለ እንዲሆን ማድረግ ደግሞ ውጤታማነትን የላቀ የማድረግ አቅሙ ግዙፍ ነው፡፡

**ስፖርቱ ባለበት ስለመርገጡ ስለተደረገው፤ያልተደረገው አሊያም የማይደረገው ጥያቄ ሲነሳ መልሳችን ሰበብ ከሆነ በሞተ ትናንትና ባልተወለደ ነገ መሃል መሆናችንን መረዳት አለብን፡፡ከዚህ ቅርቃር ለመውጣት ደግሞ ዘርፉ እንዴት ይለወጣል? የሚለውን ብቻ ሳይሆን ክፍተቱንም ለመመልከት ዝግጁ መሆን እና የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት የግድ ይለናል**

በሀገር አቀፍ ደረጃ የወጣው የስፖርት ፖሊሲ፣ ክለቦች ደረጃ በደረጃ በሂደት ህዝባዊ አደረጃጀት እንዲኖራቸው ይደግፋል፡፡ የፖሊሲው ፍላጎትና የትኩረት አቅጣጫም የስፖርት አጠቃላይ እንቅስቃሴ፣ አደረጃጀትና አመራር ህዝባዊ መሰረት እንዲኖረው ነው።

ከዚህ በተጓዳኝ ስፖርቱ ከመንግሥት በጀትና ድጎማ ደረጃ በደረጃ የሚላቀቁበትና ራሱን የሚችልበት ምቹ ሁኔታ መፍጠርንም ይመለከታል። ይሁንና አሁን ላይ እንደሚታየው ከሆነ ጥቂት ከሚባሉት በስተቀር አብዛኞቹ የሀገሪቱ ክለቦች በመንግሥት ስር የተደበቁና ህዝባዊ አደረጃጀት የሌላቸው ናቸው።

ዘጠና በመቶ የሚሆኑት የሚተዳደሩም በመንግሥት የልማት ድርጅቶች ስር ነው። ይህ እንደመሆኑም ከመንግሥት የገንዘብ ድጎማ የተላቀቁ አይደሉም። ከመንግሥት ከሚመደብላቸው ውስን በጀት ውጪ የራሳቸው የሆነ ቋሚ የገቢ ምንጭ የላቸውም። የራሳቸው ቋሚ ገቢ ለመፍጠር የሚያስችሉ አሰራሮችን የሚተገብሩም አይደሉም።

ለአብነት እግር ካስን ብንመለከት አብዛኞቹ በሀገሪቱ የሚገኙ ክለቦቹ በመንግሥት ድጎማ የሚንቀሳቀሱና ህልውናቸውና አደረጃጀታቸው የመሰረቱ ናቸው፡ ፡ በዚህም ምክንያትነት የመንግሥት ድጎማ ሲቀር የክለቦቹ አደረጃጀትም አብሮ ይቀራል። የመንግሥት መዋቅር ሲስተካከልና ሲለዋወጥ ክለቦቹም አብረው ይለወጣሉ። አሊያም ይፈርሳል።

አብዛኞቹ ክለቦችም በመንግሥት የልማት ድርጅቶች የሚተዳደሩ እንደመሆናቸው ለአብነት የአንድ ፋብሪካ መዋቅር ሲቀየር ክለቦቹም አብረው ይቀየራሉ። አሊያም ስለስፖርት ጥሩ አመለካከት የሌለው አመራር ወደ ፋብሪካ በአመራርነት ከመጣ በግለሰብም ፍላጎት ሳይቀር ህልውናቸው አክትሞ ሊፈርሱ ይችላሉ። በዚህ ሂደት ለመፍረስ የበቁም አሉ። ለዚህ ደግሞ በርካታ ክለቦች ምሳሌ ይሆኑናል።

አሁን ላይ በሀገሪቱ በሁሉም ክልሎች የከነማ ክለቦች አሉ። የእነዚህ ክለቦችም አደረጃጀትም ተመሳሳይ ነው። ሙሉ በሙሉ በሚባል መልኩ የራሳቸው የሆነ ቋሚ ገቢ የሌላቸውና የክልል ከተማ አስተዳደር በቀጥታ ኢንቨስት የሚያደርግባቸው ናቸው።ከድጎማና ጣልቃ ገብነት የተላቀቁም አይደሉም።

የዚህ የክለቦችና የመንግሥት ያልተገባ ጥምረት መቀጠልም በርካታ ምክንያቶች ይነሳሉ፡፡ በተለይ መንግሥት ክለቦችን ምን ያህል እየደጎመ ማቆየት እንደሚቻል ያስቀመጠው የጊዜ ገደብ አለመኖሩ ዋነኛው ተጠያቂ እንዲሆንና ለችግሩ ዘላቂነት የጎላውን ድርሻ እንዲወስድ ያደርገዋል። ይህ ድክመቱም፣ ክለቦች በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ ልክ ቀጣይ አደረጃጀታቸውን የሚመለከት አቅጣጫ እንዳይቀይሱና ባሉበት ደረጃ ሁሌም እንዲመላለሱ አብይ ምክንያት ሆኗል።

ክለቦችም ቢሆን የመንግሥት ድጎማ ተመችቷቸዋልና ሌሎች አማራጮችን ላለመመልከት አይናቸውን ሸፍነዋል። የህልውናቸው ቀጣይነት የሚመሰረተው በመንግሥት ድጎማ የተለቀቀ አደረጃጀት ሲከተሉ መሆኑን ረስተዋል።በዚህም ምክንያት አደረጃጀታቸውን የሚመለከት ቀጣይ አቅጣጫ ሲቀይሱ አይስተዋልም።

ዘላቂ ውጤት ባለው መሰረት ላይ የተሻለ ሕዝባዊ አደረጃጀት፣ አሰራር ሥርዓትና የራሳቸው ቋሚ የገቢ ምንጭ ለመፍጠር አይንቀሳቀሱም፡፡ ስፖርቱን ከኢንቨስትመንት ጋር ለማስተሳሰርና ኢኮኖሚያዊ አበርክቶውን ከፍ ለማድረግ ከተፈለገ መሰል ችግሮች ልዩ ትኩረትና መፍትሄ ሊሰጣቸው የግድ ነው፡፡

ስፖርቱ ባለበት ስለመርገጡ ስለተደረገው፤ ያልተደረገው አሊያም የማይደረገው ጥያቄ ሲነሳ መልሳችን ሰበብ ከሆነ በሞተ ትናንትና ባልተወለደ ነገ መሃል መሆናችንን መረዳት አለብን። ከዚህ ቅርቃር ለመውጣት ደግሞ ዘርፉ እንዴት ይለወጣል?የሚለውን ብቻ ሳይሆን ክፍተቱንም ለመመልከት ዝግጁ መሆን እና የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት የግድ ይለናል፡፡

ከሁሉ በላይ መንግሥት እየደጎመ የሚያወዳድራቸው ክለቦች ከጥገኝነት ተላቀው ራሳቸውን እንዲችሉ ማድረግ አለበት። መንግሥትም ክለቦችን እየደጎመ መቀጠል የለበትም። ስፖርቱን ሕዝብና ክለቦቹ በጋራ እንዲመሩት ማድረግ ይኖርበታል። መስራት ያለበት እነዚህ አካላት የሀገሪቱን ህግና ደንብ አክበረው የሚሰሩበትን እድል መፍጠር ነው። ክለቦችም ከመደጎም የሚላቀቁበት የመውጫ ስትራቴጂ ሊያዘጋጁ የግድ ይላል። ክለቦች ሕዝባዊ አደረጃጀቶች ለመተግበር መንቀሳቀስና የራሳቸው የሆነ የገቢ ምንጭ በአስተማማኝ ሁኔታ መገንባት ላይ ትኩረት ሠጥተው ሊሠሩ ይገባል።

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## መፍጠን ያለበት የሳይበር መከላከል ሥራና ዝግጁነት

**ወርቅነሽ ደምሰው**

በዚህ የዲጂታል ዘመን የሀገሮች ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች የሚከወኑት በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ነው:: የመረጃ ልውውጡ፣ ክፍያው፣ ሕክምናው፣ ትምህርቱ፣ ግብርናው፣ ግንባታው፣ ኢንዱስትሪው፣ ወዘተ... ከእዚህ ቴክኖሎጂ ውጭ ሊሆን አይችልም::

ኢትዮጵያም የዲጂታል ቴክኖሎጂ አስፈላጊነትን በማመን በሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያዋ የአስር ዓመት መሪ አቅድ ለምጣኔ ሀብቱ ምሰሶ አርጋ ከያዘቻቸው አምስት ዘርፎች መካከል ይህ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ አንዱ ነው:: ሀገሪቱ በ2025 ዲጅታል ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ ስትራቴጂ ነድፋ መሥራቱን ተያይዛዋለች:: በመረጃ ለውውጡ፣ በክፍያው፣ የተለያዩ አገልግሎቶች በቴክኖሎጂው እንዲከናወኑ ለማድረግ እየተካሄዱ የሚገኙ ሰፋፊ ሥራዎችና ይህን ተከትሎ እየተከናወኑ ያሉ ተግባሮችም ይህንኑ ያመለክታሉ::

ቴክኖሎጂውን የመተግበሩ ሥራ ከተለያዩ አካላት ሊደርስበት የሚችልን ጥቃት የመከላከል ሥራም እንዲሁ ሌላው በዘርፉ መከናወን ያለበት ተግባር ነው። በቴክኖሎጂው የሚፈለገው ስፍራ ለመድረስ አንዱ መከናወን ያለበት ተግባር የማይበገር የሳይበር ደህንነት አቅምን መገንባት ነው::

የዲጅታል ኢኮኖሚ ግንባታው እየሰፋና እያደገ በመጣ ቁጥር የሳይበር ደህንነት ማስጠበቅ ደረጃ በዚያው ልክ እያደገ መምጣት ይጠበቅበታል:: ይህም ደግሞ የሳይበር ደህንነት ጉዳይ የእያንዳንዱ ዜጋ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ አካል እንዲሆን ያደርገዋል:: ለዚህም በየጊዜው ከሳይበር ምህዳር ጋር አብሮ የሚሄድ የሳይበር ግንዛቤ ያለው ዜጋ ማፍራትን ይጠይቃል::

ኢትዮጵያ ዲጅታል ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ እየሰራች ባለችበት በዚህ ወቅት የዜጎች የሳይበር ንቃተ ሕሊና ምን ይመስላል የሚለው መታየት ያለበት ወሳኝ ጉዳይ ነው:: ለእዚህም የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ ብሔራዊ የሳይበር ደህንነት ንቃተ ሕሊና ጥናት ውጤት በቅርቡ ይፋ አድርጓል::

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ዋና ዳይሬክተር አቶ ሰለሞን ሶካ እንዳሉት፤ የጥናቱ ዋና ዓላማ በሀገሪቱ የሳይበር ተጠቃሚ ዜጎችን የሳይበር ንቃተ ሕሊና ደረጃን በማወቅ የታዩ ክፍተቶችን ለመሙላት ቀጣይነት ያለው ሥራ ለመሥራት ነው::

በዓለም አቀፍ ደረጃ በሳይበር ንቃት ህሊና ዙሪያ የሚሰሩት ጥናቶችን ዋቢ አድርገው ዋና ዳይሬክተሩ እንዳሉት፤ ከ80 እስከ 90 በመቶ የሳይበር ጥቃት የሚደርሰው በተጠቃሚዎች የንቃተ ሕሊና ክፍተት ነው:: ይህ ጥናት መካሄዱ በሀገሪቱ ያሉት የንቃተ ሕሊና ክፍተቶች ተለይተው የሳይበር ደህንነትን ሊያስጠብቅ የሚችል ዜጋን ለመገንባት ያስችላል::

እሳቸው እንዳሉት፤ ሳይበር ሦስት ዋና ዋና ምሰሶዎች አሉት:: እነርሱም ቴክኖሎጂ፣ የአሰራር ሥርዓት እና ሰው ናቸው:: ከእነዚህ ውስጥ አንዱ በሆነው ሰው ላይ መሥራት ይገባል:: የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ሀገራዊ የሳይበር ደህንነት ባለቤትነትን በማረጋገጥ የሳይበር ምህዳርን ሊመሩ የሚችሉ የሕግ ማዕቀፎችና የአሰራር ሥርዓቶች በማዘጋጀት እንዲሁም የተቋማትና የዜጎችን ንቃተ ኅሊና ሊያዳብሩ የሚችሉ በርካታ ሥራዎች እየሰራ ይገኛል። የሳይበር ደህንነት ጉዳይ የሁሉም የጋራ ኃላፊነት ነው። የሀገሪቱን ዲጅታል ሉዓላዊነት የማስጠበቅና የማስከበር ሥራ በአንድ ተቋም ብቻ የሚሳካ ሳይሆን የሁሉንም ተቋማትና የዜጎች ቅንጅት ጥረት ይጠይቃል::

የሳይበር ደህንነት ጥቃት በሀገራችንም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከጊዜ ወደ ጊዜ በዓይነት ሆነ በብዛት ፈጣን በሆነ ሁኔታ እየጨመረ ይገኛል ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ እንደ ሀገር የሳይበር ጥቃት የመከላከል ሥራና ዝግጁነት ከሳይበር ጥቃት ባሕሪያትና ፍጥነት ጋር እኩል መራመድ ብቻ ሳይሆን መፍጠን ይኖርበታል ብለዋል:: ለዚህም የተቋማትና የዜጎች የሳይበር ንቃተ ኅሊናን በቀጣይነት መገንባት የግድ መሆኑን አስገንዝበዋል::

> **የሳይበር ደህንነት ጥቃት በሀገራችንም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከጊዜ ወደ ጊዜ በዓይነትም ሆነ በብዛት ፈጣን በሆነ ሁኔታ እየጨመረ ይገኛል፤ እንደ ሀገር የሳይበር ጥቃት የመከላከል ሥራና ዝግጁነት ከሳይበር ጥቃት ባሕሪያትና ፍጥነት ጋር እኩል መራመድ ብቻ ሳይሆን መፍጠን ይኖርበታል**

የጥናቱ አቅራቢ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር የሳይበር ደህንነት ባለሙያ አቶ አየለ ሞሴ የሳይበር ደህንነት ንቃተ ሕሊናን የተመለከተው ጥናት ብዙ መነሻዎችን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት መሰራቱን ይገልጻሉ:: ይህ ጥናት በኢትዮጵያ የሳይበር ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ የሆኑ ዜጎችን የሳይበር ንቃተ ኅሊና ደረጃ በማወቅ በቀጣይ የንቃተ ኅሊና ፕሮግራሞችን ለመቅረጽ ግብዓት እንደሚሆን አመላክተዋል::

እሳቸው እንደሚሉት፤ በዓለም አቀፍም ሆነ በአፍሪካ ደረጃ ባሉ ሀገራት የሳይበር ጥቃት በከፍተኛ ሁኔታ ለመጨመሩ ምክንያቶች ተብለው ከተቀመጡት ውስጥ አንዱ የተጠቃሚዎች የንቃተ ኅሊና ደረጃ ዝቅተኛ መሆን ነው:: ሁለተኛው ደግሞ የዲጅታል መሠረተ ልማቶች እድገት ነው:: በኢትዮጵያ እንዲሁም ከጊዜ ወደ ጊዜ የሳይበር ጥቃት በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ ያለበት ሁኔታ መኖሩን የአስተዳደሩ ሪፖርቶችም እንደሚያመለክቱ አቶ አየለ ጠቅሰዋል::

እስካሁን በኛ ሀገር የሳይበር ደህንነት ንቃተ ኅሊና ደረጃ ለማወቅ የሚያስችል ጥናት አልተሰራም ያሉት አቶ አየለ፤ ይህ ጥናት አጠቃላይ የተለያዩ ዓለም አቀፍ መረጃዎችን እና ባንኮችን አማካኝነት የተሰሩ ጥናቶችን መሠረት ተደርጎ የተሰራ መሆኑን ይናገራሉ:: ይህ ደግሞ የሚያሳየው የሳይበር ደህንነት ንቃተ ኅሊና ጉዳይ ገና በጅምር ላይ እንደሆነ ነው ብለዋል:: ለዚህም እንደ ምክንያት የሚነሳው ዝቅተኛ የሆነ የሳይበር ደህንነት ንቃተ ኅሊና መኖር እንደሆነ ጠቅሰው፤ ዝቅተኛ የሆነ የኢንዱስትሪው ተሞክሮ መኖሩ እና የሳይበር ደህንነት ስታንዳርድ፣ መመሪያዎች እና ፖሊሲዎች አለመኖራቸው የደህንነቱን ጉዳይ እንደጎዳው ያሳያል ብለዋል::

እሳቸው እንዳመለከቱት፤ ሌላኛው የኢንተርኔት ተጠቃሚዎች ቁጥር መጨመር ነው፤ በኢትዮጵያ ያለው የኢንተርኔት ተጠቃሚ ቁጥር እ.ኤ.አ 2017/2018 22 ነጥብ 3 ሚሊዮን የነበረ ሲሆን፣ ይህ አሃዝ እስከ እ.ኤ.አ 2022 33ነጥብ9 ሚሊዮን እንደ ደረስ ከኢትዮ ቴሌኮም የተገኘው መረጃ ያሳያል:: ይህም የኢንተርኔት ተጠቃሚ ቁጥር አሁን ላይ እየጨመረ መምጣቱ የዲጅታል ተጠቃሚነት በጨመረ ቁጥር ለሳይበር ጥቃት የመጋለጥ እድል በዚያው ልክ እየጨመረ የሚመጣ ለመሆኑ ማሳያ እንደሆነ ገልጸዋል::

ጥናቱ በርካታ ፋይዳዎች ያሉት ሲሆን፣ አንደኛ በኢትዮጵያ ያለው የንቃተ ኅሊና ደረጃ ምን ላይ እንደሆነ በዳታ የተደገፈ መረጃ ለማግኘት ይረዳል:: ሁለተኛ በኢንፎርሜሽን መረጃ ደህንነት አስተዳደር የንቃተ ኅሊና ግንባታ ለመስረጽ እየተካሄዱ ያሉ የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራሞች ምን ያህል ውጤታማ እንደሆኑ ለመገምገም ያስችላል:: ሦስተኛው ወደፊት በሀገር ደረጃ የሚሰጡ የንቃተ ሕሊና ሥራዎችን ለመቅረጽ ያግዛል፤ አራተኛውና የመጨረሻው በዚህ ጉዳይ ላይ ጥናት ለሚያደርጉ ሁሉ የመረጃ ምንጭ ሆኖ ማገልገሉ ነው::

ጥናቱ በዋናነት በኢንተርኔት ተጠቃሚዎች ላይ መሠረት ያደረገ ሲሆን፤ የሳይበር ንቃተ ሕሊና ደረጃን ለመለየት የሚያስችሉ የተጠቃሚዎች እውቀት ደረጃ፣ የአመለካከት እና አጠቃቀም ሁኔታዎች ላይ ትኩረት ተደርጎ የተሰራ ነው:: በዚህም በኢትዮጵያ የሳይበር ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ዜጎች አጠቃቀም (practice) ደረጃ ምን ይመስላል? የሳይበር ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ዜጎች አመለካከትስ ምን ደረጃ (attitude ) ላይ ይገኛል? የሳይበር ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ዜጎች የእውቀት (knowledge )ደረጃ ምን ይመስላል? የሚሉት በትኩረት ታይተውበታል::

ጥናቱ የሀገሪቱን ክልሎችና ዋና ዋና ከተሞች እንዲያካትት ተደርጓል:: የትምህርት ተቋማትን፣ የንግድ ስፍራዎችን፣ የተቋማት ቢሮዎችን፣ የመዝናኛ እና የመኖሪያ ስፍራዎችን ያካተቱ መረጃዎች የተሰበሰበበትም ነው::

የጥናቱ መመዘኛ መስፈርቶች በዓለም አቀፍ ስታንዳርድ መሠረት የተቃኙ ናቸው የሚሉት አቶ አየለ፤ እያንዳንዱ መመዘኛ መስፈርት የሳይበር ንቃተ ኅሊናን ለመፈተሽ እንደሚያስችልም ይናገራሉ:: ለአብነትም በእውቀት ደረጃ (knowledge) መመዘኛ መስፈርት ውስጥ የይለፍ ቃል፣ የፀረ ቫይረስ፣ የመተግበሪያዎች ዝመና፣ የሳይበር ጥቃት ክስተት፣ የነጻ ዋይፋይ አጠቃቀም፣ የኮምፒዩተር ቫይረስ፣ የኢሜል፣ የማህበራዊ ሚዲያ እና የመሳሰሉትን ተጠቃሚዎች ምን ያህል እንደሚያወቁ እንደሚጠይቅም አመላክተዋል::

በዚህም ረገድ የሳይበር ንቃተ ኅሊና እውቀት የሌላቸው 29 ነጥብ 23 በመቶ ሲሆኑ፣ ዝቅተኛ እውቀት ያላቸው 35ነጥብ 60፣ መካከለኛ እውቀት 11 ነጥብ75 እና ከፍተኛ እውቀት ያላቸው 23 ነጥብ 40 በመቶ ያህል መሆናቸውን ጥናቱ ያመላክታል:: ይህም በአጠቃላይ በኢትዮጵያ የሳይበር ደህንነት ንቃተ ኅሊና እውቀት ያላቸው 35 በመቶ እንዲሁም 65 በመቶ ያህል ዜጎች ደግሞ እውቀት የሌላቸው መሆናቸውን እንደሚያሳይ አመልክተዋል::

የሳይበር ደህንነት ንቃተ ኅሊና የአመለካከት ደረጃን (attitude) በተመለከተ በተዘጋጀው የሳይበር ጥቃት ሪፖርት፣ የይለፍ ቃል መቀያየር፣ የአካውንት ደህንነት አጠባበቅ፣ ጠንካራ የይለፍ ቃል መጠቀም የሚሉትና የመሳሰሉት መመዘኛ መስፈርቶች የተካተቱበት ነው። በዚህም በኢትዮጵያ የሳይበር ደህንነት ንቃተ ኅሊና አመለካከት ደረጃ አጠቃላይ 47 በመቶ ያህሉ አዎንታዊ አመለካከት ያላቸው ሲሆን ፤ 53 በመቶ ያህሉ አሉታዊ አመለካከት ያላቸው መሆናቸው ተመላክቷል::

በኢትዮጵያ የሳይበር ደህንነት ንቃተ ኅሊና አጠቃቀም (practice) ደረጃ በተመለከተም እንዲሁ በጥናቱ የተለያዩ መመዘኛዎች ቀርበዋል፤ የሳይበር ጥቃት ሪፖርት፣ የኢሜል ደህንነት፣ የይለፍ ቃል አጠቃቀም እና የመሳሰሉትን ተካተውበታል:: በዚህ ዙሪያ በተካሄደው ጥናት በኢትዮጵያ የሳይበር ደህንነት ንቃተ ኅሊና አጠቃቀም 50ነጥብ 2 በመቶ አዎንታዊ ልምምድ ያደረጉ ተጠቃሚዎቹ ሲሆኑ አሉታዊ ልምምዶች ያደረጉት ተጠቃሚዎች 48 ነጥብ 9 በመቶ ያህሉ ናቸው::

በአጠቃላይ ሀገር አቀፍ የሳይበር ደህንነት ንቃተ ኅሊና ደረጃ የሳይበር ደህንነት እውቀት፣ አመለካከት እና ልምምድ የታየበት ነው ያሉት የጥናቱ አቅራቢ፣ በጥናቱ የተገኘው ውጤት የሳይበር ደህንነት ንቃተ ኅሊና እውቀት ያላቸው ዜጎች 35 በመቶ መሆናቸውን ማመላከቱን ጠቅሰዋል፤ 65 በመቶ ያህል ዜጎች እውቀቱ እንደሌላቸው ተናግረዋል::

በአመለካከት በኩልም አዎንታዊ አመለካከት ያላቸው 47 በመቶ ያህል መሆናቸውን ጠቅሰው፣ 53 በመቶ ያህሉ አሉታዊ አመለካከት ያላቸው ናቸው ብለዋል። አጠቃቀም እንዲሁም አዎንታዊ ልምምድ ያደረጉ ተጠቃሚዎች ቁጥር 50 ነጥብ 2 በመቶ መሆናቸውን ገልጸው፣ አሉታዊ ልምምዶች ያደረጉት ተጠቃሚዎች 48 ነጥብ 9 በመቶ ያህሉ መሆናቸው ጥናቱ አመላክቷል ብለዋል:: በኢትዮጵያ ያለው የዜጎች የሳይበር ደህንነት ንቃተ ኅሊና ደረጃ 65 በመቶ ክፍተት እንዳለበት በጥናቱ መታወቁን አመልክተዋል::

እሳቸው እንዳሉት፤ የጥናቱ ተሳታፊዎች የትምህርት ደረጃ በአጠቃላይ ሲታይ 77 ነጥብ 3 ያህሉ ዲፕሎማ፣ ዲግሪ፣ ማስተርስ እና ፒኤችዲ ያላቸው ናቸው። ከእነዚህም 87 ነጥብ 5 ያህሉ ከ14 እስከ 35 ባለው የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ የኢንተርኔት ተጠቃሚዎች ናቸው:: በመሆኑም አብዛኞዎቹ የተማሩ ተጠቃሚዎች ሆነው ሳለ ለምን ይህንን ያህል የሳይበር ንቃተ ኅሊና ክፍተት ሊመዘገብ ቻለ የሚለውንም ለማየት ተሞክሯል።

በአጠቃላይ የትምህርት ሀገር አቀፍ የሳይበር ደህንነት ንቃተ ኅሊና ተለምዷዊ የሆነውን የሥነ ትምህርት በማሳደግና በማስፋፋት ብቻ ችግሩን መቅረፍ እንደማይቻል አቶ አየለ ጠቅሰው፣ በሀገራችን ይህ ከፍተኛ የሆነ የሳይበር ደህንነት ንቃተ ኅሊና ክፍተት ለሁሉም ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ዜጋ እኩል ስጋት እንደሆነ ያመላክታል ብለዋል:: ይህ ማለት ደግሞ የትምህርት ደረጃ ብቻውን የሳይበር ደህንነት ንቃተ ኅሊናን ለማረጋገጥ በቂ አለመሆኑን እንደሚያሳይ ጠቅሰው፣ ሁሉም ዜጋ የሳይበር ደህንነት ጉዳይን የራሱ ጉዳይ አድርጎ የሳይበር ምህዳሩ የሚያስፈልገውን ፕሮቶኮል አሟልቶ መጓዝ እንደሚያስፈልግ ማሳያ መሆኑን አስገንዝበዋል::

አቶ አየለ እንደሚሉት፤ ከጥናቱ ምክረ ሃሳቦች አንዱ በሳይበር ንቃተ ኅሊና ላይ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ነው:: ሌላኛው የሳይበር ደህንነት ጉዳይ ሜይንስትሬም መደረግ መቻል ያለበት መሆኑ ነው:: ይህንንም በፖሊሲ፣ በሕግ ጸድቆ የግልም ሆነ የመንግሥት ተቋማት የሳይበር ደህንነት ጉዳይን ሜይንስትሪም አድርገው ካልሰሩበት አሁንም የሳይበር ንቃተ ኅሊና ክፍተቱ ሊቀጥል ይችላል::

ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ አንደኛ የሳይበር ደህንነት ጉዳይ በየተቋማቱ በመዋቅር ደረጃ ሜይንስትሪም መደረግ አለበት:: ሁለተኛ ለዚህም አስፈላጊውን የቴክኖሎጂና የሰው ኃይል አሟልቶ ወደ ሥራ መግባት ያስፈልጋል:: ይህንን ለማድረግ ደግሞ የመንግሥትና የግል ተቋማት እንዲሁም በተለየ መልኩ የሚዲያ ተቋማት ትኩረት አድርገው መሥራት ይጠበቅባቸዋል ሲሉ አቶ አየለ አጽዕኖት ሰጥተው አስታውቀዋል::

ይህ ሁሉ ከተደረገ በኋላ እንዴት ነው ንቃተ ኅሊናን በማስፋት ግንዛቤ ማምጣት የሚቻለው የሚለውን ለማየት ብዙ ዓይነት መንገዶች መጠቀም ይቻላል የሚሉት አቶ አየለ፤ ከእነዚህ መንገዶች ውስጥ ለኛ ሀገር ነባራዊ ሁኔታ በሚሆን መልኩ የምንፈልገውን ዓይነት የሳይበር ንቃተ ኅሊና ለማምጣት የሚያስችሉ ስልቶች መጠቀም ይገባል ብለዋል::

እንደ ሀገር የሳይበር ንቃተ ኅሊና ክፍተት ከፍተኛ መሆኑን ጠቅሰው፣ በተወሰነ ፕሮግራም ብቻ ሰዎች ማንቃት አይቻልም ብለዋል:: ለዚህም የሳይበር ምህዳሩ የሚፈልገው እውቀትና አተገባበር እንዲኖር ከግለሰብ ጀምሮ በየደረጃው ያለው ሁሉም አካል በቅንጅትና በትብብር መሥራት ይጠበቅበታል ሲሉ ምክረ ሃሳባቸውን ሰጥተዋል::

# ወቅታዊ ትንታኔ

# መጪውን ጊዜ የሚወስነው አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ

**ምሕረት ሞገስ**

አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ የሰውን አእምሮ ማለትም ችግር የመፍታት እና ውሳኔ የመስጠት ችሎታዎችን ይዞ ሰውን ተክቶ ሥራዎችን ማከናወን ማስቻል መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ። ይህ አሁን ላይ በኢትዮጵያም ሥራ ላይ እየዋለ፤ ምርምር እየተካሔደበት ያለው አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ምንድን ነው? ስንል ባለሙያዎችን አነጋግረናል፡፡

የኢቲስዊች ፕሮግራም ቢሮ ዳይሬክተር አቶ አቤኔዘር ወንድወሰን እንደሚናገሩት፤ ቀደም ባሉት ዓመታት ኮምፒውተርም ሆነ ሌሎች ቴክኖሎጂዎች ሰውን ተክተው የመሥራት አቅም አልነበራቸውም፡፡ አሁን ግን የተለያዩ አልጎሪዝሞች ማለትም በፊት ከነበረው በላይ ለኮምፒውተሩ ብዙ መረጃ በመሥጠት፤ በተሠጠው መረጃ ልክ እንደሰው ማሰብ እንዲሞክር እና ውሳኔ እንዲሠጥ ማስቻል አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ የሚባለውን አዲስ ቴክኖሎጂ አስተዋውቋል፡፡

ይህ ቴክኖሎጂ የተገኘው ሰው የተለያዩ መረጃዎችን ይዞ እንዴት እንደሚወስን በማስተማር እና ኮምፒውተሩ ያንን መረጃ ይዞ የሚጠየቀውን ጥያቄ እንዲመልስ ለማስቻል በተሠራው ሥራ ነው፡፡ በተዘዋዋሪ የኮምፒውተር ሥርዓት ላይ ሰው የሚሠራቸውን ሥራዎች እንዲሠራ ለማሻሻል በተካሔደው ሙከራ፤ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ተፈጠረ ማለት ነው፡፡ ይህ እንደሰው በምክንያታዊነት ማሰብን እና መሥራትን ያካተተ ሥርዓት መሆኑን አቶ አቤኔዘር ያስረዳሉ፡፡

አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ አንድ ነገር ብቻ አለመሆኑን ሲያስረዱ፤ አንደኛው ማሽንን ማስተማር ነው፡፡ ማሽን ወይም ኮምፒውተር ሲማር ከሚሰጠው መረጃ ተነስቶ ምላሽ እንደሚሠጠው ሁሉ፤ ይሄኛውም ማለትም አርቴፊሻል ኢንተለጀንሱ ተምሮ ዕውቀት እንዲያካብት ይደረጋል ይላሉ፡፡

ሌላኛው አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ጥልቅ ማስተማር ነው፡፡ ይህ ማሽኑ በጣም ብዙ መረጃ ተሸክሞ ለምሳሌ ምስሎችን፣ የንግግር ድምፆችን እና ሌሎችንም መለየት የሚችል ሲሆን፤ ይሄኛው በሁለተኛ ደረጃነት ተቀምጦ እንደሚገኝ ያብራራሉ፡፡

ተፈጥሯዊ የቋንቋ ሂደት ወይም ተፈጥሯዊ ንግግርን ለኮምፒውተሩ ማሳየት፣ ማስተማር እና ማስተርጎም የሚቻልበት ሁኔታም አለ፡፡ ይሄ ማሽኑ እንደሰው ማውራት እንዲችል ማድረግ ነው፡፡ ከዛ ውስጥ ለምሳሌ በአገልግሎት መስጫዎች ሰዎች ሳይኖሩ የደንበኞችን ጥያቄዎች ልክ እንደሰው ሆኖ መመለስ እና ድምፅ እየሠሙ ቋንቋን መተርጎምም በአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ መፈፀም ተችሏል ሲሉ አቶ አቤኔዘር አርቴፊሻል ኢንተለጀስን የደረሰበትን ደረጃ ያብራራሉ፡፡

አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ የሚያየውን ወይም የተሠጠውን ምስል እና ቪዲዮ በመተርጎም ማወቅ የሚችልበት ሁኔታ መኖሩን አመልክተው፤ ለምሳሌ አንድ ሰው ቤት ለመግባት የአንድ ሰው ፊት የቤቱ መግቢያ ቁልፍ ማድረግ እንደሚቻል አብራርተዋል፡፡ ይሄ የሆነው ማሽኑ ከዚህ በፊት የተመዘገበ ነው ብሎ የሰውን ፊት እንዲለይ ፕሮግራም በመደረጉ መሆኑንም ነው ያስረዱት፡፡

እንደ አቶ አቤኔዘር ገለፃ፤ ከላይ የተገለፁትን ሥርዓቶች አንድ ላይ በማድረግ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስን ለተለያዩ ጉዳዮች መጠቀም ይቻላል፡፡ ይሄን ለምሳሌ በጤና፣ በፋይናንስ ሥራዎች በተለይም በባንክ አገልግሎት፣ በትምህርት እና በመዝናኛ ላይ ትልቅ ለውጥ እያመጣ ነው፡፡

በአጠቃላይ ግን አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ የተፈጠረበት ምክንያት ሰዎች በሚያስፈልጉበት ቦታ ሁሉ ገብቶ በመሥራት የሰዎች ድካም ለመቀነስ መሆኑን በማመላከት፤ በተለያዩ ዘርፎች ላይ ሰዎችን ተክቶ እየሠራ መሆኑ ለአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ሃሳብ እንደምሶሶ የሚወሰድ ጉዳይ ነው ይላሉ፡፡

አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ በመኖሩ ሥራዎች የሚከናወኑበት ጊዜ እጅግ ያጠሩ እንደሚሆኑ፤ አርቴፊሻል ኢንተለጀንሱም ተንትኖ እና ተርጉሞ በሰከንዶች ምላሽ መስጠቱ ሕይወትን እንደሚያቀል አብራርተዋል፡፡ በባንክ የገንዘብ ልውውጥ ላይ እየተሠራ ያለውን ጠቅሰው፤ የመጀመሪያው ጥቅም የክፍያ ማጭበርበሮችን መለየት እንዲችል ተደርጎ ተሠርቷል፤ በዚህም ብዙ ውጤት



አቶ አቤኔዘር ወንድወሰን



አቶ አበበ በቀለ

መጥቷል ብለዋል፡፡

አርቴፊሻል ኢንተለጀንሱ ደንበኛው ከቀን ወደ ቀን እንዴት አድርጎ ገንዘብ እንደሚያዘዋውር በማጥናት ያ ደንበኛ ከሚሳየው የአጠቃቀም ልምድ ወጣ ሲል ወዲያውኑ በመለየት ያ ደንበኛ ራሱ ላይሆን እንደሚችል አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ምልክት በመሥጠቱ ደንበኞች እንዳይጭበርበሩ ሰዎችን እና ተቋማትንም እየጠበቀ መሆኑንም ጠቁመዋል፡፡

አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ በደህንነት ጥበቃ በኩልም ትልቅ ሥራ እየሠራ መሆኑን በማስታወስ፤ ዐሻራን አንብቦ በር መክፈት የእዚሁ ቴክኖሎጂ ውጤት መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ አሁን ላይ በየቦታው ፊትን እና ዐሻራን የሚለየው አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ መሆኑን ተናግረዋል። በደንበኞች አገልግሎት ላይም በዚሁ ቴክኖሎጂ የታገዘ የጥሪ ማዕከል አገልግሎት እየተሰጠ መሆኑን በመጥቀስ፤ ለደንበኞች የተለያዩ መረጃዎችን፣ ግላዊ ምክረ ሃሳቦችን የመሥጠት ሥራ በአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ አማካኝነት እየተካሔደ ነው ብለዋል፡፡

አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ የሚይዘው መረጃ የብዙዎችን በመሆኑ የአንድ ተቋም ደንበኛ ምን እንደሚፈልግ በመገመት ለደንበኞቹ መሠጠት ያለበትን አገልግሎት ቀድሞ ተረድቶ በተቋሙ የሚሰጠው አገልግሎት እንዲያሻሽል መረጃ ይሰጣል ብለዋል፡፡

አንድ ተቋም ከደንበኞች ባህሪ እና ፍላጎት በመነሳት ምን ዓይነት ዕቃ ላቅርብ ወይም ምን ዓይነት አገልግሎት ልስጥ የሚለውን በመተንተን ምን ዓይነት አገልግሎቶችን በቀላሉ ቀድሞ በመረዳት ብዙ ተቋማት ማቅረብ እንዲችሉ አስችሏቸዋል፡፡

እንደ አቶ አቤኔዘር ገለፃ፤ በጤና ዘርፍ ላይ ልክ እንደ ሕክምና ባለሙያ ሆኖ ምክረ ሃሳቦችን ሁሉ የመስጠት ሁኔታ እየታየ ነው፡፡ ኤክስሬ፣ ኤም አር አይ እና ሲቲ ስካን በማንበብ አንድ ታካሚ የት ቦታ ላይ ምን እንዳመመው በቀላሉ በሰው ዓይን ተነበው ሊለዩ የማይችሉትን በሙሉ በመለየት የተሻለ የሕክምና አገልግሎት እንዲኖር አስችሏል፡፡

አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ የታካሚውን ያለፈ የሕክምና መረጃን ስለሚይዝ ቀጣይነት ያለው ሕክምናዎችን ለምሳሌ እጅ ላይ የሚታሰር ነገር በማድረግ የታካሚውን የጤና ሁኔታ የሕክምና ባለሙያዎች መከታተል እንዲችሉ የሚያግዝበት ሁኔታ ላይ መደረሱንም አብራርተዋል፡፡

የተለያዩ መረጃዎችን በመተንተን እና በመተንበይ በምርምር የተሻለ መድኃኒት እንዲኖር የተሻለ አስተዋፅኦ ያደርጋል ያሉት አቶ አቤኔዘር፤ በትምህርት ላይም የተሻለ አገልግሎት እንዲገኝ ያስቻለ መሆኑን ተናግረዋል፡፡ በአንድ ክፍል ውስጥ ግላዊ የማስተማሪያ ማለትም የተማሪውን አቅም በማጥናት የተመቸ የማስተማሪያ መንገድ በመቅረፅ ዕገዛ እያደረገ እንደሚገኝም ተናግረዋል፡፡

የፈተና ውጤትን ወዲያውኑ አርሞ በደቂቃ ውጤቱን የማሳወቅ እና አስጠኚ ሆኖ የማገልገል እንዲሁም ለተማሪዎች የመለማመጃ ጥያቄዎችን የመሥጠት ሥራ በአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ እየተሠራ መሆኑን ነው ያመላከቱት፡፡

በአጠቃላይ በቤት ውስጥ የተሻለ ሕይወት እንዲኖር፣ የኃይል አጠቃቀም ላይ እንዳይባክን የማገዝ፣ የደህንነት ካሜራ እንዲኖር የማድረግ እና አኗኗራችን ምርጥ እንዲሆን የማገዝ ሥራንም ያከናውናል ብለዋል፡፡

የቤት ውስጥ ዕቃዎች ሲበላሹ ቶሎ ከመለየት ጀምሮ መኪናዎች ያለ አሽከርካሪ መነዳት የሚችሉበትን ሁኔታ በአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ አማካኝነት ማከናወን መቻሉንም አመላክተዋል፡፡

በዓለም አቀፉ የግሎባል ቴክኖሎጂ ኤንድ ዲጂታል ሶልዩሽን የሚሠሩት አቶ አበበ በቀለ በበኩላቸው፤ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ በቀላል አገላለፅ ሰው ሠራሽ የማሰብ ችሎታ ማለት ነው ይላሉ፡፡ ሰው ያስባል፣ ይሠራል፡፡ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስም እንደሰው ሆኖ አስቦ አንድ ሰው ሊያከናውነው የሚችለውን ውስብስብ ሥራዎች ያካሂዳል፡፡ ምናልባት ማመዛዘን እና ውሳኔ እስከ መስጠት የዘለቀ ሊሆን እንደሚችል ተናግረዋል፡፡

የአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ጥቅምን አስመልክቶ ሲያስረዱ፤ በጦር ቴክኖሎጂ እና በሌሎችም በተለያዩ ዘርፎች ላይ እጅግ የተወሳሰቡ ሥራዎች በአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ አማካኝነት በመሠራት ላይ ናቸው ብለዋል፡፡ የሰው ልጅ ጉልበት ውስን በመሆኑ አንድን ሥራ የሚሰራበት ሰዓትም ውስን ነው፡፡ የአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ያለ ምንም ድካም ከሰው በላይ እየሠራው መሆኑንም አመላክተዋል፡፡

ሰው ለረዥም ሰዓት ሊሠራው የማይችለው ጉልበቱ ወይም አዕምሮውን የሚደክመውን አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ በቀላሉ ይሰራዋል ሲባል፤ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫዎች አካባቢ፣ የአየር ትራንስፖርት በሚሰጥበት አካባቢ፣ የባቡር መስመሮች፣ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች በሌሎችም ከፍተኛ የሰው አቅም የሚጠይቁ ብልሽት ሲያጋጥም ጀምሮ ያሉ ሥራዎችን ለማከናወን አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ፕሮግራም በተደረገው ልክ እየሠራ እንደሚገኝ ተናግረዋል፡፡

በርግጥ ሰዎችን ተክቶ ሲሠራ ሥራ አጥነት ሊፈጠር እንደሚችል እና ከማሰብ አንፃር ሲታይ የሰዎች የመሥራት እና የማሰብ አቅምን በመንጠቅ የሚገባቸውን እንዳይሠሩ የማድረግ እና የምርምር ሥራዎች ላይ ብዙ ድጋፍ በማድረግ የማሰላሰል ችሎታ ላይ ተፅዕኖ ሊፈጥር ይችላል ተብሎ ይገመታልም ብለዋል፡፡

ነገር ግን ከሚያስከትለው ጉዳት ይልቅ ያለው ጠቀሜታ ብዙ በመሆኑ፤ ቴክኖሎጂውን መጠቀም የተሻለ ነው የሚል እምነት እንዳላቸው ተናግረዋል፡፡ መረሳት የሌለበት ሰዎች እንሥራ ቢሉም የማይሠሩትን እና የማይወስኑትን ውሳኔ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ይሠራል፡፡

አቶ አቤኔዘር እንደ አቶ አበበ ሁሉ፤ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ከቁጥጥር ውጭ ይሆናል የሚል ስጋት መኖሩን ይጠቁማሉ፡፡ ቴክኖሎጂው በጣም ምጡቅ በመሆኑ፤ ከሰዎች ቁጥጥር ውጭ ከሆነ አደጋው የከፋ ሊሆን ይችላል ብለዋል፡፡ በተቃራኒው ሰዎች በቀናት እና በሰዓታት የሚሠሩትን ሥራ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ በሰከንዶች መሥራቱ የሥራ ዕድልን ይሻማል የሚለው ግን እርሳቸው አያምኑበትም፡፡

አንድ ሰው ቀኑን ሙሉ የሚሠራውን ሥራ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ በሰከንዶች ቢሠራው፤ ያ ሰው በሌላ አምራች በሚያደርገው ሥራ ላይ እንዲያተኩር ያግዘዋል እንጂ ሰዎች የሥራ ዕድል እንዳይኖራቸው አያደርግም ብለዋል፡፡

በርግጥ በዓለም ላይ አሁን ያለው የፀሐፊዎችን ሥራ ሙሉ ለሙሉ ይቀንሳል የሚለው ስጋት መኖሩን አመልክተው፤ የፀሐፊዎችን ሥራ ተክቶ ኢሜል መያዝ፣ ደብዳቤ መፃፍ እና ፕሮግራም ማውጣት በአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ እየተከናወነ በመሆኑ፤ በቀጣዩ አንድ ዓመት ሙሉ ለሙሉ የፀሐፊዎች ሥራ ይጠፋል ተብሎ ይፈራል ብለዋል፡፡ አቶ አቤኔዘር እንዳመለከቱት፤ ይህ ቢሆንም ትኩረትን አንድ ሥራ ላይ ከማድረግ ይልቅ ሌሎች አማራጮችንም ለማየት እንዲቻል መንገድ ይፈጥራል ብለዋል፡፡

ሁሉንም ነገር አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ከሠራው ሰዎች ብዙ እንዳያስቡ እና እንዳያሰላስሉ ያግዳል የሚለውንም ሃሳብ የሚቃወሙት አቶ አቤኔዘር፤ እንደውም የአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ መምጣት ሰዎች ብዙ እንዲያነቡ እና ብዙ እንዲያውቁ ያግዛል ብለዋል፡፡ በፊትም በጎግል ፍለጋ ተካሂዶ ለማንበብ ይመጣ የነበረው ውጤት፤ በአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ በጣም ፈጣን እና ብዙ መረጃ በአንድ ጊዜ የሚገኝበት ሁኔታ መኖሩ እንደውም የሰዎች ዕውቀት የበለጠ በንባብ እንዲያድግ ያግዛል ብለዋል፡፡ ዋናው ነገር ቴክኖሎጂ ሲመጣ መልካም ጎን ቢኖረውም በተቃራኒው ጉዳት አይኖረውም ማለት አይቻልም፡፡ ሙሉ ለሙሉ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ላይ ጥገኛ መሆን ጥሩ ባይሆንም በጥንቃቄ በመያዝ ቴክኖሎጂውን መጠቀም የግድ ነው ብለዋል፡፡

አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ከኢትዮጵያ አንፃር ተለይቶ ሲታይ፤ ቴክኖሎጂዎችን በመኮረጅ የመሥራት ተነሳሽነት አለ፡፡ አጠቃላይ ከኢትዮጵያ ስትራቴጂ እና ከኢኮኖሚው ጋር የማያያዝ ብዙ ተነሳሽነቶች ታይተዋል ያሉት አቶ አቤኔዘር፤ በአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ መሠረት ላይ እየተገነቡ ያሉ ጅምር የቴክኖሎጂ እንቅስቃሴዎች እና ብዙ ጥናቶችን እየተካሔዱ መሆናቸው ፤ የአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ፕሮግራሞች ተቀርፀው በየዩኒቨርሲቲው ትምህርቶች መሠጠት መጀመራቸው ተገቢ እና ትክክለኛ ርምጃ ነው ብለዋል፡፡ ዓለም ወደፊት ሲሔድ ወደኋላ መቅረት ሁልጊዜም እንደ ሀገርም እንደ ግለሰብም ተጎጂ እንደሚያደርግ አመልክተው፤ ኢትዮጵያም አምናበት ከጊዜው ጋር ለመሔድ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ብዙ እንቅስቃሴዎች ማድረጓን አጠናክራ መቀጠል እንዳለባት አመላክተዋል፡፡

አሁን ኢትዮጵያ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስን ተግባራዊ ማድረጓ በብዙ መልኩ የሚጠቅማት መሆኑን አቶ አበበም የተናገሩ ሲሆን፤ ለሰላም፣ ለኢኮኖሚ በአጠቃላይ ተዘርዝረው ለማያልቁ ጉዳዮች ጥቅም ያለው በመሆኑ ኢትዮጵያም በአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ላይ የምትሠራውን ሥራ አጠናክራ መቀጠል አለባት ብለዋል።

አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ በተመራማሪዎች ብቅ ያለው በ1950ዎቹ ነበር፡፡ መነሻው በፈላስፋው በአለን ቱሪንግ ስም የተሰየመው የቱሪንግ ፈተና ፕሮግራም ነው። አንድ ማሽን ከሰው ባህሪ ጋር ምን ያህል ሊጣጣም እንደሚችል ለማወቅ በ1950 ቱሪንግ ፈተና አከናወነ፡፡ በመቀጠል በ1956 ዓ.ም የሒሳብ ረዳት ፕሮፌሰር የሆኑት ጆን ማካርት ስለሰው ሰራሽ ማሽን የማሰብ ችሎታ ጉዳይ አነሱ፡፡ በመቀጠል አሁን የደረሰበት ደረጃ ላይ ደረሰ፡፡

ምሁራኖቹ የወደፊቱን አስመልክቶ ሲናገሩ፤ ኢትዮጵያ ዓለም የደረሰበት ደረጃ ላይ ደርሳ፤ እየታዩ ያሉ ትልልቅ ለውጦች ይበልጥ ያድጋሉ የሚል እምነት እንዳላቸው ተናግረዋል፡፡ በኢትዮጵያ ደረጃ አሁን ጅምር ቢሆንም፤ በኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ዕድገት ላይ ትልቅ ለውጥ ይመጣል፡፡ በሰዎች አገልግሎት አሰጣጥ ላይ መሻሻሎች ይኖራሉ፤ ግብርና፣ ትምህርት እና ጤና ላይ ትልልቅ መሻሻሎች ይመጣሉ ብለዋል፡፡ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስን መሠረት ያደረጉ ምርትን ለማሳደግ የሚረዱ ብዙ ምርምሮች ሊካሔዱ እና በዛም ውጤት ሊገኝ ይችላል፡፡ ግን ይሄን ሲባል ሊመጣ የሚችለውንም ጉዳት በጥንቃቄ እየተከታተሉ ማለፍ ያስፈልጋል ብለዋል።

ማህበራዊ

# ሴቶች

# አፍላ ወጣትነት + ሴትነት + ኤች አይ ቪ

**አስመረት ብስራት**



ወጣት ናት። በ20ዎቹ እድሜ መጀመሪያ አካባቢ የምትገኝ። ወጣትነቷ ይሁን ሌላ ዓይነግቡ የምትባል ዓይነት ቆንጆ ልጅ ናት። ጸጉሯ የሀር ነዶ የሚባል ዓይነት ነው። በፍልቅልቅ ፊቷ ላይ ከእድሜዋ በላይ ብስል ያለች ጨዋታዋ የማይሰለች ዓይነት መሆኗ ደግሞ ይበልጥ ትኩረቴን ስቦታል። ሰላማዊት ተስፋዬ ትባላለች። ኤች አይ ቪ ኤድስ በደማቸው ውስጥ ኖሮ ከተወለዱ ልጆች መካከል አንዷ ናት።

በአጋጣሚ ከሰዎች ጋር ስለ ኤች አይ ቪ ኤድስ ሥርጭት መብዛት፤ ይበልጥ አፍላ ወጣቶችን እያጠቃ መሆኑንና የመሳሰሉትን ጉዳዮች በምንጨዋወትበት ወቅት ነበር የተዋወቅነው። ስሟን በሌላ እንድቀይርና ፎቶዋን እንዳልጠቀም ካስጠነቀቀችኝ በኋላ ነበር ለዛሬ የሴቶች ዓምድ እንግዳ ለመሆን የተስማማችው። ከሰላም ጋር የነበረንን አፍ አያስከድኔ ወግ በዚህ መልኩ ይዘንላችሁ ቀርበናል መልካም ንባብ።

እንደምታይኝ ወጣት ነኝ። ቆንጆም ነኝ። አይደለሁም እንዴ ? አለች በፈገግታ። እንደ ሌሎቹ ወጣቶች ግን እንደ ልቤ ለመሆን ያልታደልኩ ስወለድ ጀምሮ ኤች አይ ቪ በደሜ ውስጥ ይዤ የተወለድኩ ልጅ ነኝ። ኤች አይ ቪ ኤድስ በደሜ ውስጥ መኖሩ በየቀኑ መድኃኒት እንድወስድ ከማድረጉ ያለፈ ይህ ነው የሚባል ተፅዕኖ አሳድሮብኛል ብዬ አላምንም። ያለፈኩትን በሙሉ አልፌ ዛሬን የሰጠኝን አምላክ እያመሰገንኩ ባለሁበት መትጋትን ሥራዬም ምርጫዬም አድርጌዋለሁ።

አባቴ ኮንትሮባንድ ንግድን የሚቆጣጠር መውጫ መግቢያ ኬላዎች ላይ የሚውልና የሚያድር የፖሊስ አባል እንደነበረ አሁን አብሬያት የምኖረው አክስቴ ነግራኛለች። አንድ ወርም ሁለት ወርም ቆይቶ ነው የሚመጣው። አባቴ ከእናቴ ጋር የነበራቸው ፍቅር እጅግ በጣም የሚያስቀና እንደነበረም ጎረቤቶቻችን ነግረውኛል። እና አሁን አብራን የምትኖረው አክስቴ እናቴ ብቻዋን እንዳትሆን አምጥታ ታስተምራት የነበረች እህቷ ናት።

እናትና አባቴ በጣም የሚተማመኑና የሚከባበሩ ባለትዳሮች ስለነበሩ በሽታው እስኪጎዳቸው ድረስ ወደ ሕክምና አልሄዱም ነበር። እናቴም ከሕክምና ክትትል በላይ ፀበልን የምታዘወትር ሴት ነበረች። እርጉዝ ሆና እንኳን ለክትትል ስትሄድ የኤች አይ ቪ ምርመራ አለማድረጓን ሰምቻለሁ።

እንደዛ በፍቅርና በመከባበር የሚኖሩት እናትና አባቴ አንዴ መንፈስ ነው፤ አንዴ የሰው እጅ ነው በማለት ፈለቀ የተባለ ፀበል በሙሉ አንድም አይቀራቸውም ነበር። ቀኑ እየረዘመ በሽታ የመከላከል አቅማቸው እየደከመ ሲሄድ እንደ ጉንፋን አድርጎ የጀመራቸው ሕመም በጣም ሲባባስ ሆስፒታል ቢሄዱም በቂ ሕክምና ሳይደረግ በሽታቸው ከመታወቁ በወራት እድሜ ውስጥ ተከታትለው አለፉ።

ያኔ እኔ ሶስት ዓመቴ ነበርና አብራን ትኖር ለነበረችው የእናቴ እህት ሐኪሞቹ እንድታስመረምረኝ ነግረዋት ወላጆቼም በኤች አይ ቪ መሞታቸውን እኔም በደሜ ውስጥ መኖሩን ያረዷታል። የኮሌጅ ተማሪ የነበረችው አክስቴ በሽታው እንዳለብኝ ስትሰማ ወዲያው የመሞት መስሏት በጣም አዝና እንደነበረ ነግራኛለች።

በወቅቱም የኤች አይ ቪ ቫይረስ እንዴት እንደሚተላለፍ እና ከኤች አይ ቪ ጋር መኖር ምን እንደሚመስል እጅግ በጣም ብዙ የተሳሳቱ አመለካከቶች፤ ጭፍን ጥላቻ እና መገለልን ስለነበር አክስቴ ስለህመሜ ሳትናገር ሐኪሞቹ የሚሏትን በማድረግ እስካሁን ድረስ ልትንከባከበኝ ወሰነች።

በድብቅ ልትንከባከበኝ ብታስብም ስለበሽታው መተላለፊያ መንገዶች የምትሰማው ነገር እሷም በበሽታው እያዝ ይሆን የሚል ስጋት ውስጥ ከቷት እንደነበረ ታስታውሳለች። ይህ የተሳሳተ ግንዛቤ ለረዥም ጊዜ በኤች አይ ቪ በሚኖሩ ሰዎች ላይ መድልዎ ሲያስከትል መመልከቷን አክስቴ የነገረችኝ ሲሆን በወቅቱ ብዙ ሰዎች ኤች አይ ቪ በቆዳ ንክኪ ወይም በምራቅ እንደሚተላለፍ ያምኑ ነበር ብላኛለች።።

በንክኪ፣ በእንባ፣ በላብ፣ በምራቅ ወይም በሽንት፤ ተመሳሳይ አየር መተንፈስ ማቀፍ፣ መሳም ወይም እጅ መጨባበጥ የመመገቢያ ዕቃዎችን መጋራት የውሃ ፍሳሽ መጋራት የግል ዕቃዎችን መጋራት የስፖርት ማዘውተሪያ መሳሪያዎችን በጋራ መጠቀም የመጸዳጃ ወንበርን፣ የበርን እጀታ ወይም እጀታውን መንካት ቫይረሱን የማያስተላልፍ መሆኑንና በቫይረሱ ከተያዘ ሰው ኤች አይ ቪ የሚተላለፈው እንደ ደም፣ የዘር ፍሬ፣ የሴት ብልት ፈሳሽ እና የጡት ወተት በመሳሰሉ የፈሳሽ ልውውጥ መሆኑን ዶክተሮች አስረግጠው ከነገሯት በኋላ ነው እንግዲህ እኔን እንደ ብቸኛ ልጇ ማሳደግ የጀመረችው።

ቀን ቀንን እየወለደ የሕክምና ክትትልን በቋሚነት መውሰድ ስጀመር ደህና እየሆንኩ ሄድኩ። አክስቴም የራሷን ሕይወት ትታ እኔን እንደ ልጇ ማሳደግና መንከባከብ ጀመረች። ወላጆቼ የራሳቸው ቤት ስለ ነበራቸው በኪራይ በምናገኘው ገቢ ዘና ብለን መኖር ጀመርን።

> **እንደዛ በፍቅርና በመከባበር የሚኖሩት እናትና አባቴ አንዴ መንፈስ ነው፤ አንዴ የሰው እጅ ነው በማለት ፈለቀ የተባለ ፀበል በሙሉ አንድም አይቀራቸውም ነበር**

እኔም ለትምህርት ስደርስ ጥሩ የሚባል ትምህርት ቤት ገብቼ መማር ጀመርኩ። ከጓደኞቼ ጋር በደስታ የምጫወት ቢሆንም ከልጅነቴ ጀምሮ መድኃኒት መወሰዴ ግን በጣም ያስጠላኝ ነበር። በተለያዩ ጊዜያት ለክትትል ሆስፒታል ስሄድም ሌሎቹ ልጆች ሐኪም ቤት ብለው ያለመቅረታቸው ውስጤን ይበላው ነበር።

አክስቴ ከሕክምናው ጎን ለጎን በመንፈሳዊ ሕይወት እንድጠነክር አድርጋ ስላሳደገችኝ ሁልጊዜ ተስፋ መቁረጥን አላውቅም ነበር። ሰባተኛ ክፍል ስደርስ ግን ጓደኞቼ መድኃኒት የማይወስዱ መሆኑና እኔ ለምን እንደምወስድ ስጠይቅ የሚመልስለኝ ባለመኖሩ መድኃኒቱን ለመተው ወስንኩ። ያን ጊዜ በጣም የተጨነቀችው አክስቴና ክትትል የሚያደርጉልኝ ሐኪሞች አብረው በመሆን ኤች አይ ቪ በደሜ ውስጥ እንዳለና የግድ መውሰድ እንደሚኖርብኝ አስረዱኝ።

ለመጀመሪያ ጊዜ በደሜ ውስጥ ኤች አይ ቪ እንዳለ ካወኩ እለት ጀምሮ በጣም ነበር ያዘንኩት። በኔ እውቀት ልክ ኤች አይ ቪ የሚይዛቸው ሰዎች ከወንድ ጋር ግንኙነት ያላቸው ናቸው። ለምን እኔን? እያልኩ በጣም ነበር ያዘንኩት።

የኤች አይ ቪ መተላለፊያ መንገዶች ጥንቃቄ በጎደለው ልቅ የግብረ ሥጋ ግንኙነት፤ ኤች አይ ቪ ካለባት እናት ወደ ፅንስ ወይም ልጅ እና በደም አማካኝነት ማለትም በኤች አይ ቪ የተያዘ ሰው ደም በመጠቀም ኤች አይ ቪ ከሰው ወደ ሰው ሊተላለፍ መቻሉን እንኳን ያወኩት ከብዙ ጊዜ በኋላ ነበር።

እኔ ኤች አይ ቪ የያዘኝ ከእናት ወደ ፅንስ ወይም ልጅ የሚተላለፈው መንገድ ነው። ይህም ኤች አይ ቪ ካለባት እናቴ በእርግዝናዋ ወቅት፣ በወሊድ ጊዜ እና ጡት በምታጠባበት ጊዜ ኤች ከአይ ቪው ወደ ፅንሱ/ልጁ ስለተላለፈ እንደሆነ ዶክተሮቹ አስረዱኝ።

በጣም ራሴን ጠልቼ ተስፋ ቆርጬ የነበረ ቢሆንም የነበረኝ ጠንካራ መንፈሳዊ መሠረት በፈጣሪ ላይ ያለኝ እምነት ያንን እንድሻገረው አድርጎኛል።

ራሴን ተቀብዬ ራሴን መንከባከብ ስጀምር ፍፁም ጤነኛ የመሆን ስሜት ይሰማኛል። እንደ ጓደኞቼ ለብሼ አምሬ መውጣት ያስደስተኛል። እስካለሁ ድረስ ጎበዝ ተማሪ ሆኜ ማለፍ ነው የምፈልገው ብዬ በትጋት እማራለሁ። በማትሪክ ውጤት ጥሩ ባመጣም አክስቴ ክፍለ ሀገር ሄጄ እንድማር ስላልፈቀደች እዚሁ አዲስ አበባ ውስጥ በሚገኝ የግል ኮሌጅ ቢዝነስ አድምንስትሬሽን እየተማርኩ እገኛለሁ። በቀጣይ ዓመትም እጨርሳለሁ።

አሁን ላይ በእኔ እድሜ ያሉ ወጣቶች ምንም ዓይነት ግንዛቤ እንደሌላቸው መመልከቴ እጅጉን ያሳስበኛል። ከማሳሰብ አልፎ ግን እኔ እንደዚህ ነኝ ብዬ መውጣት አልፈልግም። ምክንያቱም ከልጅነታችን ጀምሮ አብሪያቸው ያደኩት ጓደኞቼ ይሄንን እንዲያውቁ ጭርሶውንም አልፈልግም።

አንዳንዴ ግን ስለ ፆታዊ ግንኙነት ስናወራ ሁሉም ወጣቶች የሚያሳስባቸው እርግዝና መፈጠር እንጂ ኤች አይ ቪ አለመሆኑ አዲሱ ትውልድ በከፋ ደረጃ ሊጠቃ የሚችልበት አጋጣሚ እንደሚኖር አውቄያለሁ። ኤች አይ ቪ ላይ ያለው ግንዛቤ በአፈላ ወጣቶች ዘንድ እጅግ በጣም አናሳ ነው።

አሁንም ትኩረት ተሰጥቶ እንዲሰራ የምፈለገው ጉዳይ ወጣቶች ስለ ኤች አይ ቪ በቂ ግንዛቤ ኖሯቸው ራሳቸውን መጠበቅ እንዲችሉ ማድረግ ላይ ነው። ወጣቶች ኮንዶም ከመግዛት ይልቅ ፖስት ፒልን መግዛት ላይ ቅድሚያ ሰጥተዋል። በአፍላ እድሜ ግብረ ሥጋ ግንኙነትን መጀመረን እንደ ጀብዱ የሚያዩትም አይጠፉም። ስለዚህ ትኩረት አፍላ ወጣቶች ላይ ተደርጎ ቢሰራ መልካም ይሆናል እላለሁ። በማለት ሰላማዊት ሀሳቧን አካፍላናለች።

ዘንድሮው የኤች አይ ቪ ኤድስ ቀን ሲከበር በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ36ኛ ጊዜ በኢትዮጵያ ደግሞ ለ35ኛ ጊዜ ተከብሯል፡፡ ዕለቱ በተከበረበት ወቅትም የጤና ሚንስትር (ዶ/ር) ሊያ ታደሰ ባደረጉት ንግግር፤ የኤች አይ ቪ ሥርጭትን በመከላከል ረገድ መንግሥትና ማህበረሰቡ ባደረጉት ጥረት ከነበረበት ከፍተኛ የሥርጭት መጠን አሁን ወዳለበት 0.91 በመቶ ማድረስ መቻሉን ገልጸዋል።

የዓለም ሀገራት በ2030 ኤች አይ ቪ ኤድስ ለማኅበረሰብ ሥጋት ወደማይሆንበት ደረጃ ለማድረስ ጥረት እያደረጉ ነው ያሉት ሚንስትሯ፤ በኢትዮጵያ በ2025 ኤች አይ ቪ በደማቸው ከሚገኙ ሰዎች 95 በመቶ የሚሆኑት ተመርምረው እራሳቸውን እንዲያውቁ ማድረግ፣ ኤች አይ ቪ በደማቸው ከሚገኘው ውስጥ 95 በመቶ የሚሆኑት ሕክምና እንዲያገኙ እና ሕክምና ከጀመሩት 95 በመቶ የሚሆኑትን የቫይረሱ መጠን ዝቅ እንዲል የማድረግ ሥራ እንደሚሰራ አስታውቀዋል።

በበዓሉ ላይ የተገኙት በኢትዮጵያ የአሜሪካ አምባሳደር ኤርቪን ጄ ማሲንጋ በበኩላቸው የአሜሪካ ሕዝብ እና መንግሥት ኤች አይ ቪ ኤድስን ለመከላከል እስከ አሁን ከ3 ቢሊየን ዶላር በላይ ባደረጉት ድጋፍ አመርቂ ውጤቶች ተመዝግበዋል፡፡ በቀጣይም የሚደረጉ ድጋፎች እና ህብረተሰቡ የሚያደርገው የመከላከል ሥራ ሊቀጥል ይገባል ብለዋል፡፡

በሌላ መረጃ ደግሞ ዌልስ ውስጥ በሙከራ ላይ የነበረውና በሰውነት ውስጥ የኤች ኤይ ቪ ቫይረስ ሥርጭትን የሚገታው መድኃኒት ውጤታማ መሆኑ በጥናት መረጋገጡም ሰሞንኛው አስደሳች ዜና ነው።

የመድኃኒቱ ውጤታማነት የተረጋገጠው በመላው እንግሊዝ ከተውጣጡ እና በጥናቱ በተካተቱ ከ24 ሺህ በላይ የመድኃኒቱ ተጠቃሚዎች ላይ ምርመራ ከተካሄደ በኋላ መሆኑን ተመራማሪዎቹ ይፋ ሲያደርጉ እንደ ሰላማዊት ላሉ ብዙ ተስፋ ላላቸው ወጣቶች ሊደርስ መቻሉ አስደስቶኛል።

ለሁሉም ግን ታሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ ነውና ወጣቶቻችን ላይ የግንዛቤ ሥራዎችን የመሥራት ኃላፊነታችንን እንወጣ እላለሁ።

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

ሙሉጌታ ብርሃኑ

አዲስ ዘመን ትናንት እንደምን ሰነበተ እያልን ከትውስታ ማህደሩ ቀንጨብ በማድረግ በአዲስ ዘመን ድሮ እናስታውሳቸው ዘንድ ወደናል:: 1965ዓ.ም የኢትዮጵያ አየር መንገድ ንብረት የሆነውን የቦይንግ አውሮፕላን የመጥለፍ ሙከራ ስላደረጉት ወንበዴዎች ከፖሊስ የተሰጠ መግለጫ፣ ባላገሮችን የማታለያ ዘዴው አሁንም ቀጥሏል:: ከወዲህ ደግሞ ማስጠንቀቂያ ለአማርኛ አንባቢያን...ከጳውሎስ ኞኞ ደበዳቤዎችም የተወሰኑትን እናካፍላችኋለን::

አውሮፕላን ለመጥለፍ ስለሞከሩት ወንጀለኞች ከፖሊስ መግለጫ ተሰጠ

ባለፈው ዓርብ የኢትዮጵያ አየር መንገድ አውሮፕላን ለመጥለፍ ሙከራ አድርገው የነበሩትን ወንጀለኞች ዓላማ ለማወቅ የፖሊስ ሠራዊት ሰሞኑን ስለፈጸመው ምርመራ ውጤት ትናንት ከዚህ የሚከተለውን መግለጫ ሰጥቷል።

ኅዳር 29 ቀን 1965ዓ.ም የኢትዮጵያ አየር መንገድ የበረራ መስመር ቁጥር 720 ቦይንግ ጀት አውሮፕላን 94 መንገደኞችና 9 የአውሮፕላኑን ሠራተኞች አሳፍሮ ከጧቱ 1 ሰዓት ተኩል በአሥመራ በኩል ወደ አቴንስ ሮም፣ፓሪስ ለመሔድ ከአዲስ አበባ ተነሥቶ 13 ደቂቃ ያህል እንደበረረ በወቅቱ ማንነታቸው ያልታወቀ ወንበዴዎች ለማስገደድ በመሞከራቸው ከጠዋቱ 2 ሰዓት ከ25 ደቂቃ ተመልሶ አዲስ አበባ ቦሌ ኢንተርናሽናል አውሮፕላን ጣቢያ አርፏል።

ሁኔታው እንደተሰማ ከኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የመንግሥት የፖሊስ ሠራዊት የደረሠው የምርመራ ቡድን በሥፍራ ላይ ተገኝቶ ባደረገው ምርመራ አምስት ወንዶችና ሁለት ሴቶች የጦር መሳሪያና ቦንብ ይዘው ለማስገደድ በመሞከር በአውሮፕላኑ ውስጥ ባስነሱት ተኩስ በተደረገው መከላከል ከአንዷ ሴት በቀር የተቀሩት በሙሉ ተገድለዋል።

**(አዲስ ዘመን ታህሳስ 9 ቀን 1965ዓ.ም)**

### ባላገሮችን ያታለሉ ተፈረደባቸው

“ከሀብታሞች ዘንድ ወስደን ገንዘብ እናሰጣለን” በማለት ከገጠር የሚመጡትን ገበሬዎች ከመንገድ እየጠበቁ አታለው ገንዘብ የወሰዱት ሁለት አታላዮች የ15ዓመት እሥራት ተፈረደባቸው::

ከአሩሲ ጠቅላይ ግዛት ከአርባ ጉጉ አውራጃ የመጡት አቶ ኢንካ አብዲን “ሀብታሞች ለድሃ ገንዘብ ይሰጣሉ” በማለት 30 ብርና አንድ ጋቢ አጭበርብሮ የወሰደው ታደሰ ቢነግዴ የ10 ዓመት እሥራት ትናንት ተፈረደበት:: ከሸዋ ጠቅላይ ግዛት ከሜታ ሮቢ የመጡት አቶ ጒንፋ ሙለታን “ትልልቅ አዛውንት ገንዘባቸውን በነፃ ለሕዝብ ስለሚያድሉ በኪስዎ ያለውን ገንዘብ ከእኔ ዘንድ አስቀምጠው ብዙ ገንዘብ ተቀብለው ሲመጡ ይወስዳሉ” በማለት 100 ብር የወሰደባቸው አሰፋ መንገሻ በ5 ዓመት እሥራት እንዲቀጣ የአዲስ አበባ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ትናንት በየነበት ::

ሁለቱም አታላዮች ወይም እንደፖሊሶቹ አጠራር “እነ ቁጭበሉ” በአዲስ አበባ ከተማ አንዳንድ ባላገሮች በማታለል “ለአርበኞች ፣ለአገለገሉ ፣ለሽመገሉና ምንም ለሌላቸው ሰዎች ገንዘብ በነፃ ይሰጣል:: የያዛችሁትን ሁሉ ከኛ ዘንድ አስቀምጣችሁ ስትመለሱ ትወስዳላችሁ” በማለት ይዘው እየጠፉ የሚያታልሉ መሆናቸው ተመስክሮባቸዋል::

ወንጀለኞቹ ደኅና ልብስ እየለበሱ ታማኞችና ሽማግሌዎች በመምሰል ባላገሮችን “ገንዘብ በነፃ ለመቀበል በምትሄዱበት ጊዜ ተፈትሻችሁ ገንዘብ ከኪሳችሁ የተገኘ እንደሆነ ትወረሳላችሁ፤ደኅና ልብስ የለበሳችሁ እንደሆነ ትገፈፋላችሁ በማለት” የሚያታልሉ መሆናቸው በምስክር ተረጋግጦባቸዋል::

**(አዲስ ዘመን ሰኔ 15 ቀን 1964ዓ.ም )**

### ለአማርኛ አንባቢያን ማስጠንቀቂያ

አቶ ጥላሁን በየነ የተባሉ ሰው በቅርቡ በተጻፈች “ልሳን” በተባለች መጽሐፋቸው ውስጥ”የቀ.ኃ.ሥ ዩኒቨርሲቲ መምህራን የሆኑት ዶክተር ጌታቸው ኃይሌና ዶክተር አብርሃም ደሞዝ መጽሐፌን ከመታተሙ በፊት ባማረና ልዩ ልዩ ጽሑፎችን በማቅረብ እርዳታ ሰጥተውኛል” ብለው መሠረተ ቢስ የሆነ መግለጫ ከመጽሐፉ መግቢያ ላይ አስፍረው ትንሽ የሆነች መጽሐፋቸውን አንዷን በአሥር ብር ሒሳብ ጉዳዩን ለማያውቅ ሕዝብ በመቸብቸብ ላይ ናቸው።

....

እንዲያውም በመጽሐፉ ውስጥ የሚገኘው ስሕተት ከመጠን በላይ የበዛ ስለሆነ ያንን ሁሉ ስሕተት ከማረም አዲስ መጽሐፍ ለመጻፍ የሚቀለን መሆኑን ገልጠን ጊዜያችንን ለማባከን እንደማንፈቅድ አስረድተናቸዋል።

**(አዲስ ዘመን ኅዳር 17 ቀን 1966ዓ.ም)**

### ጥያቄ አለኝ

**ይድረስ ለጳውሉስ ኞኞ**

*ጅማ ሆኜ ሶዶ ያለችውን የምወዳትን ልጅ በሕልሜ የማየው እግዚአብሄር ነው የሚያሰየኝ ወይንስ ሰይጣን?

**እሥራኤል መና (ከሚዛን ተፈሪ)**

-ነገሩ ከአሳብህም ሊሆን ይችላል። ግን ሰይጣን አሳየህ ከማለት እግዚአብሄር አሳየህ ማለት ይሻላል?

*ጥላሁን ገሠሠ በደንብ ስለሚያጫውት ለምን ይሰድቡታል? አንተስ ለምን አዝማሪ ትለዋለህ?

**መ.ፐ (ከአዲስ ከተማ)**

**- ታዲያ ምን ልበለው?**

**(አዲስ ዘመን የካቲት 3 ቀን 1965ዓ.ም)**

*የሴቶች ማኅፀን ወደ ወንዶች ተለወጠ የሚሉትን ነገር ሰማሁ። ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል?

-የተለወጠው ማኅፀን ሳይሆን ወንዱን ሴት አደረጉት። ይህም ተችሎ ተሥነ ሥዕሉ አይተናል። የሰው ልጅ ተራቅቆ ከእንዲህ ያለው ደረጃ በደረሰበት ጊዜ እናንተ ከእዚህ ምቀኛ አስቸገረኝ እያላችሁ ልቤን ውልቅ ታደርጉታላችሁ። ድሀ ድሀን ቢመቀኘው ምን ሊጎዳው? ይልቅስ ለሥራው እንበርታ።

**(አዲስ ዘመን የካቲት 3 ቀን 1965ዓ.ም)**

***ሦስቱ ሀሐን በአንድ ቢጠቃለሉ አይሻልም ወይ?**

**ሁሴን ያሲን**

- ምን ሦስት ብቻ ናቸው? ሰባት ናቸው ሀሃሐሓኀኃኻ እነዚህ ሁሉ አንድ ቢሆኑ እንዴት ጥሩ ነበር። ይህ ነገር እንዲሻሻል በጋዜጣ ላይ ንትርክ የተጀመረው ከዛሬ 50 ዓመት በፊት ጀምሮ ነበር። 1917ዓ.ም ይታተሙ በነበሩ ጋዜጦች ላይ ሁሉ ይቀነሱ በዝተዋል የሚል ክርክር የበዛ ነበር። ግን እስካሁን አልተሻሻሉም። በተለይ በአሁኑ ዘመን ጽሕፈት በመኪና በሚካሄድበት ዘመን ብዙ አስቸግረውናልና ሊሻሻሉ የሚገባ ይመስለኛል።

(አዲስ ዘመን ኅዳር 17 ቀን 1965ዓ.ም)

*ጫት እንደ ጎመን ተሠርቶ ይበላል አሉ:: እውነት ነው?

**ዮናስ ዘሺፍ(ልደታ)**

-ጥሬውን እየቀረደዱት ምን መሥራት ያሻል? ወይንስ ሆዳቸውን እንዳያማቸው::

**(አዲስ ዘመን ኅዳር 10 ቀን 1965ዓ.ም)**

# ዓለም አቀፍ

## የአሜሪካ ጦር መርከብ ቀይ ባሕር ላይ ከየመን የተተኮሱ ድሮኖችን መትቶ መጣሉን ገለጸ

በጋዜጣው ሪፖርተር

የአሜሪካ ጦር መርከብ ሶስት ድሮኖችን ቀይ ባሕር ላይ መትቶ መጣሉን የአሜሪካ ማዕከላዊ ዕዝ ገልጿል።

ድሮኖቹ ሶስቱ የንግድ መርከቦች ላይ ጥቃት ለማድረስ ሲቃጡ ነው የአሜሪካ ጦር መከርብ እርምጃውን የወሰደው።

ከ14 ሃገራት ጋር ግንኙነት ያለው ዩኤስኤስ ካርኒ የተሰኘው የጦር መርከብ እሑድ ዕለት በኢራን ከሚደገፉት የየመን ሁቲ አማፂያን ጋር ሲዋጋ መዋሉ ተሰምቷል።

ማዕከላዊ ዕዙ እንደገለጸው፤ ሁለት የንግድ መርከቦች በሚሳዔል ቢመቱም የተጎዳ ሰው ግን የለም። የሁቲ አማፂያን ቃል አቀባይ ሁለት የእስራኤል መርከቦች ከቡድኑ ባሕር ኃይል ጥቃት እንደደረሰባቸው አሳውቀዋል።

በኢራን የሚደገፉት የሁቲ ታጣቂዎች እ.አ.አ. 2014 መንግሥት ተገልብጦ የእርስ በርስ ጦርነት ከተከሰተ ጀምሮ አንዳንድ የሃገሪቱን ክፍሎች ተቆጣጥረው እየተንቀሳቀሱ ይገኛሉ።

ቡድኑ በተለይ ደግሞ በቅርቡ ከተቀሰቀሰው የእስራኤል ሐማስ ጦርነት በኋላ ቀይ ባሕር ላይ የሚንቀሳቀሱ የእስራኤል መርከቦችን ዒላማ እያደረገ ይገኛል።

የዩናይትድ ስቴትስ ማዕከላዊ ዕዝ እንደገለጸው ፤እሑድ ጠዋት ዩኤስኤስ ካርኒ ፀረ-መርከብ ባሌስቲክ ሚሳዔል ዩኒቲ ኤክስፕሎረር ወደተሰኘ የዩናይትድ ኪንግደም የንግድ መርከብ ተተኩሷል።

ከዚህ ጥቃት በኋላ ሌላ ድሮን ወደ ጦር መርከቡ ቢሰነዘርም ሊያከሽፍ መቻሉን ያሳወቀው ዕዙ ጥቃቱ የአሜሪካ ጦር መርከብን ዒላማ ስለማድረጉ ግን እርግጠኛ አይደለንም ብሏል።

በተመሳሳይ ቀን ከሰዓት ዩኒቲ ኤክስፕሎረር ከሁቲ ቁጥጥር ሥር ከሚገኝ ሥፍራ በተተኮሰ ሚሳዔል ተመትቶ አነስተኛ ጉዳት ደርሶበታል።

የአሜሪካ ጦር መርከብ ሌላ የድሮን ጥቃት እንደተሰነዘረ ከተገነዘበ በኋላ ጥቃቱ ጉዳት ከማድረሱ በፊት መትቶ እንደጣለው ተነግሯል።

ከዚህ ጥቃት በኋላ ደግሞ ሁለት የፓናማ ባንዲራ የሰቀሉ መርከቦች በሚሳዔል ጥቃት እንደተመቱ ተዘግቧል። ዩኤስኤስ ካርኒ እኒህን መከርቦች ለመርዳት እየሄደ ሳለ ሌላ የድሮን ጥቃት ተሰንዝሮ እሱንም ማከሸፉን አሳውቋል።

ማዕከላዊው ዕዝ እንዳለው ጥቃቶቹ መርከቦቹ ላይ የሚሰሩ የበርካታ ሃገራት ዜጎችን “ሕይወት አደጋ ላይ ጥለዋል” ይህ ደግሞ “ለዓለም አቀፍ ንግድና የባሕር ጉዞ ስጋት ነው።”

“አልፎም እኒህ ጥቃቶች የመን ከሚገኙ ሁቲዎች ይሰንዘሩ እንጂ በኢራን እየተደገፉ እንዳለ እናምናለን። ዩናይትድ ስቴትስ ከዓለም አቀፍ አጋሮቿ ጋር በመሆን ተመጣጣኝ ምላሽ እንደምትሰጥ ልንገልጥ እንወዳለን” ብሏል።



በያዝነው ሳምንት መባቻ አሜሪካ፤ ከእስራኤል ጋር ግንኙነት አላቸው የተባሉ መርከቦች ላይ ጥቃት ያደረሱ ታጣቂዎችን በቁጥጥር ሥር ማዋሏን ገልጻ ነበር።

ሁቲዎች ራሳቸውን በኢራን ከሚደገፉ ቡድኖች ጋር “የተቃውሞ ዘንግ” ብለው የሚጠሩ ሲሆን እስራኤል፣ ዩናይትድ ስቴትስና መላው የምዕራቡ ዓለምን የሚቃወሙ ናቸው።

## የዩኬ ጠቅላይ ሚኒስትር ቢቢሲ ከዜጎች የሚሰበስበው ክፍያ እውነታን መሰረት ሲያደርግ እንደሚገባ አሳሰቡ

በጋዜጣው ሪፖርተር

ከፍተኛ የዋጋ ንረት ባለበት በዚህ ወቅት ቢቢሲ ከዜጎች የሚሰበስበው የቴሌቪዥን ግብር ተጨባጭ እውነታን መሰረት ያደረገ ሊሆን ይገባል ሲሉ የዩናይትድ ኪንግድም ጠቅላይ ሚኒስትር ሪሽ ሱናክ ተናግረዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ቢቢሲ የሚሰበሰስበው ክፍያ ተገቢነት ሊኖረው ይገባልም ብለዋል። እስካሁን ባይረጋገጥም በዋጋ ንረት ምክንያት ቢቢሲ ከቀጣዩ የፈረንጆች አዲስ ዓመት ጀምሮ ከዜጎች የሚሰበስበውን ክፍያ እንደሚጨምር ተሰምቷል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ቢቢሲ የሚሰበስበው ክፍያ ዘላቂ ይሆናል ወይ? ተብለው ሲጠየቁ “ነገሮች አስቸጋሪ በሆኑበት ሰዓት ሰዎች የቤተሰባቸውን የኑሮ ውድነት ለማቃለል የሚችሉትን ሁሉ ያደርጋሉ” የሚል ምላሽ ሰጥተዋል።

በዋጋ ንረትና ክፍያው ለሁለት ዓመት ተቋርጦ በመቆየቱ ምክንያት ቢቢሲ በቴሌቪዥን ግብር አማካኝነት 500 ሚሊዮን ፓውንድ የመሰብሰብ ዕቅድ አለው። የቴሌቪዥን ግብር የቢቢሲ ዋነኛ የገንዘብ ምንጭ ነው።

ዱባይ እየተካሄደ በሚገኘው የአየር ንብረት ለውጥ ስብሰባ ላይ እየተሳተፉ የሚገኙት ሱናክ እንደማንኛውም ድርጅት ዜጎችን ማገልገል አለበት ያሉ ሲሆን ክፍያውን በተገቢ መንገድ ሊያደርግ ይገባል ብለዋል።

ሆኖም ጠቅላይ ሚኒስትሩ በቀጥታ የታቀደው የክፍያው መጠን ላይ ገደብ ለማስቀመጥ እንደሚፈልጉ አልተናገሩም።

ቢቢሲ ባለፈው ስምንት ታዋቂውን የምሽት የቴሌቪዥን ፕሮግራሙ ላይ ለውጥ ማድረጉን አስታውቋል። ይህንንም ውሳኔ ብሄራዊ የጋዜጠኞች ማህበር በምርመራ ዜና ላይ ያጋጠመ ትልቅ ክስተት ነው ብሎታል።

ይህ ታዋቂ የቴሌቪዥን ፕሮግራም እውቅ ጋዜጠኞቹን የሚያጣ ሲሆን የሚያካትተውን የ10 ደቂቃ የምርመራ ፕሮግራም ቀንሶ ስቱዲዮ ውስጥ ወደሚደረግ ክርክር ይቀይረዋል።

ከዚህም በተጨማሪ ወጪ ለመቀነስ ቢቢሲ ሌሎች ፕሮግራሞቹ ላይ ለውጥ ያደርጋል። በርካታ የቲቪ ፕሮግራሞችን በመቀነስ ወደ ዲጂታል ጋዜጠኝነትና የቀጥታ ዘገባ ላይ ያተኩራል። በዚህም ለውጥ ቢቢሲ እስከ 7 ነጥብ 5 ሚሊዮን ፓውንድ እንደሚቆጥብ ይጠበቃል።

የቢቢሲ ቃል አቀባይ በአውሮፓውያኑ 2022 መንግሥትና ቢቢሲ የ6 ዓመት የቴሌቪዥን ግብር ለመሰብሰብ መስማማታቸውን ጠቅሷል።

# ዘርፉን ከመንግሥት ጆርባ ለማውረድና ኢኮኖሚያዊ ጥቅሙን ለማጎልበት

ታምራት ተስፋዬ

ስፖርት በተለይ በአሁኑ ወቅት ለስሜት አሊያም በማዝናናት ብቻ አይወሰንም። ጤናማና አምራችና ትውልድ ከማፍራት በተጓዳኝ በርካታ የኅብረተሰብ ክፍልን በቀጥታና ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ ተጠቃሚ ያደርጋል። በርካታ ቢሊዮን ዶላር የሚንቀሳቀስበት ግዙፍ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ሆኖም የሀገራት ዋነኛ የኢኮኖሚ ምንጭና የምጣኔ ሀብት እድገታቸው መዘውር ሆኗል።

የተለያዩ ስፖርቶች በፍቅር ከሚወደዱባቸው ሀገራት መካከል ኢትዮጵያ አንዷ ናት፡፡ በሀገሪቱ ዘመናዊ የስፖርት ውድድሮች መካሄድ ከጀመሩ አንድ ክፍለ ዘመን ሊሞላቸው ተቃርቧል። ይሁንና እነዚህን ሁሉ ዓመታት መመልከት ሳያስፈልገን የቅርቦቹን አስርና አስራ አምስት ዓመታት እንኳን ብንቃኝ የስፖርት ዘርፍ በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ፈሰስ ይደረግለታል።

በመንግሥት ወጪ በርካታ የስፖርት መሰረተ ልማት አውታሮች እየተስፋፉ በተለይ የውድድር ማከናወኛ ግዙፍና ዘመናዊ ስታዲየሞች ተገንብተዋል። የአንዳንዶቹ ግንባታም ቀጥሏል። ከስቴዲየም ግንባታ በተጓዳኝ በተለያዩ ከተሞች የወጣት ስፖርት አካዳሚዎች ተከፍተዋል።

ይህ የሀገሪቱ መንግሥት ስፖርቱን የማጎልበት ዓላማና ሚና መሰረተ ልማቶችን በማስፋፋት ብቻ ተወስኖ የሚቆም ግን አይደለም። በሀገሪቱ የሚገኙ ፌዴሬሽኖች መካከል ከ90 በመቶ በላይ የሚሆኑት በራሳቸው ገቢ መፍጠርና ማምጣት የማይችሉና ከዓመት ዓመት የሥራ ማስኬጃ ድጎማ ለመጠየቅ የመንግሥት በር ከማንኳካት ያልቦዘኑ ናቸው። ይህ እንደመሆኑም የሀገሪቱ መንግሥት በየዓመቱ በሩን ለሚያንኳኩ ፌዴሬሽኖች እጁን አያጥፈም።

ከፌዴሬሽኖች በተጓዳኝ በመንግሥት ተቋማት አሊያም ልማት ድርጅቶች ስር የሚገኙ ክለቦችም በየዓመቱ የዚሁ ድጎማ ተቋዳሽ ናቸው።የራሳቸውን ገቢ በራሳቸው መሸፈን እንኳን ያልሆነላቸው አንዳንድ የመንግሥት ጥገኛ ክለቦች በአንፃሩ ለአንድ ተጫዋች በሚሊዮን የሚቆጠር የፊርማና የወር ደሞዝ ይከፍላሉ። ከሀገር ውስጥ አልፈው ከውጭ ተጫዋቾች ያስመጣሉ።ከዓመት ከዓመት ከቀበሌ ጀምሮ የሚደረጉ ስፖርታዊ ውድድሮች ለማከናወን፤ ለስልጠና ለምልመላ፤ የስፖርት ትጥቆችን ለመግዛት እንዲሁም ለተዋናዮቹ የሚሆን አበል እየተባለ ረብጣ ገንዘብ ፈሰስ ይደረጋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ማንኛውንም ሀገር ከዓለም አቀፍ የስፖርት የሀብት ምንጭ ተጠቃሚ ከሚያደርጉ መንገዶች አንዱና ዋነኛው የስፖርት ኢንቨስትመንት መሆኑ ይታወቃል። የኢትዮጵያን የስፖርት ዘርፍ በዚህ መነፅር ከተመለከትነው ግን እንደ አንድ ኢኮኖሚና ኢንቨስትመንት ሆኖ አናየውም።

ዘርፉ «አክሳሪ አሊያም አትራፊ ነው» የሚለው በቅጡ አይታወቅም። ዘርፉ በሀገሪቱ አጠቃላይ ኢኮኖሚ ውስጥ ያለው ድርሻ ምን ያህል እንደሆነና ለኢንቨስትመንት ያለውን አመቺነት ለመረዳት በዚህ ረገድ የተጠኑ ጥናቶችን መኖር አለመኖራቸውን ማረጋገጥም እጅጉን ከባድ ነው፡፡

ዘርፉ በሀገሪቱ ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት (ጂዲፒ) ውስጥ ትርጉም ያለው ገቢ ማስገኘት ችሏል ወይንስ ጨርሶ በኢኮኖሚ ገቢ ምንጭነት ደረጃ አልደረሰም ለማለትም በቂ መረጃ የለም፡፡ ይህ መረጃ የሀገሪቱን ስፖርት በበላይነት ከሚመራው ተቋም በሪፖርት መልክ ሲቀርብ አይታይም፡፡ አይሰማም፡፡

በእርግጥ አነጋጋሪ ቢሆንም ቀጥታም ሆነ ቀጥተኛ ባልሆነ መልኩ በሀገሪቱ ውስጥ የስፖርቱ ዘርፍ አበርክቶ ሙሉ በሙሉ የለም ማለት አያስደፍርም። በተለይ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ከውድድርነት ተሻግሮ ታላላቅ የግንባታ ፕሮጀክቶች ለማስፈፀም የህዝብ ተሳትፎ ለማጠናከር በሚደረገው ርብርብ ላይ የማስተባበር ሚና እያበረከት ነው። ይህም እንደ አንድ ሀገራዊ ኢኮኖሚያዊ ምንጭ ሊወሰድ የሚገባው ነው። ይሁንና ይህም ቢሆን ቦግ ጭለም የሚል እንደመሆኑ የዘርፉን አበርክቶ ውስን አድርጎታል።

ሌላው ከሥራ ፈጠራ አንፃር ነው። ስፖርት በሀገር እድገት ከሥራ እድል ፈጠራ አኳያ ያለው ፋይዳ በአንድና በሁለት ደረጃ ተጠቅሶ የሚቆም አይደለም። ለአብነት በኮንስትራክሽን ዘርፍ አንድ ስታዲየም ሲገነባ በአማካኝ ለብዙ ሺ ዜጎች የሥራ እድልን የመፍጠር አቅም አለው። ሥራ እጥነትን መቅረፍ በራሱ አንድ የኢኮኖሚ አስተዋጽኦ ነው። ይሁንና በሥራ እድል ፈጠራም ቢሆን የሀገራችን የስፖርት ሴክተር ምን ያህል ሰዎችን በስሩ አቅፏል ለምን ያህል ዜጎችስ የሥራ እድል ፈጥሯል የሚለው በቅጡ የሚታወቅ አይመስለኝም።

በእርግጥ ስፖርቱ ከተሞች እንዲለሙ ምክንያት እየሆነ ነው። ትላልቅና ዓለም አቀፋዊ ይዘትን የተላበሱ ስታዲየሞች ግንባታ መገንባት ሌሎች የመሰረተ ልማት ግንባታዎች ጎን ለጎን እንዲገነቡ መልካም አጋጣሚ ይፈጥራል። ይህም ትልቅ የልማት በርን በመክፈት የስታዲየሙ ግንባታ በሰፈረበት ከተማ ውበትና ኢኮሚኖሚያዊ እድገት የራሱን አስተዋጽኦ እንደሚፈጥር የሚካድ አይደለም፡፡

ይሁንና እነዚህ የስፖርት መሰረተ ልማቶች ከሚሰጡት ስፖርታዊ አገልግሎት በተጨማሪ እንዴት ተጓዳኝ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም መስጠት ይችላሉ? እንዴትስ እየሰጡ ነው? የመሰረተ ልማቱን ያህል ስፖርቱን ኢኮኖሚ ማድረግ የሚችል ተመጣጣኝ አሰራርና አመራር እንዲሁም ስፖርተኛ አፍርተናል? ስፖርቱ ከሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ ፖለቲካዊና ማህበራዊ እድገት አንፃር እየተጋዘ ነው ወይንስ ተንቀራፏል? የሚለውን ጥያቄ ለጠየቀ መልሱን ማግኘት ቀላል አይሆንለትም፡፡

በቅርቡ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ቆይታ ያደረጉት የባህልና ስፖርት ሚኒስትሩ አቶ ቀጀላ መርዳሳም ይህን ታሪክ ለመለወጥና የስፖርት ዘርፉ ከድጋፍ ወጥቶ በሀገራዊ ኢኮኖሚ ዕድገት ላይ አስተዋጽኦ እንዲኖረው ለማድረግ አቅጣጫ ተቀምጦ ሥራዎች መጀመራቸውን አሳውቀዋል፡፡፡

«የብዙ ሀገራት ተሞክሮ የሚያሳየው ስፖርት የገቢ ምንጭ ሆኖ ሀገራዊ ጥቅም እያስገኘ ነው፡፡ መንግሥት ስፖርትን ከመደገፍ አልፎ ዘርፉ በራሱ መንግሥትን እንዲደግፍ መሥራት ያስፈልጋል።» ያሉት አቶ ቀጄላ፤ በኢትዮጵያም ዘርፉን ለኢንቨስመንት ክፍት በማድረግ ተጠቃሚ ለመሆን እየተንቀሳቀሰች መሆኑንም ነው የጠቆሙት፡፡

እርሳቸው እንደነገሩንም፣ እስካሁን ሲሠራበት የቆየው ስፖርትን ማልማት በሚል አካሄድ ነበር። አሁን ግን ስፖርትን ለልማት ማዋል የሚቻልበት አቅጣጫ ተቀምጧል፡፡ በዚሁ መሠረትም በዘርፉ ለሚሰማሩ ኢንቨስተሮች ምቹ በማድረግ ስፖርቱ ከድጋፍ ወጥቶ በሀገራዊ የኢኮኖሚ ዕድገት ላይ አስተዋጽኦ እንዲኖረው እየተሠራ ነው፡፡

ይህ ስፖርቱን ከኢንቨስትመንት ጋር ለማስተሳሰር የተጀመረ እንቅስቃሴ ይበል የሚያሰኝ ነው፡፡ይሁንና በተለይም ክለቦችን ከመንግሥት ጀርባ የማውረድ ተግባር ጊዜ ሊሰጠው የሚገባ እንዳልሆነ ሊታሰብበት ይገባል፡፡ ስፖርትን ወደ ኢንቨስትመንት ለመቀየር ከሚረዱ አማራጮች መካከልም ክለቦች በሕዝባዊ መሰረት እንዲታቀፉ ማድረግ አንደኛው ነው፡፡

እንደሚታወቀው ክለቦች በውድድር መድረኮች ለሚኖራቸው ውጤታማነትና ቆይታ በተለይም ለህልውናቸው ቀጣይነት የሚከተሉት የክለብ አደረጃጀት እጅግ ወሳኙን ድርሻ ይወስዳል። የክለቦችን አደረጃጀትና አመራር ቀጣይነትና መሰረት ባለው መልኩ ሕዝባዊ መሰረተን የተከተለ እንዲሆን ማድረግ ደግሞ ውጤታማነትን የላቀ የማድረግ አቅሙ ግዙፍ ነው፡፡

**ስፖርቱ ባለበት ስለመርገጡ ስለተደረገው፤ያልተደረገው አሊያም የማይደረገው ጥያቄ ሲናሳ መልሳችን ሰበብ ከሆነ በሞተ ትናንትና ባልተወለደ ነገ መሃል መሆናችንን መረዳት አለብን፡፡ከዚህ ቅርቃር ለመውጣት ደግሞ ዘርፉ እንዴት ይለወጣል? የሚለውን ብቻ ሳይሆን ክፍተቱንም ለመመልከት ዝግጁ መሆን እና የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት የግድ ይለናል**

በሀገር አቀፍ ደረጃ የወጣው የስፖርት ፖሊሲ፣ ክለቦች ደረጃ በደረጃ በሂደት ህዝባዊ አደረጃጀት እንዲኖራቸው ይደግፋል፡፡ የፖሊሲው ፍላጎትና የትኩረት አቅጣጫም የስፖርት አጠቃላይ እንቅስቃሴ፤ አደረጃጀትና አመራር ህዝባዊ መሰረት እንዲኖረው ነው።

ከዚህ በተጓዳኝ ስፖርቱ ከመንግሥት በጀትና ድጎማ ደረጃ በደረጃ የሚላቀቁበትና ራሱን የሚችልበት ምቹ ሁኔታ መፍጠርንም ይመለከታል። ይሁንና አሁን ላይ እንደሚታየው ከሆነ ጥቂት ከሚባሉት በስተቀር አብዛኞቹ የሀገሪቱ ክለቦች በመንግሥት ስር የተደበቁና ህዝባዊ አደረጃጀት የሌላቸው ናቸው።

ዘጠና በመቶ የሚሆኑት የሚተዳደሩም በመንግሥት የልማት ድርጅቶች ስር ነው። ይህ እንደመሆኑም ከመንግሥት የገንዘብ ድጎማ የተላቀቁ አይደሉም። ከመንግሥት ከሚመደብላቸው ውስን በጀት ውጪ የራሳቸው የሆነ ቋሚ የገቢ ምንጭ የላቸውም። የራሳቸው ቋሚ ገቢ ለመፍጠር የሚያስችሉ አሰራሮችን የሚተገብሩም አይደሉም።

ለአብነት እግር ካስን ብንመለከት አብዛኞቹ በሀገሪቱ የሚገኙ ክለቦቹ በመንግሥት ድጎማ የሚንቀሳቀሱና ህልውናቸውና አደረጃጀታቸው የመሰረቱ ናቸው፡፡ በዚህም ምክንያትነት የመንግሥት ድጎማ ሲቀር የክለቦቹ አደረጃጀትም አብሮ ይቀራል። የመንግሥት መዋቅር ሲስተካከልና ሲለዋወጥ ክለቦቹም አብረው ይለወጣሉ። አሊያም ይፈርሳል።

አብዛኞቹ ክለቦችም በመንግሥት የልማት ድርጅቶች የሚተዳደሩ እንደመሆናቸው ለአብነት የአንድ ፋብሪካ መዋቅር ሲቀየር ክለቦቹም አብረው ይቀየራሉ። አሊያም ስለስፖርት ጥሩ አመለካከት የሌለው አመራር ወደ ፋብሪካ በአመራርነት ከመጣ በግለሰብም ፍላጎት ሳይቀር ህልውናቸው አክትሞ ሊፈርሱ ይችላሉ። በዚህ ሂደት ለመፍረስ የበቁም አሉ። ለዚህ ደግሞ በርካታ ክለቦች ምሳሌ ይሆኑናል።

አሁን ላይ በሀገሪቱ በሁሉም ክልሎች የከነማ ክለቦች አሉ። የእነዚህ ክለቦችም አደረጃጀትም ተመሳሳይ ነው። ሙሉ በሙሉ በሚባል መልኩ የራሳቸው የሆነ ቋሚ ገቢ የሌላቸውና የክልል ከተማ አስተዳደር በቀጥታ ኢንቨስት የሚያደርግባቸው ናቸው።ከድጎማና ጣልቃ ገብነት የተላቀቁም አይደሉም።

የዚህ የክለቦችና የመንግሥት ያልተገባ ጥምረት መቀጠልም በርካታ ምክንያቶች ይነሳሉ፡፡ በተለይ መንግሥት ክለቦችን ምን ያህል እየደጎመ ማቆየት እንደሚቻል ያስቀመጠው የጊዜ ገደብ አለመኖሩ ዋነኛው ተጠያቂ እንዲሆንና ለችግሩ ዘላቂነት የጎላውን ድርሻ እንዲወስድ ያደርገዋል። ይህ ድክመቱም፤ ክለቦች በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ ልክ ቀጣይ አደረጃጀታቸውን የሚመለከት አቅጣጫ እንዳይቀይሱና ባሉበት ደረጃ ሁሌም እንዲመላለሱ አብይ ምክንያት ሆኗል።


ክለቦችም ቢሆን የመንግሥት ድጎማ ተመችቷቸዋልና ሌሎች አማራጮችን ላለመመልከት አይናቸውን ሸፍነዋል። የህልውናቸው ቀጣይነት የሚመሰረተው በመንግሥት ድጎማ የተለቀቀ አደረጃጀት ሲከተሉ መሆኑን ረስተዋል።በዚህም ምክንያት አደረጃጀታቸውን የሚመለከት ቀጣይ አቅጣጫ ሲቀይሱ አይስተዋልም።

ዘላቂ ውጤት ባለው መሰረት ላይ የተሻለ ሕዝባዊ አደረጃጀት፤ አሰራር ሥርዓትና የራሳቸው ቋሚ የገቢ ምንጭ ለመፍጠር አይንቀሳቀሱም፡፡ ስፖርቱን ከኢንቨስትመንት ጋር ለማስተሳሰርና ኢኮኖሚያዊ አበርክቶውን ከፍ ለማድረግ ከተፈለገ መሰል ችግሮች ልዩ ትኩረትና መፍትሄ ሊሰጣቸው የግድ ነው፡፡

ስፖርቱ ባለበት ስለመርገጡ ስለተደረገው፤ ያልተደረገው አሊያም የማይደረገው ጥያቄ ሲናሳ መልሳችን ሰበብ ከሆነ በሞተ ትናንትና ባልተወለደ ነገ መሃል መሆናችንን መረዳት አለብን። ከዚህ ቅርቃር ለመውጣት ደግሞ ዘርፉ እንዴት ይለወጣል?የሚለውን ብቻ ሳይሆን ክፍተቱንም ለመመልከት ዝግጁ መሆን እና የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት የግድ ይለናል፡፡

ከሁሉ በላይ መንግሥት እየደጎመ የሚያወዳድራቸው ክለቦች ከጥገኝነት ተላቀው ራሳቸውን እንዲችሉ ማድረግ አለበት። መንግሥትም ክለቦችን እየደጎመ መቀጠል የለበትም። ስፖርቱን ሕዝብና ክለቦቹ በጋራ እንዲመሩት ማድረግ ይኖርበታል። መስራት ያለበት እነዚህ አካላት የሀገሪቱን ህግና ደንብ አክበረው የሚሰሩበትን እድል መፍጠር ነው። ክለቦችም ከመደጎም የሚላቀቁበት የመውጫ ስትራቴጂ ሊያዘጋጁ የግድ ይላል። ክለቦች ሕዝባዊ አደረጃጀቶች ለመተግበር መንቀሳቀስና የራሳቸው የሆነ የገቢ ምንጭ በአስተማማኝ ሁኔታ መገንባት ላይ ትኩረት ሠጥተው ሊሠሩ ይገባል።

# ስፖርት



# መቀሌ ሰባ እንደርታን ለማጠናከር የተጀመረው ጥረት

**ብርሃን ፈይሳ**

በ2012 ዓ.ም የውድድር ዘመን በኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግ ተፎካካሪ ከነበሩ ክለቦች መካከል ሦስቱ የትግራይ ክልል ክለቦች መቀሌ ሰባ እንደርታ፣ ስሁል ሽረ እና ወልዋሎ አዲግራት ዩኒቨርሲቲ ዋነኞቹ ነበሩ፡፡ እነዚህ ክለቦች የሊጉ ድምቀት ከመሆን ባለፈ ጠንካራ የዋንጫ ተፎካካሪም እንደነበሩ ይታወሳል። ተሰጥኦ ያላቸውና ጠንካራ ተጫዋቾችን ለብሄራዊ ቡድን እንዲሁም በአጠቃላይ ለኢትዮጵያ እግር ኳስ በማፍራትም የራሳቸውን አስተዋፅኦ ማበርከት ችለዋል፡፡

ሦስቱ ክለቦች በትግራይ ክልል በነበረው ጦርነት ምክንያት ውድድራቸውን ለማቋረጥና ተጫዋቾቻቸውንም ለመበተን ተገደዋል፡፡ ባለፈው ዓመት የተደረሰበትን የሰላም ስምምነት ተከትሎም ክለቦቹን ወደ ውድድር ለመመለስ ጥያቄ አቅርበው ነበር፡፡ የክለቦቹ ጥያቄ እስከተያዘው የውድድር ዓመት ተቀባይነት ባያገኝም ወደ ቀደመ አቋማቸው ለመመለስ የተለያዩ ጥረቶችን እያደረጉ ይገኛሉ፡፡

በ2011 ዓ.ም የኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግ ቻምፒዮን የነበረው መቀሌ ሰባ እንደርታ እግር ኳስ ክለብ አሁንም በብዙ ፈተናዎች ውስጥ እንደሚገኝ ሥራ አስኪያጁ አቶ ሽፈራው ተክለሃይማኖት ይናገራሉ፡፡

አቶ ሽፈራው እንደሚናገሩት፣ ዓለም አቀፉ የኮሮና ቫይረስ ስርጭትን ተከትሎ የተነሳው የሰሜኑ ጦርነት ስፖርትን ጨምሮ በተለያዩ ዘርፎች በርካታ ጥፋቶችን አድርሷል፡፡ በዚህም አብዛኞዎቹ



የኢትዮጵያ እግር ኳስ ክለቦች በመንግሥት ተደጓሚ እንደመሆናቸው በነዚህ ችግሮች በእጅጉ ተፈትነዋል፡፡ በተለይም የክልሉ ክለቦች ተጨማሪ ችግር መጋፈጣቸው የግድ ሆኗል። በአሁኑ ወቅትም በመቀሌ ከተማ አስተዳደር ይደጎም የነበረው የክለቡ ድጋፍ የተቋረጠ ሲሆን፤ ከስፖርት ንግድ ይገኝ የነበረውም ገቢም አሁን ላይ የለም፡፡ ይህ ሁኔታ ተደማምሮም ክለቦቹን ወደ መፍረስ አዝማሚያ እንዲቃረቡ አድርጓል፡፡ በርካታ ደጋፊዎች ያሉት መቀሌ ለ30 ወራት ደመወዝ መክፈል አልቻለም ነበር፡፡ በዚህ ዓመት የክለቦች ምዝገባ ቢኖርም ኖሮ ክለቡ አቅም አልነበረውም፡፡ አሁንም ዋናው ቡድን ቀርቶ ለታዳጊ ቡድኑ እንኳን ማሊያና ኳስ ለማቅረብ ያልተቻለበት ሁኔታ ላይ እንደሚገኝም ሥራ አስኪያጁ ያስረዳሉ፡፡

የክለቦቹን በዚህ ሁኔታ መገኘትና የቀድሞ ተጫዋቾችን መበተን ተከትሎም ስፖርቱን የመደገፍ እንቅስቃሴዎች በተለያዩ አካላት መጀመራቸው ይታወቃል፡፡ በተለይም የፕሪምየር ሊጉ ተሳታፊ የነበሩ ክለቦችን ከመፍረስ የመታደግ ዓላማ በማንገብ ‹‹ክለቦቻችንን እንታደግ›› በሚል ንቅናቄ የገቢ ማሰባሰቢያ ቴሌቶን እና ሌሎች የገቢ ማስገኛ መንገዶችን በሀገር ውስጥ እና በውጪ በሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንን ለማሳተፍ ታቅዶ ሰፊ እንቅስቃሴ ተጀምሮ ነበር፡፡

በጦርነቱ ምክንያት ከፍተኛ ውድመት ያስተናገዱትን ክለቦች መልሶ ለማጠናከር በዚህ የሀብት ማሰባሰብ እንቅስቃሴ የተጓዙበትን ርቀት ሥራ አስኪያጁ ሲያብራሩ፤ ካለፈው ዓመት ግንቦት ወር አንስቶ እንቅስቃሴው እንደተጀመረ ይናገራሉ፡፡ መቀሌ ሰባ እንደርታ እግር ኳስ ክለብ ከአንድ ተቋም ጋር በመሆን የገቢ ማሰባሰብ ሥራውን ለማከናወን ውል ቢያስርም በተለያየ ምክንያት ሊዘገይ ችሏል። ነገር ግን የስፖርት ቤተሰቡ እንዲሁም ተቋማት በሚያደርጉት ርብርብ እቅዱ በቅርቡ ግቡን ሊመታ ይችላል የሚል ተስፋ አላቸው፡፡

ውድድርን በሚመለከትም የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ቀድሞ በሊጉ ተሳታፊ የነበሩ ክለቦች በህጉ መሰረት ከዓመታት በኋላ ‹‹ወደ ውድድር እንመለስ›› የሚለውን ጥያቄ ውድቅ ማድረጉ የሚታወስ ነው። በዚህ ውሳኔ ያልተስማሙት ክለቦችም፤ በፕሪቶሪያ የተደረሰው የሰላም ስምምነት ከሚያካትታቸው ጉዳዮች መካከል እንደዘርፍ ስፖርትንም ታሳቢ ሊያደርግ ይገባል የሚል አመለካከት በማራመድ ላይ ይገኛሉ፡፡ ክለቦቹ ወደ ከፍተኛ ሊግ እንዲወርዱ መደረጋቸው ‹‹ፍርደ ገምድልነት ነው›› የሚሉት ሥራ አስኪያጁ፤ ሁኔታዎችን ታሳቢ ያላደረገ ውሳኔ ነው ሲሉ ቅሬታ ያቀርባሉ፡፡ በመሆኑም ሊግ ካምፓኒውና ፌዴሬሽኑ ይህንን ከግንዛቤ በማስገባት የሰላም ስምምነቱ፤ ተቋማትን ወደነበሩበት መመለስ የሚል በመሆኑ ይኸው ሁኔታ ተቀባይነትን አግኝቶ በቀጣዩ ዓመት ወደ ሊጉ እንዲመለሱ ማድረግ እንደሚገባቸው ያስረዳሉ፡፡

ክለቦቹ በዚህ የውድድር ዓመት እንዳቀዱት ወደነበሩበት መመለስ ባይችሉም በ2017 ዓ.ም በሀብት ደረጃ በመላው ኢትዮጵያውያንና መንግሥት ድጋፍ በሁለት እግራቸው የሚቆሙበት ዓመት እንደሚሆንም ሥራ አስኪያጁ ያላቸውን ተስፋ ተናግረዋል፡፡ ለዚህም ዘንድሮ የተለያዩ ሥራዎች እየተከናወኑ ሲሆን፤ እንደ መቀሌ ሰባ እንደርታ ክለብ ደግሞ ወደ ደመቀበት መድረክ ይመለሳል የሚል እምነት አላቸው፡፡ መቀሌ ሰባ እንደርታ ጠንካራ ተፎካካሪና በርካታ ቁጥር ያለው ደጋፊ ባለቤት ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ዓመት ሀብት በማሰባሰብ፣ አሰልጣኝና ተጫዋቾች በመመልመልና በማደራጀት ላይ ትኩረቱን እንደሚያደርግም ጠቁመዋል፡፡

# የጨረታ ማስታወቂያ

## የጨረታ ቁጥር፡- 01/2016

የክልሉ ስፖርት ኮሚሽን ለ2016 በጀት ዓመት አገልግሎት የሚውል ጥራትና ደረጃውን የጠበቀ የስፖርት ትጥቅ ቁሳቁስና አልባሳትን በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል፡፡ ለዚሁም ተጫራቾች ቀጥሎ በተመለከተው መስፈርት መሠረት ጨረታውን መግዛት ይችላሉ፡፡ **ስለሆነም ተጫራቾች ማሟላት ያለባቸው መስፈርቶች**

1.ተጫራቾች በጨረታው ለመወዳደር የታደሰ የዘመኑን ንግድ ፈቃድ፣ የአቅራቢነት ሠርተፍኬት ያለው በክልል (በፌዴራል) ደረጃ የተመዘገበበት ተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ ሠርተፍኬት የግብር ከፋይነት ሠርተፍኬት ያላቸው ከጨረታ ውድድር ያልታገዱ መሆን ይገባቸዋል፡

2.ተጫራቾች የጨረታው ሠነድ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለተከታታይ 15 ቀናት ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ፋና ብሮድካስቲንግ ፊት ለፊት ከሚገኘው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ባህልና ስፖርት ኮሚሽን ግዥ/ፋይ/ንብ/አስ/ ዳይሬክቶሬት ቢሮ ጨረታዎች ለእያንዳንዳቸው የማይመለስ ብር 150 /አንድ መቶ ሃምሳ ብር /የኢትዮጵያ ብር በመክፈል የጨረታ ሠነድ መግዛት ይችላሉ፡፡

3. ተጫራቾች በተራ ቁጥር 1 ላይ የተጠቀሱትን መስፈርቶችንና የሚወዳደሩበትን የአንዱን ዕቃ ነጠላ ዋጋ ከቫት በፊትና ከቫት በኋላ ያለውን በትክክል በማስላት በአንድ ኦሪጅናል እና በሁለቱ ኮፒ ለያይተው በየወስጥ ገፆች እና በየፖስታው ጀርባ በድርጅቱ ህጋዊ ስልጣን ባለው አካል አጭር ፊርማና ክብ ማህተም በማሳረፍ በሰም በታሸገው ኤንቨሎፕ አሽገው ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀው የጨረታ ሣጥን ውስጥ እስከ 16ኛው ቀን ከጠዋቱ 4፡30 ድረስ ማስገባት ይችላሉ፡፡

4.ተወዳደሪ ድርጅቶች በሚወዳደሩበት ዕቃ ናሙና ጨረታው በሚከፈትበት ቀን ጠዋት ላይ ቀደም ብለው ከጠዋቱ 2፡30 -4:00 ባለው ጊዜ ይዘው የዕቃ ዝርዝር በኮፒ አዘጋጅተው በማቅረብ ማስረከብ አለባቸው፡፡ በባህሪያቸው ክብደት ያላቸው ዕቃዎች በየስቶካቸው መለየት ይችላሉ፡፡

5.ጨረታው ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወክሎቻቸው በተገኙበት ጨረታው አየር ላይ ከዋለበት አንስቶ በተከታታይ ቀናት በሚቆጠር በአስራ ስድስተኛው ቀን ከጠዋቱ ልክ 4፡30 ላይ ታሽጎ ወዲያው 5፡00 ሰዓት ላይ ጨረታዎች ይከፈታሉ፡፡ ዕለቱ የሥራ ቀን ላይ ካልዋለ በቀጣይ ቀናት በተመሳሳይ ሰዓት ይከናወናል፡፡ የጨረታ ሣጥኑ ከታሸገ በኋላ በሚቀርብ የጨረታ ሠነድ ተቀባይነት የለውም፡፡

6.ተጫራቾች ከጨረታው ሠነድ ጋር ተያይዞ የሚሰጣቸውን የተጫራቾች መመሪያን ማንበብና መተግበር አለባቸው፡፡

7.ተወዳደሪዎች የጨረታ ማስከበሪያ ለእያንዳንዱ ጨረታ 5,000(አምስትሺህ ብር) ህጋዊ ሰውነት ካለው ባንክ በሲፒኦ ወይም በጥሬ ገንዘብ ማስያዝ አለባቸው፡፡ የሚዘጋጀው ሲፒኦ ለስፖርት ትጥቅና ቁሳቁስ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መንግስት ስፖርት ኮሚሽን ስም ሲሆን ውድድሩ እንዳበቃ ለተሸናፊ ድርጅቶች ያስያዙት ሲፒኦ ተመላሽ ይደረጋል፡፡

8. አሸናፊ ድርጅቶች ባሸነፉባቸው ጠቅላላ ዋጋ የውል ማስከበሪያ ሲፒኦ 10% ለእያንዳንዱ ጨረታ ማስያዝ ይገባቸዋል፡፡ አሸናፊ ድርጅቶች በመንግስት የግዥ መመሪያ መሠረት የሽያጭ አገልግሎት ዊዝሆልድንግ ዋጋን መክፈል ይገባቸዋል፡

9. አሸናፊ ድርጅቶች አሸናፊ መሆናቸው ከተገለፀበት ጊዜ ጀምሮ 8 ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ውል መግባት፤ ውል በገቡ በ15 ቀናት ውስጥ ዕቃዎችን ሙሉ በሙሉ ማስረከብ አለባቸው፡፡

10. የመንግስት ግዥ አዋጅና መመሪያዎች ግዴታቸውን በማይወጡት አሸናፊ ተጫራቾች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

11.አሸናፊ ድርጅቶች ባቀረቡትና ተቀባይነት ባገኘው ናሙና አሸናፊ በሆኑባቸው ዕቃዎች ዓይነት ፣ጥራትና መጠን ጠብቀው ማቅረብ አለባቸው፡፡

12. የክፍያ ሁኔታ በሚመለከት ቢሮው ዕቃዎችን እንደተረከበ በትራንስፈር ፣በቼክ ወይም በጥሬ ገንዘብ ወዲያውኑ ለድርጅቶቹ ክፍያን ይፈፅማል፡፡ በዚህ ጨረታ የቅድመ ክፍያ ጥያቄ ማቅረብ አይቻልም፡፡ የማስረከቢያው ቦታ አ/አበባ ሰሜን ሆቴል አከባቢ 3ኛ ፖሊስ ጣቢያ ፊት ለፊት ዮናታን ፔንሲዮን ውስጥ ይሆናል፡፡

13. በነጠላና በድምር ዋጋ መካከል ልዩነት ቢፈጠር የነጠላ ዋጋ ገዥ ይሆናል፡፡

14. ስርዝ ድልዝ ያለበት ዋጋ ማቅረብ ተቀባይነት የለውም፣

15.ጨረታውን የሚፈርመው አካል ወኪሉ ከሆነ የውክልና ደብዳቤ መያያዝ አለበት፣

16.የጨረታው ዋጋ ጸንቶ የሚቆየው የጨረታው ውድድር ከተጠናቀቀ በኃላ በስድስተኛ ወር ጸንቶ ይቆያል፣

17.ማንኛውም ተጫራች በሌላ ተጫራች በተሰጠው ዋጋ ላይ ተንተርሶ ዋጋ ማቅረብ አይችልም፣

18.ተጫራቾች ለበለጠ መረጃ 057-775-2431 እና 0911535379 /0917-13-15-35 መጠቀም ይችላሉ፣

19 ኮሚሽኑ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

## በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት ስፖርት ኮሚሽን